# አማርኛ

## ቋንቋ የተማሪ መጽሐፍ



## ፱ኛ ክፍል

# አማርኛ

# ቋንቋ የተማሪ መጽሐፍ

# (፱ኛ) ክፍል

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ


አዘጋጆች

ሲሳይ ቴሌ ቲና

አየለ አለማየሁ ባንጃው

ጌትነት ገነቴ እጅጉ

ገምጋሚዎችና አርታኢዎች

መስፍን ደፈረሱ ወ/መድህን

ትንቢት ግርማ ሀይሉ

ዳንኤል አስራት መንግሥቴ

ፋሲል ብዙነህ በቀለ

ጥራት ተቆጣጣሪና ገምጋሚ

ፍሬሕይወት አሰፋ ከበደ

አስተባባሪ

ጌታቸው ታለማ አጥናፉ

አቀማመጥ እና ስዕል

እንጦጦ ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጅ

(TMS)

© የመጽሐፉ ህጋዊ ቅጂ ባለቤት 2014 ዓ.ም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ ነው፡፡

## ምስጋና

ይህን የትምህርት መጽሐፍ ከዝግጅት ጀምሮ በከተማችን በሚያስተምሩ መምህራን እንዲዘጋጅ በማድረግ ፣ አስፈላጊውን በጀት በማስፈቀድ እንዲሁም በጥብቅ ዲስፕሊን እንዲመራ ላደረጉት ከፍተኛ ሙያዊና አስተዳደራዊ ድጋፍ ላደረጉት ለትምህርት ቢሮ ኃላፊ ለዶ/ር ዘላለም ሙላቱ ፣ እንዲሁም የዝግጅቱ ስራ ቁልፍ ስራ መሆኑን ተረድተው ትኩረት በመስጠት በሚያጋጥሙ ችግሮች መፍትሄ በመስጠት ፣ የአፈጻጸም ሂደቱን በመከታተል፣በመገምገምሁሌም ከጎናችን ለነበሩ የትምህርት ቢሮ የማኔጅመንት አባላት የስርዓተ ትምህርት ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ አድማሱ ደቻሳ፣የትምህርት ቴክኖሎጂ ዘርፍ ምክትል ቢሮ ኃላፊ አቶ ዳኛው ገብሩ፣ የመምህራን ልማት ዘርፍ ምክትል ቢሮኃላፊ አቶ ሳምሶን መለሰ ፣ ለትምህርት ቢሮ ኃላፊ አማካሪ ወ/ሮ አበበች ነጋሽ ፣ለትምህርት ቢሮ ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ ሲሳይ እንዳለ ፣ ለቴክኒክ አማካሪ አቶ ደስታ መርሻ ላበረከቱት አስተዋጽኦ ምስጋና ይገባቸዋል፡፡

በመጨረሻም መጽሐፉ ተጀምሮ እስኪጠናቀቅ ድረስ የትምህርት ቤት ርዕሰ መምህራን ለአዘጋጅ መምህራን ከዚህ በላይ ስራ የለም በማለት ፍቃድ በመስጠትና የሞራል ድጋፍ ስላደረጋችሁም ምስጋናችን እናቀርባለን፡፡

# ማውጫ


| ይዘት | ገጽ |
| --- | --- |
| መግቢያ | I |
| ምዕራፍ አንድ፡- ቋንቋ | 1 |
| ምዕራፍ ኹለት፡- ግብር | 21 |
| ምዕራፍ ሦስት፡- ማዕድን ማውጣት | 41 |
| ምዕራፍ አራት፡- ልቦለድ | 57 |
| ምዕራፍ አምስት፡- ቃላዊ ስነፅሑፍ | 73 |
| ምዕራፍ ስድስት፡- ግጥም | 88 |
| ምዕራፍ ሰባት፡- ኮቪድ -19 (ኮሮና) | 104 |
| ምዕራፍ ስምንት፡- ተውኔት | 120 |
| ምዕራፍ ዘጠኝ፡- ማህበራዊ መገናኛ ብዙኃን እና ተግባቦት | 146 |
| ሙዳዬ ቃላት | |
| ዋቢ ጽሑፎች | |
| የአማርኛ የፊደል ገበታ | |
| የኢትዮጵያ ቁጥሮች /የአማርኛ ቁጥር/ | |

# መግቢያ

የቋንቋ ትምህርት ዋነኛ ዓላማ የተማሪዎችን የማዳመጥ፣ የመናገር፣የማንበብ እና የመጻፍ ክሂልን ማዳበር፣እንዲሁም የዕውቀት ዘርፍ የሆኑትን የስነጽሑፍ እና የስነልሳን ዕውቀትን ማዳበር ነው፡፡ እነዚህን ዓላማዎች ለማሳካት በመርሀ ትምህርቱ ላይ የማዳመጥ፣ የመናገር፣ የማንበብ እና የመጻፍ ክሂልን ለማዳበር፣ እንዲሁም የቃላት እና የሰዋስው ዕውቀትን ለማጎልበት የሚያስችሉ ይዘቶች ተካተዋል፡፡

የቋንቋን ትምህርት ዋነኛ ዓላማዎች ለማሳካት ከሚያስችሉ የማስተማሪያ መሳሪያዎች ውስጥ አንዱ የተማሪው መማሪያ መጽሐፍ ነው፡፡ የተማሪው መማሪያ መጽሐፍ እንዲለወጥ ወይም በአዲስ መልክ እንዲዘጋጅ የሚያችሉ በርካታ ነገሮች አሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ አንዱ የመርሀ ትምህርት ማሻሻል ወይም ለውጥ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ ይህ አዲስ የመማሪያ መጽሐፍ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡

ይህ የዘጠነኛ (፱) ክፍል መማሪያ መጽሐፍ በመርሀ ትምህርቱ ላይ ትኩረት የተሰጣቸውን ነገሮች ሙሉ በሙሉ እንዲያካትት ተደርጓል፡፡

ምንባቦቹና ማብራሪያዎቹ ግልጽና ሳቢ በሆነ መልኩ እንዲካተቱ ተደርገው የተዘጋጁ ናቸው፡፡

በመጨረሻም ለመጽሐፉ ዝግጅት ጽሁፎችን በመስጠት የተባበሩነንን እያመሰገንን ስለመጽሐፉ ከመምህራን ፣ ከተማሪዎች እና ከሌሎች አካላት የሚቀርበውን አስተያየት ለመቀበል ዝግጁ መሆናችንን እንገልጻለን፡፡

አማርኛ

(፱ኛ) ክፍል

# ምዕራፍ አንድ፦ ቋንቋ

**የምዕራፉ ዓላማዎች፦**

**ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፣**

- የተራዘሙ ንግግሮችን አዳምጣችሁ ምላሽ ትሰጣላችሁ።
- በውይይት ውስጥ በመሳተፍ ሀሳባችሁን ትገልጻላችሁ።
- የቃል ዘገባ ታቀርባላችሁ።
- የራሳችሁን ማስታወሻ በመጠቀም ጽሑፍ ትጽፋላችሁ።
- የምንባቡን ዋና ዋና ሃሳቦች ትጽፋላችሁ።
- አውድን በመጠቀም ለአንድ ቃል የተለያየ ትርጉም ትሰጣላችሁ።
- አረፍተነገሮችን ትመሰርታላችሁ።
- የተለያዩ የአረፍተ ነገር ዓይነቶችን ለተለያዩ ተግባራት (ለማተት፣ ለመጠየቅ፣ ለትዕዛዝ)ትጠቀማላችሁ።

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

## የቋንቋ ምንነትና ተግባራት

### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

፩. ተማሪዎች በጥንድ በመሆን ስለቋንቋ ምንነትና አገልግሎት ከተወያያችሁ በኋላ የተወያያችሁበትን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለጹ፡፡

፪. ተማሪዎች መምህራችሁ "የቋንቋ ምንነትና አገልግሎት" በሚል ርዕስ ምንባብ ያነቡላችኋል፡፡ ከርዕሱ በመነሳት የምንባቡ ይዘት ምን ሊሆን እንደሚችል ገምቱ፡፡

፫. የሚከተሉት ቃላት ከምታዳምጡት ምንባብ የተወሰዱ ናቸው፡፡ የቃላቱን ፍች ግለጹ፡፡

ሀ. ተራ ለ. ዘዬ ሐ. ነጸብራቅ መ. መስረጽ

### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

ሀ. ተማሪዎች እስካሁን ካዳመጣችሁት ምንባብ ምን ተገነዘባችሁ?

ለ. ቀጥሎ በምታዳምጡት የምንባቡ ክፍልስ ምን ምን ጉዳዮች የሚተረክ ይመስላችኋል?

### የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

፩. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መነሻነት በቃል መልስ ስጡ፡፡

ሀ. ቋንቋ ምንድን ነው?


ለ. ቋንቋ ከእንስሳት መግባቢያ በምን ይለያል?

ሐ. "ቋንቋ 'ተራ' ጩኸት ሳይሆን በስርዓት የተሰደሩ ድምጾች ስብስብ መሆኑ ነው፡፡" ሲል ምን ማለቱ ነው?

መ. ዋና ዋና የቋንቋ ተግባራት ምን ምን ናቸው?

ሠ. የምንባቡን አጠቃላይ መልዕክት ግለጹ፡፡

፪. ያዳመጣችሁትን ምንባብ መነሻ በማድረግ የቋንቋ ዋና ዋና ተግባራት ላይ ከተወያያችሁ በኋላ መልሳችሁን በሚከተለው ቻርት ላይ አስፍሩ፡፡




## ክፍል ኹለት፡- መናገር

፩. የዘገባ አቀራረብ መንገዶች ምን ምን እንደሆኑ በመወያየት መልሳችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለጹ፡፡

፪. የሰው ልጅ ቋንቋ ከእንስሳት መግባቢያ ጋር ያለውን ልዩነት በቡድን በመወያየት ዋና ዋና ነጥቦችን ለጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡ፡፡

**የውይይት ዝግጅትና አቀራረብ መመሪያ**

ውይይት ዓላማ ያለው በእቅድ የተዘጋጀና በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑ ርዕሰ-ጉዳዮች ዙሪያ ሀሳብ የሚለዋወጡበትና ከጋራ መግባባት ላይ የሚደርሱበት ተግባር ነው፡፡ ውይይት ራሱን የቻለ የዝግጅትና የአቀራረብ መመሪያ አለው፡፡ በውይይት ዝግጅት ወቅት ከሚከናወኑ ተግባራት ውስጥ ርዕሱን በሚገባ ማስተዋል፣ ርዕሱን በሚመለከት መረጃ መሰብሰብ፣ የተሰበሰቡት መረጃዎች ለተሳታፊዎች የሚመጥኑ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣ መረጃዎችን በቅደም ተከተል ማደራጀት፣ ወዘተ. የሚሉት ይገኙበታል፡፡

በውይይት አቀራረብ ወቅት ከሚከናወኑ ተግባራት ውስጥ ደግሞ የውይይት ዓላማንና ርዕስን ማስተዋወቅ፣ የውይይቱን ጭብጥ በቅደም ተከተል ለተደራሲያን ማቅረብ፣ ሀሳብን በተመጠነ ድምጽ ማቅረብ፣ በተሰጠው የጊዜ ገደብ መጠቀም፣ በውይይቱ መጨረሻ ተሳታፊዎችንና ታዳሚዎችን ማመስገን፣ ወዘተ. ይገኙበታል፡፡

## ክፍል ሦስት፡- ንባብ

# የቋንቋ መሠረታዊ ባህርያት

### ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች በእያንዳንዱ ቡድን (ከ3_5) በመሆን ከተወያያችሁ በኋላ መልሳችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለጹ፡፡

ሀ. የቋንቋዎች መሠረታዊ ባህርያት ምን ምን ሊሆኑ ይችላሉ?

ለ. የሰው ልጅ ቋንቋን የሚለምደው እንዴት ይመስላችኋል?

## የቋንቋ መሠረታዊ ባህርያት

ቋንቋ ማኅበራዊ የመግባቢያ መሳሪያ ነው፡፡ የሰዎች ማኅበራዊ ኑሮ ትርጉም ይኖረው ዘንድ ቋንቋ ያስፈልገዋል፡፡ የሰዎች ማኅበራዊነት ያለ ቋንቋ ሙሉ እንደማይሆን ሁሉ ቋንቋም ያለ ማኅበራዊነት ሙሉ አይሆንም፡፡ የቋንቋ ማኅበራዊነት ስንል፣ ቋንቋ ሰው ከመሰሉ ጋር የሚግባባበት መሆኑን ለማመልከት ብቻ ሳይሆን ቋንቋ “ሰው”የፈጠረው ከአካባቢው ጋር የሚለዋወጥ፣የሚወለድ፣ የሚያድግና የሚሞት፣ የሰው መለያ የሆነ ምድራዊ ውጤት መሆኑንም ለማመልከት ነው፡፡ በዚህ መሠረት ቋንቋ የሚለመድና የሚማሩት እንጂ የሚወለዱበት አይደለም፡፡

በዓለማችን ላይ የሚነገሩ ቋንቋዎችን ከሌሎች መግባቢያዎች በተለየ አኳኋን አንድ የሚያደርጓቸው ብዛት ያላቸው የጋራ ባህርያት አሏቸው፡፡ የቋንቋዎች መሠረታዊ ባህርያት በመባል የሚጠቀሱትም እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

ቋንቋ የማንኛውም ዕውቀት ማስተላለፊያ መሳሪያ ነው፡፡ ይህ የዕውቀት ማስተላለፊያና መቀበያ መሳሪያ ለሰብዓዊ ፍጡር ብቻ የሚያገለግል ከመሆኑ የተነሳ ቋንቋን ሰብዓዊ ነው ያሰኘዋል፡፡ ከሰው ልጅ በስተቀር ቋንቋ ያለው ሌላ ፍጡር የለም፡፡ በዚህም የተነሳ ቋንቋ ሰብዓዊ ባህሪ አለው ይባላል፡፡

በዓለማችን ላይ የሚገኙትን ቋንቋዎች ከሚያመሳስሏቸው ባህርያት ውስጥ

ዘፈቀዳዊነት ተጠቃሽ ነው፡፡ ቋንቋዎች የዘፈቀዳዊነት ባህሪ አላቸው የምንለውም የሰው ልጅ መጀመሪያ ቋንቋን መናገር ሲጀምር ከአንደበቱ የሚወጡ ድምጾችን አቀናጅቶ ለአንድ ነገር ወይም ሀሳብ ወኪል እንዲሆኑ ሲያደርግ ባጋጣሚ የተስማማበትን እንጂ ቃላቱ በውክልና ከቆሙለት ነገር ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት ላይ ተመስርቶ አይደለም፡፡ በአንድ ድምጽ ወይም በአንድ ቃልና ድምጹ ወይም ቃሉ በሚያመለክተው ወይም በሚሰይመው ነገር መካከል የባሕርይ ግንኙነት የለም፡፡ ምሳሌ "ዉሻ" የሚለው በዚህ ስያሜ ለምንጠራው እንስሳ ሥጋው አይደለም፡፡ "ዉሻ" በማለት ፈንታ "ላላ" ብንለው ዉሻነቱ አይለወጥም፤ ድመት ብንለውም ድመት አይሆንም፡፡ ለማንኛውም ነገር የሚሆን "ትክክል" የምንለው መጠሪያ ወይም " ተገቢ" የምንለው ስያሜ የለውም፡፡ እንዲያው በዘልማድ "ትክክል"ወይም "ተገቢ"የምንለው የቋንቋ ተናጋሪዎች ተስማምተው ያወጡለትን ነው፡፡ "ትክክለኛ "ወይም "ተገቢ" የሚሆነውም ለእነዚያ ተናጋሪዎች ብቻ ነው፡፡ እንደውም በዘመንም ይወሰናል ፡፡ ይህም ማለት በአንድ ዘመን ለነበረ ትውልድ በቋንቋው አንድ ቃል የነበረው ትርጉም ለሚከተለው ትውልድ ሌላ ትርጉም ሊኖረው ይችላል ፡፡ ስለዚህ ሕዝቡ ወይም ኅብረተሰቡ ሁኔታው እንደ ሚፈቅደው ና እንደ ሚያስገድደው ቃል ይፈጥራል ፤ ትርጉም ያሰፋል፤ ያጠባል፤ ይለውጣል፡፡

በዘፈቀደ የተፈጠሩት ትዕምርቶች ለተፈላጊው የማግባባት አገልግሎት ይውሉ ዘንድ ኅብረተሰቡ በይሁን (በስምምነት) ተቀብሎ የሚጠቀምበት የቋንቋ ሥርዓት አለው፡፡ ይህ የቋንቋ ባህርይ ከላይ ዘፈቀዳዊነት በሚል ከተነሳው ጋር ጎን ለጎን ሲታይ ግራ ያጋባ ይሆናል፡፡ ባንድ ወገን "በዘፈቀደ የተፈጠረ" ብለን በሌላ በኩል ደግሞ "ሥርዓት ያለው" ማለታችን የቀደመው ተከታዩን አያፈርሰውምን? ብለን ልንጠይቅ እንገደድ ይሆናል፡፡ ይህ የሚሆነው ቋንቋን ወይም ንግግርን በሁለንተናዊ መልኩ ማየት ትተን የተለያዩ ፀባዮቹን ሌጣ ሌጣቸውን የተመለከትናቸው እንደሆነ ነው፡፡ ይህ እንዳይሆን ቀደም ሲል "ቋንቋ ማኅበራዊ ነው" ያልነውን ሳንለቅ መናገር አለብን፡፡ ከሁሉም በፊት ይህን ፀባዩን መገንዘብ አለብን፡፡ ምንም እንኳ የተለያዩ ድምጾች፣ ብሎም ቃላት ከሚያመለክቱት ነገር፣ ሁኔታ፣ ወይም ጽንሰ-ሐሳብ ጋር ባህርያዊ ግንኙነት የላቸውም ብንልም፣ እነሱ ተሰብስበው ለተፈላጊው ሙያ በሚውሉበት ጊዜ አቀማመራቸው ስድ መሆኑ ቀርቶ ማኅበሩ "ይበጅ" ብሎ የተቀበለው ቅደም ተከተል አለ፡፡ ማኅበሩ በጊዜ ብዛት፣ በልማድ ሌላ ዓይነት ቀመር ወይም ስልት እስኪሰጠው አይለወጥም፡፡ ቋንቋ ሥርዓት አለው ስንል ወይም ሕግ አለው ስንል ይህንኑ እንጂ ዘላለማዊ

የሆነ ማለታችን አይደለም፡፡ ይህንን በምሳሌ መመልከት ይበጃል፡፡ መጀመሪያ በሥርዓተ ድምጹ በኩል ብናየው፣ “ረፈደ” የሚለውን ቃል እንውሰድና በውስጡ ያሉትን ድምጾች እንመልከት፡፡ ነገሩ በጣም ግራ እንዳያጋባን ልክ በአማርኛ እንደተጻፈው እንውሰደውና ረ-ፈ-ደ ጊዜው እንደማለፍ ብሏል፤ ፀሐይ ከፍ ብላለች፤ ወዘተ. ማለት ነው፡፡ ፊደላቱ ያሉበትን ቦታ ብንቀያይር “ደፈረ”ን፣ “ፈረደ”ን እናገኛለን፡፡ ፊደላቱ ወይም ትዕምርቶቹ አንዱ የሌላውን ስፍራ ሲወስድ ትርጉሙ ይለወጣል፡፡

የሰው ልጅ ቋንቋ ረቂቅ ነው፡፡ በረቂቅነቱም አማካይነት መልዕክት ማስተላለፉ ሌላው ጠባዩ ነው፡፡ በንግግር ወቅት መልዕክት የሚተላለፈው በድምጽ ነው፡፡ ድምጹ እና ድምጹ የሚወክለው ነገር ወይም ሁኔታ ግን የግድ አንድ ላይ ላይገኙ ይችላሉ፡፡ይህም ማለት አንድ ሰው አንድን ቃል ከወካዩ ግዑዝ ነገር፣ ሁኔታ ነጥሎ ጽንሰ-ሀሳቡን ብቻ በመቅረጽ ነገሩ ወይም ሁኔታው ከነበረበት የቦታና የጊዜ ክልል ውጪ ሊናገረው ይችላል፡፡ ለራሱ ሲነገረውም አድምጦ መረዳት አይቸግረውም፡፡ ለምሳሌ “ነብር” የሚለው ቃል አውሬው በሌለበት ቦታ እና ጊዜም ቢነገር ወይም ድምጹ ቢሰማ ነብሩ በሐሳባችን ይቀረጻል፡፡ ይህም መልዕክቱን በተለየና በላቀ ደረጃ የማስተላለፍ ባህርይው ቋንቋን ረቂቅ ነው ያሰኘዋል፡፡

### የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎች

ሀ. እስካሁን ካነበባችሁት ጽሑፍ ምን ተገነዘባችሁ?

ለ. የቋንቋ የሰብዓዊነት እና የሥርዓታዊነት ባህርይ ምንን ይገልጻሉ?

ሐ. ከዚህ በታች ባለው የምንባቡ ክፍል ምን ምን ሀሳቦች የሚቀርቡ ይመስላችኋል?

ለአንድ ለተወሰ ሕዝብ ቋንቋው በራሱ ምሉዕ ነው፡፡ የቋንቋው ተናጋሪ ማኅበረሰብ አካባቢውን ተገንዝቦ፣ የተገነዘበውን ለመሰሉ ለማስተላለፍ የሚያስችለው በቂ መድበለ ቃላት፣ ሙሉ የቋንቋ ሥርዓት አለው፡፡ የማወቅ ክበቡ በሰፋ ቁጥር ቋንቋውም ይሰፋል፡፡ የማያውቀውን አለመግለጹ ቋንቋውን ጎዶሎ ወይም ዝቅተኛ አያደርገውም፡፡ ሁሉም ቋንቋዎች የተናጋሪያቸውን ወግ፣ ልማድ ወይም ባህል በተሟላ አኳኋን ይገልጻሉ፡፡ በመሆኑም ሁሉም ቋንቋዎች ባህላቸውን በመግለጽ እኩል ናቸው፡፡ ትንሽ ቋንቋ ወይም ትልቅ ቋንቋ የሚባል ነገር የለውም፡፡ በዚህም

ሳቢያ ቋንቋዎች ሁሉ ለራሳቸው ባህል ምሉዕ በመሆን አንድ ዓይነት ባህርይን ይጋራሉ።

የተለያዩ ሕዝቦች በልዩ ልዩ ምክንያት ተገናኝተው ልዩ ልዩ የባህል ቅርሶችን መለዋወጣቸው የታወቀ ነው። ቋንቋዎችም እንደዚሁ ይለዋወጣሉ። በንግድ፣ በሃይማኖት፣ በቴክኖሎጂ፣ ወዘተ. ምክንያት አንዱ ቋንቋ ከሌላው ይገናኛል፤ ያለውን ያውሳል፤ የሌለውን ይዋሳል። ብዙውን ጊዜ ተጽዕኖው የበለጠ የሚታየው "ደካማ" በሆነው ኅብረተሰብ ቋንቋ ላይ ነው። ይህም ማለት በስልጣኔ ገፍተው፣ በባህል ዳብረው፣ በፖለቲካ ወይም በጦር ኃይል ልቀው የሚገኙ ሕዝቦች በተጠቀሱት የኑሮ መስኮች ዝቅ ያሉ ጎረቤቶቻቸውን መጫናቸው የማይቀር ነው። መወራረስ፣ መዋዋስ የቋንቋና የማኅበራዊ ኑሮ ሥርዓት የሚጠይቀው ግዴታ ነው። በዚህ አንጻር ስናየው አንድም ቋንቋ ራሱን ችሎ፣ ‹‹ንጽሕናውን ጠብቆ›› የዓለሙን ሁኔታ ሁሉ መግለጽ አይቻለውም።

አንድ ቋንቋ ከሌላው ቋንቋ ድምጽን፣ቃልን፣ አገላለጽን፣ ወዘተ ሊዋስ ይችላል። አንድ ቋንቋ በሌላው ላይ የሚያሳየው ተጽእኖ ጎልቶ የሚታየው በቃላት በኩል ነው። አንዳንድ የባህል ውጤቶች ና የኑሮ ዕሴቶች ከአንድ ማኅበረሰብ ወደ ሌላ በሚሸጋገሩበት ጊዜ ሁኔታዎቹን የሚገልጹት ቃላት አብረው መወረሳቸው ብዙ ጊዜ የሚሆን ነገር ነው። ዛሬ በጣም ሰልጥኖ በብዙ የዓለም ክፍል የሚሠራበት ቋንቋ እንግሊዝኛ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ቃላቱ ከልዩ ልዩ ቋንቋዎች የተወሰዱ ናቸው። አማርኛ ቋንቋም በሃይማኖት ሳቢያ እንደ /ጽ/፣/ጵ/ ያሉ ድምጾችንና እንደ ጳጳስ ያሉ ስሞችን ተውሷል። ውሰት የሁሉምቋንቋዎች የጋራ ባህሪ ነው።

አንድ ሰው የጠቅላላ አካላቱን ቅርጽና ዓይነት ከእናት ከአባቱ ወይም ከሥጋ ዘመዶቹ ይወርሳል። ቋንቋ መናገር የሚችለው ግን በመማርና በመለማመድ እንጂ በተፈጥሮ ከእናት ከአባት በመውረስ አይደለም። አንድ ህጻን ሲወለድ ይዞት የሚወለደው ቋንቋን ሳይሆን ቋንቋን ለመልመድ የሚያበቃውን ሰብዓዊ ችሎታ ነው። በሚያድግበት አካባቢ ካለው ማኅበረሰብ ጋራ በሚኖረው መስተጋብር ባካባቢው የሚነገረውን ቋንቋ በማዳመጥ በምላሹም ለመናገር በመሞከር ቋንቋን ይለምዳል። ከዚህ ባለፈም ትምህርት ቤት በመግባትና፣ ከሌሎች ቋንቋ ተናጋሪዎች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ሌላ ተጨማሪ ቋንቋ ሊማር ይችላል። ቋንቋ ሰዎች ከተወለዱ በኂላ የሚለምዱት ወይም የሚማሩት እንጂ በተፈጥሮ የሚያገኙት አይደለም።

ቋንቋ ይወለዳል፣ ያድጋል፣ ይሞታል። ይህ ሌላው የቋንቋ ጠባይ ነው። የአንድ ቋንቋ ዘዬዎች የተለያዩ ቋንቋዎች ከመሆን ደረጃ ሲደርሱ ቋንቋ ተወለደ ይባላል። የቋንቋው ተናጋሪ ኅብረተሰብ በሳይንስ፣ በቴክኖሎጂ፣ በባህልና በአኗኗር ስልቱ ሲያድግ፣ ዕውቀቱ ሲሰፋ ወይም ርዕዮተ ዓለሙ ሲለወጥ ቋንቋውም በዚያው መጠን አዳዲስ ቃላትን በመፍጠር፣ ያሉትንም ቃላት ትርጉም በማስፋትና ከሌሎች በመዋስ አብሮ እየተሻሻለ፣ እያደገና እየበለጸገ ሲመጣ ቋንቋ አደገ ይባላል። ቋንቋው ቀስ በቀስ ወደሌላ ቋንቋ ሲለወጥ፣ በሌላ ቋንቋ ሲዋጥ፣ ተናጋሪ ሲያጣ ደግሞ ቋንቋ ሞተ ይባላል።

በአጠቃላይ ከዚህ በላይ የተጠቀሱት በሁሉም ቋንቋዎች ላይ የሚታዩ የጋራ ባህርያት ናቸው። ሆኖም ግን እያንዳንዱ ቋንቋ የራሱ የሆኑ መለያ ባህርይ ያለው መሆኑ ሊዘነጋ የማይገባ ነው።

(ምንጭ፡- ዮሐንስ አድማሱ (1966)
"አማርኛ ለኮሌጅ ደረጃ" ከሚለው ተሻሽሎየተወሰደ)

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

፩. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ትክክል ለሆኑት "እውነት"፣ ስህተት ለሆኑት ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልሱ፤ ምክንያታችሁንም ግለጹ።

1. የቋንቋ ማኅበራዊነት የሰው ልጅ ቋንቋን ከመሰሉ ጋር ለተግባቦት አገልግሎት ብቻ የሚያውለው መሳሪያ መሆኑን ያመለክታል።
2. ማንኛውም ቋንቋ በራሱ ምሉዕ ነው።
3. በአንድ ቃል እና ቃሉ በሚወክለው አካል መካከል ያለው ግንኙነት ተፈጥሯዊ ነው።
4. ንግድ፣ ሃይማኖት፣ ቴክኖሎጂ በቋንቋዎች መካከል ለሚካሄደው ውሰት በምክንያትነት ይጠቀሳሉ።
5. የቋንቋ የዘፈቀዳዊነት ባህርይ ከቋንቋ የሥርዓታዊነት ባህርይ ጋር ይቃረናል።

፪. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ተገቢውን መልስ በቃል ግለጹ፡፡

ሀ. ከቋንቋዎች መሠታዊ ባህርያት ቢያንስ ሁለቱን ጥቀሱ፡፡

ለ. በምንባቡ ሁለተኛ አንቀጽ "... ቋንቋዎችን ከሌሎች መግባቢያዎች ..." የሚለው ሐረግ ምንን ያመለክታል? ከቋንቋ ውጭ የሆኑት ሌሎች መግባቢያዎች ምን ምን ሊሆኑ ይችላሉ?

ሐ. "... ቋንቋ የሚለመድ፣ የሚማሩት እንጂ የሚወለዱበት አይደልም፡፡ " ሲል ምን ማለቱ ነው?

መ. "ቋንቋ ዘፈቀዳዊ ነው" የሚለውን አገላለጽ አብራሩ፡፡

ሠ. አንድ ቋንቋ ከሌላ ቋንቋ ምን ምን ነገሮችን ሊዋስ ይችላል?

ረ. ቋንቋ ሞተ የሚባለው ምን ሲሆን ነው?

፫. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ተገቢውን መልስ ምረጡ፡፡

1. "የሰው ልጅ ድምጾችን ወይም ቃላትን ለአንድ ነገር ወኪል እንዲሆኑ የሚሰይማቸው በውክልና ከቆሙለት ነገር ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት ላይ ተመስርቶ አይደለም፡፡" የሚለው አገላለጽ ከቋንቋ ባህርያት ውስጥ የትኛውን ያመለክታል?

   ሀ. ሰብዓዊነቱን ለ. ሥርዓታዊነቱን

   ሐ. ዘፈቀዳዊነቱን መ. ረቂቅነቱን

2. ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ የቋንቋ የተዋዋሽነት ባህርይን አስመልክቶ ትክክል የሆነው የቱ ነው?

   ሀ. ለቋንቋ መጥፋት ምክንያት መሆኑን ያመለክታል፡፡

   ለ. አንድ ቋንቋ በራሱ ምሉዕ አለመሆኑን ያሳያል፡፡

   ሐ. የኅብረተሰቡ ቋንቋ ደካማ መሆኑን ያመለክታል፡፡

   መ. ቋንቋው ሙሉ በሙሉ ራሱን አለመቻሉን ያመለክታል፡፡

3. አንድ ህጻን አንድን ቋንቋ መናገር የሚለምደው፡-

ሀ. ከአካባቢው ለ. ከተፈጥሮ በማግኘት

ሐ. ከአያቶቹ በውርስ መ. ከትምህርት ቤት በመማር

4. በምንባቡ መሠረት ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ ትክክል የሆነው የቱ ነው?

ሀ. በስምና በተሰያሚ መካከል ተፈጥሯዊ ግንኙነት አለ፡፡

ለ. ማንኛውም ነገር ፍጹም ተገቢ የሆነ መጠሪያ የለውም፡፡

ሐ. ማንኛውም ሰው ባሻው ጊዜ የቋንቋ ሥርዓት መቀየር ይችላል፡፡

መ. ማንኛውም ፍጡር የሚግባባው በቋንቋ አማካይነት ነው፡፡

5. ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ ለቋንቋ ማደግ በምክንያትነት ሊጠቀስ የሚችለውን ነገር የሚያመለክተው የትኛው ነው?

ሀ. የቋንቋው ተናጋሪ ማኅበረሰብ በቴክኖሎጂ መበልጸግ

ለ. የቋንቋው ተናጋሪ ርዕዮተ ዓለም መለወጥ

ሐ. የቋንቋው ተናጋሪ ማኅበረሰብ ዕውቀት መስፋት

መ. ሁሉም መልስ ይሆናሉ

፬. በምንባቡ ውስጥ የተጠቀሱትን ዋና ዋና ነጥቦች ለይታችሁ ጻፉ፡፡

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

፩. በምንባቡ ውስጥ ከቀረቡት የቋንቋ መሠረታዊ ባህርያት ውስጥ አንዱን በመውሰድ በራሳችሁ አገላለጽ በአንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡

፪."የቋንቋ መሠረታዊ ባህርያት" የሚለውን ምንባብ መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ዝርዝር ጉዳዮች መነሻ በማድረግ አጭር ጽሁፍ ጻፉ፡፡

ሀ. የምትማሩትን የቋንቋ ዓይነት ግለጹ፡፡

ለ. የምትማሩትን ቋንቋ ከቋንቋ ባህርያት አኳያ የሚታይበትን ባህሪ ዘርዝሩ፡፡

ሐ. የዘረዘራችሁትን የቋንቋ ባህሪ መነሻ በማድረግ አንድ የተሟላ ጽሑፍ ጻፉ፡፡

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

፩. በሚከተሉት ጥንድ ጥንድ ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ቃላት ዐውዳዊ ፍች ግለጹ፡፡

ምሳሌ፡-

ሀ. ኢትዮጵያ ሀገራችን ለችግሮቿ ቋሚ መፍትሄ አገኘች፡፡ (ዐውዳዊ ፍች - ዘላቂ)

ለ. እሷ ለወንድሟ ሰርግ ቋሚ ነበረች፡፡ (ዐውዳዊ ፍች - አሳላፊ፣ አስተናጋጅ)

1. ሀ. የምንጭ ውሃን ለመጠጥ ከመጠቀማችን በፊት ማጣራት ያስፈልጋል፡፡

   ለ. አንድ ነጋዴ አዳዲስ ምርቶችን ወደ መጋዘን ከማስገባቱ በፊት የነበሩትን ማጣራት አለበት፡፡

2. ሀ. የሀገር ሽማግሌዎች ያቀረቡት የሰላም ጥሪ ድጋፍ አገኘ፡፡

   ለ. ልጁ የቤተሰቡን ድጋፍ ፈለገ፡፡

3. ሀ. ወጣቱ ትውልድ ከድህነት ለመውጣት እና ሀገሩን ለማልማት በጋራ ተነሳ፡፡

   ለ. ተማሪው ለፈተና ዝግጅት በለሊት ከእንቅልፉ ተነሳ፡፡

4. ሀ. መሐንዲሱ ለህንጻው ሥራ የሚያስፈልገውን በቂ ገንዘብ መደበ፡፡

   ለ. የሥጋ ቤቱ ባለሙያ ሥጋውን ባይነት ባይነቱ መደበ፡፡

5. ሀ. በጣለው ኃይለኛ ዝናብ ምክንያት ወንዙ ደፈረሰ፡፡

   ለ. ጓደኛዬ ለሊቱን ሙሉ ሲያጠና በማደሩ ዓይኑ ደፈረሰ፡፡

፪. ከዚህ በታች ለቀረቡት ቃላት በምሳሌው መሰረት ሊያስገኙ የሚችሉትን የተለያየ ዐውዳዊ ፍቺ የሚያመለክቱ ዓረፍተ ነገሮች ከጻፋችሁ በኋላ ዐውዳዊ ፍቻቸውን ግለጹ፡፡

ምሳሌ፡-

ቃል ---- ቆረጠ

ዐረፍተ ነገር 1. የሂሳብ ባለሙያዋ ከሠራተኞች ደሞዝ ላይ የጡረታ ተቀማጭ ገንዘብ ቆረጠች፡፡

ዐውዳዊ ፍች፡ ቀነሰች (ቀንሳ ወሰደች)

ዐረፍተ ነገር 2. ፀጉር አስተካካዩ የደንበኛውን ፀጉር ቆረጠ፡፡

ዐውዳዊ ፍች፡ አሳጠረ፣ አስተካከለ፣ ከረከመ

ዐረፍተ ነገር 3. ተማሪዋ በፈተና ጥሩ ውጤት ለማምጣት ቆረጠች፡፡

ዐውዳዊ ፍች፡ ወሰነች

1. መዋል

2. ምንጭ

3. ሳለ

4. ቀሸረ

5. በራሪ

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

### የዓረፍተ ነገር አይነቶች

ዓረፍተ ነገር በስርዓት ተቀነበባብሮ ሙሉ ሀሳብን ማስተላለፍ የሚችል የቃላት ወይም የሀረጎች ስብስብ ነው፡፡ ዓረፍተ ነገርን የሚያስገኙት መሰረታዊ ተዋቃሪዎች ስማዊ ሀረግ እና ግሳዊ ሀረግ ናቸው፡፡ እነዚህ ተዋቃሪዎች በሁሉም ረገድ የተስማሙ ሆነው መገኘት አለባቸው፡፡

በዓረፍተ ነገሩ ውስጥ የገቡት ሀረጎች ከሚይዟቸው የግስ ብዛት አንጻር ነጠላ እና ውስብስብ ዓረፍተ ነገር ተብለው በሁለት ይከፈላሉ፡፡

ነጠላ ዓረፍተ ነገር፡ በውስጡ አንድ ግስን የሚይዝ፣ ከአንድ ነጠላ ስማዊ ሀረግና ከአንድ ነጠላ ግሳዊ ሀረግ የሚመሰረት የዓረፍተ ነገር ዓይነት ነው፡፡

ምሳሌ፡- አውሮፕላኑ በሰዓቱ ደረሰ፡፡

ስማዊ ሀረግ፡- አውሮፕላኑ

ግሳዊ ሀረግ፡- በሰዓቱ ደረሰ

በምሳሌው ላይ እንደሚታየው “አውሮፕላኑ” ነጠላ ስማዊ ሀረግ፣ “በሰዓቱ ደረሰ” ነጠላ ግሳዊ ሀረግ በመሆናቸው የተነሳ ዓረፍተ ነገሩን ነጠላ ያሰኘዋል፡፡ በዓረፍተ ነገሩ ውስጥም የሚገኘው የግስ ብዛት አንድ ብቻ ነው፡፡

ውስብስብ ዓረፍተ ነገር ከአንድ በላይ ግሶችን የሚይዝ ወይም በውስጡ ሌላ ያላሰረ ዓረፍተ ነገርን የሚይዝ የዓረፍተ ነገር ዓይነት ነው፡፡

ምሳሌ፡ ትላንት የተሸለሙት ተማሪዎች ስለተደሰቱ ወደመዝናኛ ቦታ ሄዱ፡፡

ስማዊ ሀረግ፡- ትላንት የተሸለሙት ተማሪዎች

ግሳዊ ሀረግ፡- ስለተደሰቱ ወደመዝናኛ ቦታ ሄዱ

በምሳሌው ላይ የሚገኘው ስማዊ ሀረግ በውስጡ “ትናንት የተሸለሙት” የሚለውን ያሳሰረ ዓረፍተ ነገር ይዟል፡፡ ግሳዊ ሀረጉም “ስለተደሰቱ” የሚለውን ጥገኛ ዓረፍተ ነገር ይዟል፡፡ በዚህም ምክንያት በዓረፍተ ነገሩ ውስጥ ሦስት ግሶች በመገኘታቸው ዓረፍተ ነገሩን ውስብስብ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

፩. ከዚህ በታች የቀረቡትን ዓረፍተ ነገሮች ነጠላ እና ውስብስብ ዓረፍተ ነገር በማለት ለዩ፤ ምክንያታችሁንም ግለጹ፡፡

ሀ. ሀገር መከበሪያ ናት፡፡

ለ. ወርኃዊ ገቢው ስለጨመረ የቤተሰቡ ኑሮ ተሻሻለ፡፡

ሐ. ሰዎች ለሁላችንም በአንድ ወይም በሌላ መንገድ አንድ ውለታ ውለውልናል፡፡

መ. የሥራ ፍቅር ያለው የትም ቢቆፍር ወርቅ ያገኛል፡፡

ሠ. ሰዓቱ ስለደረሰ ወደየቤታችን እንሂድ፡፡

፪. ከዚህ በታች በቀረበው ጽሑፍ ውስጥ የሚገኙትን ነጠላ እና ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮች ለይታችሁ አውጡ፡፡

አንድ ገበሬ በጣም የሚወደው ፈረስ ነበረው፡፡ ፈረሱ ገበሬውን ለብዙ ዓመታት ያገለገለው ሲሆን ለቤተሰቡ ዋናው መተዳደሪያቸው ነበር፡፡ አንድ ቀን ፈረሱ ሜዳ ላይ ሳር እየጋጠ ሳያስበው የውሃ ጉድጓድ ውስጥ ወደቀ፡፡ ከጉድጓዱ ለመውጣት ብዙ ታገለ፤ ግን ደግሞ መውጣት አልቻለም፡፡ ትንሽ ቆይቶ ፈረሱ ውሃው ጉድጓድ ውስጥ መውደቁን ገበሬው ሰምቶ በከፍተኛ ሀዘን ውስጥ ሆኖ ወደ ጉድጓዱ ቀረበ፡፡ ከጉድጓዱ ጫፍ ቆሞ በጭንቀት ሲያየው ፈረሱ ቀና ብሎ ተመለከተ፡፡ ፈረሱ የገበሬውን ማዘን ሲያይ ከጉድጓዱ ሊያወጣው እንደሚችል ተስፋ አደረገ፡፡ …

፫. ከላይ የቀረበውን ማስታወሻ መሰረት በማድረግ ሦስት ነጠላ ዓረፍተ ነገር እና ሦስት ውስብስብ ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡

ነጠላ ዓረፍተ ነገር

ሀ. ________________________________

ለ. ________________________________

ሐ. ________________________________

ውስብስብ ዓረፍተ ነገር

ሀ. ________________________________

ለ. ________________________________

ሐ. ________________________________

## የዓረፍተ ነገር ስልቶች

ዓረፍተ ነገሮች በተነገሩበት ስልት መሠረት ከሚኖራቸው ተግባራት አንጻር ሐተታዊ ወይም አታች፣ መጠይቃዊ እና ትእዛዛዊ ተብለው ሊከፈሉ ይችላሉ፡፡

1. ሐተታዊ ዓረፍተ ነገር፡- ስለአንድ ድርጊት ወይም ሁነት አውንታዊ ወይም አሉታዊ የሆነ አስተያየት የሚሰጥ የዓረፍተ ነገር ዓይነት ነው፡፡ እያንዳንዱን በተናጠል እንደሚከተለው ማየት ይቻላል፡፡

1.1. አወንታዊ ዓረፍተ ነገር፡- አንድ ድርጊት በተወሰነ ቦታ እና ጊዜ፣ በተወሰነ ምክንያት የተፈጸመ ወይም የተከሰተ መሆኑን ያትታል፤ ይገልጻል፡፡

ምሳሌ፡-የከተማው ነዋሪ በነቂስ ወጥቶ አካባቢውን አጸዳ፡፡

1.2. አሉታዊ ዓረፍተ ነገር፡- የአዎንታዊ ዓረፍተ ነገር ተቃራኒ ነው፡፡ ይህም ማለት በአወንታዊ መንገድ የቀረበን ሀሳብ የሚያፈርስ ወይም የሚቃረን ዓረፍተ ነገር ነው፡፡

ምሳሌ፡-

የከተማው ነዋሪ በነቂስ ወጥቶ አካባቢውን አላጸዳም፡፡

2. መጠይቃዊ ዓረፍተ ነገር፡- በአንድ ሀተታዊ ዓረፍተ ነገር ስለተገለጸ ድርጊት ወይም ሁነት ጥያቄ የሚሰነዝር የዓረፍተ ነገር ዓይነት ነው፡፡ የሚሰነዘረው ጥያቄ በሁለት ዓይነት መልኩ ሊሆን ይችላል፡፡ አንደኛው ያልታወቀ ነገርን ለማወቅ፣ ሁለተኛው ደግሞ የታወቀ ነገርን ለማረጋገጥ ሲፈለግ የሚቀርብ ጥያቄ ነው፡፡

ምሳሌ፡-

ሀ. ማን አካባቢውን አጸዳ? (ያልታወቀ ነገርን ለማወቅ)

ለ.የከተማው ነዋሪ በነቂስ ወጥቶ አካባቢውን አጸዳ እንዴ? (የታወቀ ነገርን ለማረጋገጥ)

መጠይቃዊ ዓረፍተ ነገር ለመመስረት ብዙ ጊዜ ለምን፣ ምን፣ መቼ፣ የት፣ ወዘተ. ያሉት ቃላት ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡ ይሁንና አንዳንድ ጊዜ ግን እነዚህ ቃላት ሳይኖሩ ዓረፍተ ነገሩ መጠይቃዊ ይሆናል፡፡ ስለዚህ ለመጠይቃዊነት ስልት የመጠየቂያ ቃላት ቢኖሩም፣ ለጥያቄያዊ ዓረፍተ ነገር ዋናው አስፈላጊ ነገር የድምጽ ቅላጼ ወይም ቃና ነው፡፡

ምሳሌ፡-ሀ.የቤት ሥራችሁን ለምን አልሠራችሁም? (መጠይቃዊ ቃልን በመጠቀም)

ለ.የቤት ሥራችንሁን ሠራችሁ? (ያለ መጠይቃዊ ቃል)

3. ትዕዛዛዊ ዓረፍተ ነገር፡- አንድ ሰው አንድ ተግባር እንዲፈጽም ሲፈለግ ትዕዛዝ የሚሰጥበት የዓረፍተ ነገር ስልት ነው፡፡ ይህ ዓረፍተ ነገር በሁለት ዓይነት መንገድ ሊቀርብ ይችላል፡፡ አንደኛው ቀጥተኛ (ርቱዕ) ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ ኢቀጥተኛ (ኢርቱዕ) አቀራረብ ነው፡፡ ቀጥተኛ ትዕዛዛዊ ዓረፍተ ነገር የሚነገረው ድርጊቱን እንዲፈጽም ለሚፈለገውና በሁለተኛ መደብ ተውላጠ ስም ለተገለጸው ወይም ለተወከለው አካል ነው፡፡ ኢቀጥተኛ ትዕዛዛዊ ዓረፍተነገር ትዕዛዙ በቀጥታ ለፈጻሚው ሰው ወይም አካል የሚነገር ሳይሆን ትዕዛዙ የሚተላለፈው በሦስተኛ ወገን አማካይነት ነው፡፡

ምሳሌ ሀ.ወደክፍል ግቡ (ቀጥተኛ ትዕዛዛዊ ዓረፍተ ነገር)

ለ.ወደክፍል ይግቡ (ኢቀጥተኛ ትዕዛዛዊ ዓረፍተ ነገር)

ለቀጥተኛውም ሆነ ለኢቀጥተኛው ትዕዛዛዊ ዓረፍተ ነገር የድምጽ ቅላጼ ከፍተኛ ድርሻ አለው፡፡

(ምንጭ፡- ባየ ይማም (2010) አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው)

፩. ከዚህ በታች የቀረቡትን የዓረፍተ ነገሮች ስልት ለዩ፤ምክንያታችሁንም ግለጹ፡፡

1. የመኪናውን ፍጥነት ቀንሺ፡፡
2. የህዳሴው ግድብ የውሃ ሙሌት ደረጃ በደረጃ ተጠናቀቀ፡፡
3. የተዋስከውን መጽሐፍ መልስ፡፡
4. ትልቅ ሥራ ለመስራት ዕድሜ አይገድበውም፡፡
5. የስኬት መሰረት የሆነው ምንድን ነው?

፪. በሚከተለው ሠንጠረዥ በተ.ቁ 1 ላይ በቀረበው መሠረት የተጓደሉትን የዓረፍተ ነገሮች ስልት አሟልታችሁ ጻፉ፡፡

፫. ከላይ የቀረበውን ማስታወሻ መሰረት በማድረግለእያንዳንዳቸው የዓረፍተ ነገር ስልት ዓይነቶች ሦስት ሦስት ዓረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡

ሐተታዊ ዓረፍተ ነገር

ሀ. ______________________________

ለ. ______________________________

ሐ. ______________________________

መጠይቃዊ ዓረፍተ ነገር

ሀ. ______________________________

ለ. ______________________________

ሐ. ______________________________

ትእዛዛዊ ዓረፍተ ነገር

ሀ. ______________________________

ለ. ______________________________

ሐ. ______________________________

፫. በሚከተለው ሠንጠረዥ በተ.ቁ. 1 ላይ በቀረበው መሠረት የተጓደሉትን የዓረፍተ ነገሮች ስልት አሟልታችሁ ጻፉ፡፡

| ተ.ቁ | ሐተታዊ ዓረፍተ ነገር | መጠይቃዊ ዓረፍተ ነገር | ትዕዛዛዊ ዓረፍተ ነገር |
|---|---|---|---|
| 1 | በሕክምና ሙያ ሰለጠኑ፡፡ | በምን ሙያ ሰለጠኑ? | በሕክምና ሙያ ይሰልጥኑ፡፡ |
| 2 | | ትምህርት ቤቱ መቼ ተዘጋ? | |
| 3 | | | ሁሌም ፈተና ስለሚኖር ተዘጋጅታችሁ ጠብቁ፡፡ |
| 4 | ሥራ አስኪያጁ ወደ አዳራሹ ገቡ፡፡ | | |
| 5 | | | በቂ መረጃ ሳይኖራችሁ አስተያየት ከመስጠት ተቆጠቡ፡፡ |
| 6 | ጊዜያችሁን በአግባቡ ተጠቅማችኋል፡፡ | | |

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በምዕራፍ አንድ የቋንቋ ምንነትና ተግባራትን በማዳመጥ ክፍል ውስጥ ተምራችኋል። በክፍል ኹለትም ዘገባ በቃልና በጽሑፍ ሊቀርብ እንደሚችል ተምራችኋል። በክፍል ሦስት የቋንቋ መሠረታዊ ባህርያትን ተምራችኋል። በምንባብ መሠረትም ቋንቋዎች በዘፈቀዳዊነት፣ በሥርዓታዊነት፣ በምሉዕነት፣ ወዘተ. ባህርያት ሊመሳሰሉ እንደሚችሉ አንብባችኋል።

ቃላት በዓረፍተ ነገር ውስጥ የሚሰጡት ፍች ዐውዳዊ ፍች ተብሎ ይጠራል። የቃላትን ዐውዳዊ ፍች በሚመለከት በክፍል አምስት በቀረበላችሁ መልመጃ አማካይነት ተለማምዳችኋል። በሰዋስው ክፍል የዓረፍተ ነገር ዓይነቶችን ና ስልቶችን በሚመለከት ተምራችኋል። በዚህም ውስጥ በዓረፍተ ነገሩ ውስጥ የሚገኘውን የግስ ብዛት (መጠን) መሠረት በማድረግ ነጠላ እና ውስብስብ ተብለው ሊከፈሉ እንደሚችሉ ተምራችኋል። ዓረፍተ ነገሮች ከሚኖራቸው ተግባር አንፃርም ሐተታዊ፣ መጠይቃዊ እና ትዕዛዛዊ ተብለው ሊከፈሉ እንደሚችሉ ተመልክታችኋል።

## የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

1. የቋንቋን ምንነትና አገልግሎት ግለጹ።
2. ከቋንቋዎች መሠረታዊ ባህርያት ውስጥ ሦስቱን በመጥቀስ አብራሩ።
3. ሁለት ቃላትን በመጠቀም ዐውዳዊ ፍቻቸውን በዓረፍተ ነገር ውስጥ አመልክቱ።
4. የዓረፍተ ነገር ዓይነቶችን በምሳሌ አብራሩ።
5. ለተለያዩ አገልግሎቶች የምንጠቀምባቸውን የዓረፍተ ነገር ስልቶችን የሚያመለክቱ ዓረፍተ ነገሮችን ጻፉ።

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ አንድ የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ቅጽ ቀርቦላችኋል፡፡ በዚህም መሠረት በእያንዳንዱ ማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ቅጹን አሟሉ፡፡

| | የማመሳከሪያ ነጥቦች | √ | ? | X |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የተነበበውን ምንባብ አድምጬ ተረድቻለሁ | | | |
| 2 | የቋንቋን ምንነትና ተግባራት ተረድቻለሁ | | | |
| 3 | የዘገባን አቀራረብ መንገዶች መግለጽ ችያለሁ | | | |
| 4 | የቀረበውን ምንባብ አንብቤ ተረድቻለሁ | | | |
| 5 | የቋንቋን መሠረታዊ ባህርያት መዘርዘር ችያለሁ | | | |
| 6 | ለቃላት ዐውዳዊ ፍች መስጠት ችያለሁ | | | |
| 7 | የዓረፍተ ነገር ዓይነቶችን መለየት ችያለሁ | | | |
| 8 | የዓረፍተ ነገር ስልቶችን መመስረት ችያለሁ | | | |

፪. ከዚህ በላይ በቀረበው ቅጽ የ(?) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትገነዘቡ ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

አማርኛ

(፱ኛ) ክፍል

## ምዕራፍ ኹለት፡- ግብር

### የምዕራፉ ዓላማዎች፡-

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፣

- አዳምጣችሁ ጠቃሚና እምብዛም ጠቃሚ ያልሆኑ መረጃዎችን ትለያላችሁ
- ሀሳባችሁን በራስ መተማመን ትገልጻላችሁ።
- ከፅሑፉ ውስጥ ጠቃሚ መልዕክትን አንብባችሁ ትመዝናላችሁ።
- መረጃዎችን ትተረጉማላችሁ።
- የፊደል አሰዳደርን ለማወቅ መዝገበ ቃላትን ትጠቀማላችሁ።
- አንቀጽ ትጽፋላችሁ።
- የተለያዩ የጊዜ አመልካች ግሶችን ለንግግርና ለጽሕፈት ትጠቀማላችሁ።

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

# የግብር ጠቀሜታ እና አጀማመር

### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

፩. በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ጥንድ ጥንድ በመሆን ተወያዩባቸው፣ የውይይታችሁንም ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ።

ሀ. ግብር ምንድን ነው?

ለ. ግብር መክፈል ለምን ይጠቅማል?

፪. ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ፍች ስጡ።

ሀ. ግብር ለ. ማነቃቃት ሐ. መገባደጃ መ. አዋጅ

### የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

፩. ግብር መክፈል የተጀመረው መቼ ነው?

፪. ለዘመናዊ የግብር ሥርዓት ብቅ ብቅ ማለት በግንባር ቀደምትነት የምትጠቀሰው አገር ማን ናት?

፫. በኢትዮጵያ ግብር መክፈል የተጀመረው መቼ ይመስላችኋል?

### የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

፩. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት ትክክል ለሆኑት "እውነት"፣ ስህተት ለሆኑት ደግሞ "ሐሰት" በማለት በጽሁፍ መልሱ።

1. ግብር በውዴታና በግዴታ ለመንግስት የሚከፈል መዋጮ ነው።

2. የታዳጊ ሃገር ዜጎች ግብር መክፈል አይጠበቅባቸውም፡፡
3. ግብር መክፈል ከመንግስት መቋቋም ጋር እንደተጀመረ ይታመናል፡፡
4. በኢትዮጵያ ዘመናዊ የግብር ሥርዓት የተጀመረው በአፄ ኃይለስላሴ ዘመነ-መንግሥት ነው፡፡
5. በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የግብር አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ የወጣው እ.ኤ.አ በ1942 ዓ.ም ነው፡፡

፪. ከዚህ በታች ለቀረቡትን ጥያቄዎች ያዳመጣችሁትን ምንባብ መሠረት በማድረግ ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልሱ፡፡

1. ግብር መክፈል ለአንድ ሀገር ያለው ጠቀሜታ ምንድን ነው?

ሀ. ኢንቨስትመንትን ያበረታታል

ለ. ማህበራዊ አገልግሎትን ለማስፋፋት ያስችላል

ሐ.. የህዝቡን ኑሮ ለማሻሻል ያስችላል

መ. ሁለም መልሶች ናቸው

2. በጥንታውያን ግሪክ፣ ሮማ፣ ፐርሺያና ግብፅ ይከፈሉ ከነበሩት የግብር ዓይነቶች ውስጥ የማይካተተው የትኛው ነዉ?

ሀ. ጥንታዊ ሳንቲሞች ለ. የከበሩ ማዕድናት

ሐ. የጋማ ከብቶች መ. ልጆቻቸው

3. በኢትዮጵያ በቀደሙት ጥንታዊ ዘመናት ግብር መክፈል እንደተጀመረ በማስረጃነት የሚቀርበው ምንድን ነው?

ሀ. ጥንታዊ የድንጋይ ላይ ጽሑፎች

ለ. የአፄ ዘርዓያቆብ የታሪክ ድርሳናት

ሐ. የዋሻ ላይ ስዕሎች

መ. በነጋሪት ጋዜጣ ላይ ታትመው የወጡ አዋጆች

3. በአፄ ምኒልክ ዘመነ-መንግሥት አርሶ አደሩ ከአመረተው ምርት ግብር የሚከፍለው ምን ያህሉን ነው?

ሀ. ሩቡን ለ. አንድ አምስተኛውን

ሐ. አንድ አስረኛውን መ. ሲሶውን

4. በሀገራችን የቴምብር ቀረጥና የስራ ላይ ግብር የዋለው በስንተኛው ክፍለ ዘመን ነው?

ሀ. በ15ኛው ለ. በ18ኛው

ሐ. በ19ኛው መ. በ20ኛው

፫. ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት ለርዕሱ ጠቃሚና እምብዛም ጠቃሚ ያልሆኑ ሀሳቦችን በመለየት ቀጥሎ በቀረበው ሰንጠረዥ ላይ አስፍሩ።

| ጠቃሚ የሆኑ ሀሳቦች | እምብዛም ጠቃሚ ያልሆኑ ሀሳቦች |
|---|---|
| | |
| | |
| | |
| | |
| | |

## ክፍል ኹለት፦ መናገር

፩. ግብርን በሚመለከት ከመገናኛ ብዙኃን (ከሬዲዮ፣ ከቴሌቪዥን፣ ወዘተ.) ወይም ከተለያዩ ጽሑፎች ያነበባችሁትን መረጃ መነሻ በማድረግ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃላዊ ዘገባ አቅርቡ።

፪. ግብርን በሚመለከት ከገቢዎች ቢሮ መረጃዎችን በመሰብሰብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ቃላዊ ዘገባን በመጠቀም አቅርቡ።

፫. በቡድን በመሆን ከዚህ በታች ከቀረቡት ርዕሶች አንዱን በመምረጥ የክርክር አቀራረብ ሂደትን በመከተል ክርክር አካሂዱ፡፡

ሀ. በግብር መክፈል ጥቅምና ጉዳት ላይ ክርክር አድርጉ፡፡

ለ. ግብር ከፋዮች በአግባቡ ግብር ቢከፍሉ ተጠቃሚ የሚሆነው ኅብረተሰብ ነው ወይስ ግለሰብ፡፡

የክርክር ዝግጅትና አቀራረብ መመሪያ

ክርክር በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ ሁለት ተቃራኒ አመለካከት ባላቸው ሰዎች ወይም ቡድኖች መካከል ለማሸነፍ፣ ተናግሮ ለማሳመን የሚካሄድ ሥርዓታዊ ሙግት ነው፡፡ በሙግቱ ሂደትም የተሟጋቾችን (የተከራካሪዎቹን) ሀሳብ መዝነው ፍርድ የሚሰጡ ዳኞች ይኖራሉ፡፡ ለክርክሩም ሁለቱ ተቃራኒ ዕይታ ያላቸው ወገኖች በቂ ዝግጅት ማድረግና የክርክር አቀራረብ ስልትን ማወቅ፣ መከተል ይኖርባቸዋል፡፡

ተከራካሪ ወገኖች በክርክር የቅድመ ዝግጅት ወቅት ማከናወን ከሚገባቸው ነገሮች ውስጥ በርዕሱ ዙሪያ ከመረጃ ምንጮች መረጃዎችን ማሰባሰብ፣ ከተሰበሰቡት መረጃዎች ውስጥ ለክርክሩ ጠቃሚ የሆኑትን መምረጥና በቅደም ተከተል ማደረጀት፣ ልምምድ ማድረግ፣ ወዘተ. ይጠቀሳሉ፡፡

ተከራካሪ ወገኖች ክርክር በሚያቀርቡበት ወቅት ደግሞ በመደገፍ ወይም በመቃወም የሚከራከሩበትን የክርክር ርዕስ ለአድማጭ ማስተዋወቅ፣ በልበ ሙሉነት የመከራከሪያ ሀሳቦችን በመረጃ በማስደገፍ በቅደም ተከተል ማቅረብ፣ ሀሳብን በተገቢው የአካል እንቅስቃሴ ማቅረብ፣ በተቃዋሚዎች የሚነሱትን ሀሳቦች በትክክል መመዝገብና የመቃወሚያ ሀሳብን ማዘጋጀት፣ ለክርክሩ የተሰጠን ጊዜ በአግባቡ መጠቀም፣ ሲጨርሱ በምስጋና ማጠቃለል፣ ውጤትን በፀጋ መቀበል፣ ወዘተ፣ ይጠቀሳሉ፡፡

## ክፍል ሦስት፡- ንባብ

# ግብር እና አይነቶቹ

### ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

ከዚህ በታች በቀረቡት የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ላይ በቡድን በመሆን ከተወያያችሁ በኋላ መልሳችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

፩. የአንድ ሀገር ዜጎች ግብር የሚከፍሉት ለምን ይመስላችኋል?

፪. ነጋዴዎች ግብር ባይከፍሉ ምን የሚገጥማቸው ይመስላችኋል?

፫. የምታውቋቸውን የግብር ዓይነቶች ዘርዝሩ፡፡

ግብር የግዴታ መዋጮ ነው፡፡ መንግስታዊ ገቢን የማመንጨት ሕጋዊ ስልጣን ለረዥም ዘመናት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ከመሆኑ ጋር በተያያዘ ምክንያት ግብርን መክፈል ከውዴታ አስተዋጽኦነቱ ይልቅ የግዴታ ይዘቱ አመዝኖ እንዲታይ አድርጎታል፡፡ ግብር የመክፈል ግዴታ የተጣለበት ማንኛውም ግለሰብ በተቀመጠው መስፈርት መሠረት መክፈል ይኖርበታል፡፡ ግብር የሚጣልበት ማንኛውም ሰው ከመክፈል ውጪ ሌላ አማራጭ የለውም፡፡ ግብርን ለመክፈል እምቢተኛ መሆን በህግ ያስቀጣል፡፡

ግብር ሁኔታዊ አይደለም፡፡ ይህም ማለት ግብር ከመንግስት የተለየ ጥቅም ሲያገኙ የሚከፍሉት፣ ሳያገኙ ሲቀሩ ደግሞ የሚተውት ጉዳይ አይደለም፡፡ በምንከፍለው ግብር እና ከመንግስት በምናገኘው ጥቅም መካከል ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት የለም፡፡ በመሆኑም ግለሰቦች ግብር የሚከፍሉት ቀጥተኛና ተመጣጣኝ ጥቅም ከመንግስት ስለሚያገኙ ሳይሆን መንግስት የልማት እና መልካም አስተዳደር ዓላማውን እንዲያሳካ ለመደገፍ ነው፡፡

ግብር የሚሰበሰበው ለጋራ ጥቅም ነው፡፡ መንግስት ከነዋሪው የሚሰበስበውን ግብር እያንዳንዱ ግለሰብ ምን ያህል እንደሚከፍል ግምት ውስጥ ሳያስገባ ሁሉንም እኩል ተጠቃሚ ሊያደርጉ በሚችሉ ተግባራት ላይ እንዲውል ያደርጋል፡፡

ግብር የሚጣለው በተገኘ ጥቅም ላይ ነው፡፡ ምንም እንኳን ግብር የግዴታ መዋጮ ቢሆንም የትኛውንም ሰው ግብር የሚያስከፍል ገቢ (ጥቅም) ካላገኘ በስተቀር እንዲከፍል አይገደድም፡፡ ለምሳሌ አንድ ባለመኪና ጋራዥ ሄዶ መኪናውን ካላስጠገነ በስተቀር የአገልግሎት ተርን ኦቨር ታክስ ሊከፍል አይገባም፡፡ በተመሳሳይ አንድ ስራ የሌለው ሰው ባላገኘው ገቢ የደመወዝ ገቢ ግብር እንዲከፍል ሊገደድ አይችልም፡፡

መንግስት ግብር የሚጥለውና የሚሰበስበው የተለያዩ ዓላማዎች ለማሳካት ነው፡፡ ከዓላማዎቹ ውስጥም ገቢን በመሰብሰብ ለሚያከናውነው የልማትና መልካም አስተዳደር ሥራዎች እንዲውል ለማስቻል፣ የሀብት ክፍፍልን ለማመጣጠን፣ ኢኮኖሚውን ለማረጋጋት፣ ለህብረተሰቡ ጠንቅ የሆኑ ፍጆታዎች እንዳይበረታቱ ለማድረግ፣ የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚ ወይም ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት፣ የካፒታል ግንባታንና ክምችትን ለማፋጠን፣ የክልሎችን እድገት ለማመጣጠን፣ ውስን የሆነውን ሀብት በአግባቡ ለመጠቀም፣ የወጪ ንግድ ለማበረታታት፣ ሥራ አጥነትን ለመቀነስ ወይም የስራ ዕድልን ለመፍጠር፣ የህብረተሰቡን የገቢ አቅም ለማሳደግ፣ወዘተ. ይጠቀሳሉ፡፡

ግብር ከተለያዩ የገቢ ምንጮች ይሰበሰባል፡፡ ገቢ ማለት ማንኛውም የኢኮኖሚ ጥቅም ሲሆን፣ በመደበኛነት የተገኘ ባይሆንም ከማንኛውም ምንጭ በጥሬ ገንዘብ ወይንም በዓይነት በማንኛውም መልክ ለግብር ከፋዩ የተከፈለውን፣ በስሙ የተያዘውን፣ ወይንም የተቀበለውን ጥቅም ሁሉ ይጨምራል፡፡ ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ፣ መኖሪያ ቤትን ወይንም ድርጅትን በማከራየት የሚገኝ ገቢ፣ ከንግድ ስራ እንቅስቃሴ የሚገኝ ገቢ፣ የማዝናናት ሥራ ከሚሰራ ሙዚቀኛ ወይንም ስፖርተኛ በግል ካከናወነው ሥራ የሚያስገኘው ገቢ፣ ነዋሪነቱ በኢትዮጵያ ውስጥ ያልሆነ ሰው በቋሚ የንግድ ሥራ ድርጅት አማካይነት ከሚያከናውነው የንግድ ሥራ የሚያስገኘው ገቢ፣ ከማይንቀሳቀሱ ንብረቶች የሚገኝ ገቢ፣ከከብት እርባታ ከግብርና እና ከደን የሚገኝ ገቢ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኝ ቋሚ የንግድ ሥራ ድርጅት ተንቀሳቃሽ ንብረት በመሸጥ የሚገኝ ገቢ፣ ወዘተ. የገቢ ምንጮች በመባል ይታወቃሉ፡፡ በተለያዩ ጊዜያት በኢኮኖሚው ውስጥ በሚደረጉት ለውጦችና መሻሻል መነሻ ተጨማሪ የገቢ ምንጮች ሊፈጠሩ ወይንም የነበሩት ሊቀሩ ይችላሉ፡፡

**የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎች**

፩. ግብር ሁኔታዊ ነው ሲል ምን ማለቱ ነው?

፪. መንግስት ግብር የሚሰበስበው ለምንድን ነው?

፫. ግብር ከሚሰበሰብባቸው የገቢ ምንጮች ውስጥ ቢያንስ ሁለቱን ጥቀሱ፡፡

የግብር ገቢ በሁለት ዋና ዋና መደቦች ይፈረጃል፡፡ አንደኛው ቀጥተኛ ግብር ሲሆን፣ ማንኛውም ግለሰብ ወይንም ድርጅት ከሚያገኘው ገቢ ላይ እራሱ በቀጥታ የሚከፍለው የግብር ዓይነት ነው፡፡ በዚህ ውስጥም ከመቀጠር፣ ከቤት ኪራይ፣ ከንግድ ሥራዎች እና ከሌሎች ገቢዎች የሚገኙ የገቢ ግብሮች ይካተታሉ፡፡ ሌሎች ገቢዎች በመባል የሚጠቀሱት ከዕድል ሙከራ አሸናፊነት፣ የፈጠራ መብትን ከማከራየት፣ ከካፒታል ዋጋ ዕድገት፣ ከወለድ፣ከኢትዮጵያ ውጪ ከሚሰጥ አገልግሎት፣ ከአክሲዮን የትርፍ ድርሻ፣ ቋሚ ባልሆነ ሁኔታ ከንብረትና ኪራይ የሚገኙ ገቢዎች ናቸው፡፡

የደመወዝ ገቢ ግብር ማንኛውም ሰው ቀጥሮ ከሚያሰራቸው ሠራተኞች ላይ የሥራ ግብር ይቀንሳል፡፡ በየወሩ ከሠራተኞች ደመወዝ ተቀንሶ የሚሰበሰበውን የስራ ግብር ቀጣሪው ከእያንዳንዱ ወር መጨረሻ አንስቶ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ለግብር ባለሥልጣን ይከፍላል፡፡የዲፕሎማቲክ መብት ባላቸው ድርጅቶች የሚሠሩና ከአንድ በላይ ለሆኑ ቀጣሪዎች የሚሠሩ ሠራተኞች እራሳቸው አስታውቀው ይከፍላሉ፡፡

የቤት ኪራይ ግብር ቤትና ከቤት ጋር የተያያዙ ንብረቶችን በማከራየት የሚገኝ ገቢ ነው፡፡ ገቢውን የሚያገኘው ሰው በግብር ከፋዩ ደረጃ ላይ ተመስርቶ ከበጀት ወይም ከሂሣብ ዓመቱ ማለቂያ ጀምሮ ከአንድ እስከ አራት ወራት ባለው ጊዜ ውስጥ አስታውቆ ይከፍላል፡፡ የንግድ ሥራ ገቢ ግብር ደግሞ ከንግድ ሥራ እንቅስቃሴ በተገኘ ገቢ ላይ የሚከፈል ግብር ነው፡፡ የገቢ ማስታወቂያ የሚቀርበው በግብር ከፋዮች ደረጃ ላይ ተመስርቶ የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ ከአንድ እስከ አራት ወራት ውስጥ ነው፡፡

ሁለተኛው የግብር ዓይነት ቀጥታ ያልሆነ ግብር ነው፡፡ ቀጥታ ያልሆነ ግብር በማምረት፣ በአገልግሎትና ምርት ሽያጭ አማካይነት ከተጠቃሚው የሚሰበሰብ ነው፡፡ የግብሩ መሠረት ለምርትና አገልግሎት የሚከፈል ወጪ ሲሆን ግብሩም የምርት ወይም የወጪ ግብር ይባላል፡፡ በአገራችን የሚታወቁት ዋና ዋና ቀጥታ ያልሆኑ የግብር አይነቶች የሚባሉት የኤክሳይዝ ታክስ፣ የተርን ኦቨር ታክስ፣ የተጨማሪ እሴት ታክስ፣ የቴምብር ቀረጥ እና የጉምሩክ ቀረጥ ናቸው፡፡

የኤክሳይዝ ታክስ በአገር ውስጥ ሲመረቱም ሆነ ከውጪ ሲገቡ በተመሳሳይ ተመን የሚከፈል ግብር ነው፡፡ ማህበራዊ ጠቀሜታ ከሌላቸው፣ መሠረታዊ እና የቅንጦት ከሆኑ ምርቶች ግብሩ ይሰበሰባል፡፡ የግብሩ መሠረት ለአገር ውሰጥ ምርቶች የማምረቻ ዋጋ ሲሆን፣ ከውጪ ለሚገቡት ግን የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ዋጋ ነው፡፡ ለምሳሌ በሃገር ውስጥ በሚመረቱ እና ከውጭ ሀገር ወደ ሀገር ውስጥ በሚገቡ የተወሰኑ ዕቃዎች ላይ የሚከፈል የኤክሳይዝ ታክስ መጠንን ስንመለከት ማንኛውም ዓይነት ስኳር( በአንኳር መልክ) ሞላሰስን ሳይጨምር 33%፣ ማንኛውም ለስላሳ መጠጥ (ከፍራፍሬ ጭማቂዎችና እነዚህን ከመሳሰሉት በስተቀር) 30%፣ ማንኛውም የወይን ጠጅ መጠጥ 50%፣ ሽቶዎች እና ቶይሌት ወተርስ 100%፣ አሻንጉሊቶችና መጫዎቻዎች 20%፣ የቪዲዮ ዴክ 40%፣ በፋብሪካ የሚመረት የታሸገ ውሃ 20%፣ ጨው 30%፣ ቴሌቪዥን እና የቪዲዮ ካሜራዎች 40%፣  ከ1301 ሲ.ሲ በላይ እስከ 1800 ሲሲ ተሸከርካሪዎች 60%፣ በፋብሪካ የተሰሩ ወይም የተዘጋጁ ልብሶች 10% ነው፡፡

ተርን ኦቨር ታክስ በዕቃ ወይም በአገልግሎት ሽያጭ ላይ የሚከፈል ግብር ነው፡፡የግብር ማስከፈያው መሠረት የመሸጫ ዋጋው ነው፡፡ግብሩን የሚሰበስቡት በዓመትከብር 500,000 በታች ገቢ ያላቸው ለተጨማሪ እሴት ታክስ መመዝገብ የማይጠበቅባቸው ግብር ከፋዮች ናቸው፡፡

የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈለው በዕቃ ወይም በአገልግሎት ማምረት ወይም በንግድ ግብይት ሂደት በሁሉም ደረጃ በሚፈጠረው ተጨማሪ ዕሴት ላይ ነው፡፡ የግብሩ መክፈያ ጊዜው ወርሃዊ ሆኖ የሚቀጥለው ወር ከማለቁ በፊት ይከፈላል፡፡ የግብር ተደራራቢነትን ለማሰቀረት በግብዓት ላይ የተከፈለው ግብር ከመጨረሻ ምርት ግብር ላይ ይቀናነሳል፡፡ ይህም በአንድ ምርት ላይ ተደጋጋሚ ግብር እንዳይከፈል ያደርጋል፡፡ የግብር ተደጋጋሚነት በማስቀረትም የግብር ፍትሃዊነትን ይፈጥራል፡፡

የቁርጥ ታክስ ስርዓት ከተከፋይ ሂሳብ ላይ ግብርን ቀንሶ ማስቀረትና ዕቃዎች ወደ ሀገር በሚገቡበት ጊዜ ስለሚከፈል ግብሩ የቁርጥ ግብር አስተዳደር አንዱ አካል ነው፡፡ ስርዓቱም የግብር አሰባሰብን ለማቀላጠፍ የሚያገለግል ነው፡፡ ከመደበኛ የግብር አስተደደር ተግባሮች የሚያመልጡትን ግብይቶች ከምንጩ ለመያዝ ያግዛል፡፡

የቴምብር ቀረጥና ሽያጭ የሚፈፀመው መብት ወይም ግዴታ የተመሠረተበት፣ የተመዘገበበት፣ የተላለፈበት ማንኛውም ሰነድ ላይ ነው፡፡ የቀረጡ አከፋፈል በቁርጥ እና በዋጋ ላይ በመቶኛ ሆኖ እንደሰነዱ ይዘትና ዋጋ ይለያያል፡፡ የቴምብር ቀረጡ ከብር 50 በላይ የሚያስከፍል ሰነድ ሲያጋጥም ገንዘቡ ከተከፈለ በኋላ በሰነዶቹ ላይ ቀረጡ ስለመከፈሉ በማህተም ይረጋገጣል፡፡ ሰነዱ የያዘው ጉዳይ ከብር 50 በታች የሚያስከፍል ሲሆን የቴምብር ቀረጡ ከ0.10 ሣንቲም ጀምሮ እስከ 20 ብር ያለውን ቴምብር በመለጠፍ ይፈፀማል፡፡

በተለያዩ የገቢና ሌሎች የግብር ድንጋጌዎች መሠረት ግብር ከፋዮች ተለይተው ይመደባሉ፡፡ በህግ መሠረት ግብር ሊከፈለበት የሚገባ ገቢ የሚያገኝ ማንኛውም የምርትና አገልግሎት ወጪ የሚፈጽም ሰው ወይም ድርጅት ግብር ከፋይ ተብሎ ይታወቃል፡፡ ለግብር አከፋፈል እንዲያመች ግብር ከፋዮች በሦስት ደረጃ ተመድበዋል፡፡ የደረጃ “ሀ” ግብር ከፋዮች በህግ ሰውነት ያገኙ የግል ተቋማት፣ ዓመታዊ ገቢያቸው ከብር 500,000 እና ከዚያ በላይ የሆኑ ግለሰቦች ሲሆኑ የደረጃ “ለ” ግብር ከፋዮች ደግሞ ዓመታዊ ገቢያቸው ከብር 100,000 እስከ ብር 500,000 ድረስ የሆኑ ግለሰቦች ናቸው፡፡ እንዲሁም የደረጃ “ሐ” ግብር ከፋዮች ዓመታዊ ገቢያቸው ብር 100,000 እና ከዚያ በታች የሆኑ ግለሰቦች ናቸው፡፡

(ምንጭ፡- የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን (2002) ስለግብር/ታክስ አስተዳደር አስመልክቶ ከተዘጋጀ የግንዛቤ ማስጨበጫ ማብራሪያ ላይ ተሸሽሎ የተወሰደ)

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

፩. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከላይ የቀረበውን ምንባብ መሠረት በማድረግ ትክክል ለሆኑት "እውነት"፣ ስህተት ለሆኑት ደግሞ "ሐሰት" በማለት በቃል መልሱ፤ ምክንያታችሁንም ግለጹ፡፡

1. ግብር የግዴታ መዋጮ ቢሆንም ማንኛውም ሰው ግብር የሚያስከፍል ገቢ እስካላገኘ ድረስ እንዲከፍል አይገደድም፡፡
2. ግብር ዜጎች ከመንግስት ጥቅም ሲያገኙ የሚከፍሉት ሳያገኙ ሲቀሩ ደግሞ የሚተውት ጉዳይ ነው፡፡
3. ቀጥተኛ ግብር በማምረት፣ በአገልግሎትና በምርት ሽያጭ ከሚያገኙት ተጠቃሚዎች ላይ የሚሰበሰብ ነው፡፡
4. የቁርጥ ታክስ ስርዓት ከመደበኛ የግብር አስተዳደር ተግባራት የሚያመልጡትን ግብይቶች ከምንጩ ለመያዝ ያስችላል፡፡
5. ግብር የሚሰበሰበው የመንግስትን የገቢ መጠን ለመጨመር ብቻ ነው፡፡

፪. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከላይ የቀረበውን ምንባብ መሠረት በማድረግ ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በምረጥ መልሱ፡፡

1. ከቀጥተኛ የግብር ዓይነቶች ውስጥ የማይካተተው የትኛው ነው?

   ሀ. የጉምሩክ ቀረጥ　　ለ. የንግድ ስራ ግብር

   ሐ. የደመወዝ ገቢ ግብር　　መ. የቤት ኪራይ ገቢ ግብር

2. ስለግብር ትክክል ያልሆነው የትኛው ነው?

   ሀ. ግብር የሚሰበሰበው ለጋራ ጥቅም ነው፡፡

   ለ. ግብር የግዴታ መዋጮ ነው፡፡

   ሐ. ግብር የሚጣለው በተገኘ ጥቅም ላይ ነው፡፡

   መ. ግብር የሚከፈለው ስራ አጥነትን ለማስወገድ ነው፡፡

3. በአገር ውስጥ ሲመረቱም ሆነ ከውጭ ሲገቡ በተመሳሳይ ተመን የሚከፈል ግብር ምን ይባላል?

ሀ. ተርን ኦቨር ታክስ　　ለ. ኤክሳይዝ ታክስ

ሐ. የተጨማሪ እሴት ታክስ　　መ. የንግድ ስራ ግብር

4. "መንግስት ግብር ከሚሰበስብባቸው ዓላማዎች ውስጥ አንዱ የሀብት ክፍፍልን ለማመጣጠን ነው።" የሚለው ምንን ይገልጻል?

ሀ. ሀብታም እና ድሃ እኩል እንዲሆኑ ለማድረግ

ለ. የሀገሪቱን ሃብት እኩል ለዜጎች የየድርሻቸውን ለማከፋፈል

ሐ. የዜጎችን ፍትሃዊ የሀብት ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ

መ. ዜጎች ተመሳሳይ የሆነ ገቢ እንዲኖራቸው ለማድረግ

5. መንግስት ግብር ከሚሰበስብባቸው ምክንያቶች ውስጥ የማይካተተው የትኛው?

ሀ. ኢኮኖሚን ለማረጋጋት

ለ. የውጭ ንግድን ለማበረታታት

ሐ. የክልሎችን እድገት ለማመጣጠን

መ. ጎጂ የሆኑ ዕሴቶችን ለማበረታታት

፫. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት አጫጭር መልስ ስጡ።

ሀ. "ግብርን መክፈል ከውዴታ አስተዋጽኦነቱ ይልቅ የግዴታ ይዘቱ አመዝኖ እንዲታይ አድርጎታል።" ሲል ምን ማለቱ ነው?

ለ. የምንባቡ አምስተኛ አንቀጽ ዋና ሀሳብ ምንድን ነው?

ሐ. በቀጥተኛ ግብር እና ቀጥተኛ ባልሆነ የግብር ዓይነት መካከል ያለውን ልዩነት በአንድ አንቀጽ ጻፉ።

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

፩. ከዚህ በታች አንድ አንቀፅ የሚሆኑ የተለያዩ አረፍተነገሮች ተዘበራርቀው ቀርበዋል፡፡ እናንተ የዐረፍተ ነገሮችን ቅደም ተከተል ካስተካከላችሁ በኋላ የተሟላ አንቀጽ አድርጋችሁ ጻፉ፤ የአንቀጹንም ኃይለ ቃል ለዩ፡፡

ሀ. በጥቅሉ ያለሰላም ወጥቶ መግባት፣ ነግዶ ማትረፍ፣ ወልዶ መሳም፣ ተምሮ መመረቅ ስለማይቻል ትልቅ ዋጋ መስጠት ያስፈልጋል፡፡

ለ. መንፈሳዊና ቁሳዊ ፍላጎቶችን ለማሟላት እንዲሁም ሰው ሰራሽ እና ተፈጥሯዊ ቅርሶች ደህንነታቸው ተጠብቆ እንዲኖር ሰላም አስፈላጊ ነው፡፡

ሐ. ሰላም ለሰዉ ልጆች በጣም አስፈላጊ ከሆኑት ነገሮች ውስጥ አንዱ እና ወሳኙ ነው፡፡

መ. ሰላም የሰዎችን ደህንነት ለማስጠበቅና ለቀጣዩ ትውልድ የተሻለ ህይወትን ለመፍጠር ያስችላል፡፡

፪. ከዚህ በታች ከቀረቡት ኃይለ ቃሎች ውስጥ አንዱን በመምረጥ የተሟላ አንቀጽ ጻፉ፡፡

ሀ. ግብር መክፈል ለሀገር ዕድገት ትልቅ አስተዋጽኦ አለው፡፡
ለ. ኢትዮጵያ በርካታ ተፈጥሯዊ እና ሰው ሰራሽ የቱሪስት መስህቦች አሏት፡፡

፫. በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ገቢዎች ባለሥልጣን የአዲስ አበባ ግብር አወሳሰንና አሰባሰብ ፕሮግራም ልማት ድጋፍና ክትትል ዳይሬክተር የግንቦት ወር 2011 ዓ.ም የዋና ዋና ተግባራት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ላይ ከሐምሌ 2010 ዓመተ ምህረት እስከ ታህሳስ ወር 2011 ዓመተ ምህረት ያለውን የፌዴራል ገቢ ትልልፍ አፈጻጸም የሚያመለክት ቁጥራዊ መረጃ በሚከተለው ሠንጠረዥ ቀርቦላችኋል፡፡ ሠንጠረዡ ላይ የቀረበውን መረጃ መሠረት በማድረግ በተከታዮቹ ጥያቄዎች ላይ በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ ምላሻችሁን በጽሑፍ አስፍሩ፡፡

| ወር | በገገርው ተይዞ የሚሰበሰበው የተ.እ.ታ/VAT | 2%የገቢ ግብር ቅድመ ክፍያ | 3% የገቢ ግብር ቅድመ ክፍያ | ከኪራይ ገቢ (100%) | ጠቅላላ ድምድ |
|---|---|---|---|---|---|
| ሐምሌ | 39,954,846.08 | 39,476,954.25 | 97,515,971.29 | 1,386,111.32 | 178,333,882.94 |
| ነሀሴ | 41,604,053.24 | 81,022,596,.23 | 136,028,739,.28 | 786,362.51 | 259,441,751.26 |
| መስከረም | 83,818,712.43 | 49,085,392.47 | 91,553,440.22 | 2,157,765.76 | 226,615,310.88 |
| ጥቅምት | 35,743,238.39 | 42,469,576.13 | 88,893,501.64 | 20,483,753.61 | 187,590,069.77 |
| ህዳር | 58001575.35 | 61912076.32 | 84913498.6 | 2989.06 | 204,830,139.33 |
| ታህሳስ | 67,129,958.23 | 46,857,188.15 | 118,692,916.23 | 11,144,760.25 | 243,824,822.86 |
| ድምር | 326,252,383.72 | 320,823,783.55 | 617,598,067.26 | 35,961,742.51 | 1,300,635,977.04 |

ሀ. በሠንጠረዡ ላይ የቀረበውን መረጃ ወደ ግራፍ በመቀየር አመልክቱ፡፡

ለ. የቀረበውን ቁጥራዊ መረጃ መሰረት በማድረግ ቁጥሮቹን ወደ መቶኛ ቀይራችሁ ጻፉ፡፡

ሐ. የሐምሌ እና የነሀሴ ወርን የገቢ መጠን መሠረት በማድረግ ዘገባችሁን በአንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

፩. ቀጥሎ ከ "ሀ" እስከ "ቀ" የቀረቡትን ቃላት በፊደል ተራ ቅደም ተከተል ካስተካከላችሁ በኋላ ፍቺቸውን ከመዝገበ ቃላት በመፈለግ ጻፉ፡፡

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ሀ. ጨዋ | ለ. የብስ | ሐ. ገራገር | መ. ብራ | ሠ. ጠበቃ |
| ረ. ደባ | ሰ. አርማ | ሸ. ዙፋን | ቀ. ነጠፈች | |

፪. በተራ ቁጥር "፩" ላይ የቀረቡትን ቃላት ፍች የሚያመለክቱ ዓረፍተ ነገር ሥሩባቸው፡፡

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

### ጊዜ

የተፈጸሙም ሆኑ ያልተፈጸሙ ድርጊቶች በጊዜ ይወሰናሉ፡፡ ጊዜው በፊትና በኋላ ተብሎ የሚገለጸው ስለድርጊቱ ንግግር ከሚደረግበት በመነሳት ነው፡፡ ድርጊቱ የሚፈጸመው አሁን፣ ከአሁን በፊት ወይም በኋላ ሊሆን ይችላል፡፡ ከዚህም በመነሳት እየተፈጸመ ያለን፣ የተፈጸመን እና የሚፈጸምን ድርጊት መሠረት በማድረግ በግሶች ላይ የሚታየውን የጊዜ ሁኔታ እንደሚከተለው በሦስት ክፍሎ ማየት ይቻላል፡፡

1. የአሁን ጊዜ
2. ሃላፊ ጊዜ
3. የትንቢት ጊዜ ናቸው፡፡

1. የአሁን ጊዜ፡- አንድ በአሁኑ ጊዜ በመፈጸም ላይ ያለ ድርጊትን ወይም ሁነትን የሚገልጽ የጊዜ አይነት ነው፡፡ አሁን የሚባለዉ አንድ ሰው ስለ አንድ ድርጊት ንግግር የሚያደርግበት ጊዜ ነው፡፡ የአሁን ጊዜ ግስ "እየ-" የሚል ምእላድ ሊያስቀድም እና "ነው" የሚል ረዳት ግስ ሊያስከትል ይችላል፡፡

ምሳሌ፡-

ሀ. ልጁ እየ-አጠና ነው፡፡

ለ. ተማሪዎቹ ትምህርታቸውን እየ-ተማሩ ነው፡፡

በምሳሌዎቹ ላይ እንደተመለከተው "እየ-" የሚለው ጥገኛ ምዕላድ "አጠና" እና "ተማሩ" ከሚሉት ጋር በመቀናጀት እና "ነው" ከሚለው ረዳት ግስ ጋር በመግባት ድርጊቱ ያላለቀ እና አሁን እየተተገበረ ያለ መሆኑን ያሳያል፡፡

2. የሃላፊ ጊዜ፡- አንድ ድርጊት ከአሁን በፊት ተፈፅሞ ያለቀ መሆኑን የሚገልጽ የጊዜ ዓይነት ነው፡፡ ሃላፊ ጊዜ የዋህ ሃላፊ፣ የቅርብ ሃላፊና የሩቅ ኃላፊ ጊዜ በመባል ይታወቃሉ፡፡

ሀ. የዋህ ሃላፊ፡- ጊዜውን በውል ማሳየት የማይችል፣ አንድ ድርጊት ባለፈ ጊዜ ተፈጽሞ ያለቀ መሆኑን ብቻ ያመለክታል፡፡

ምሳሌ፡- ድርሰቷን ጽፋ ጨረሰች፡፡

በምሳሌው ላይ የተገለጸው ድርጊት ተፈጽሞ ያበቃ መሆኑን እንጂ፣ መቼ እንደተፈጸመ ጊዜውን የሚያመለክት ረዳት ግስ የለውም፡፡

ለ. የቅርብ ሃላፊ ጊዜ፡- አንድ ድርጊት ከቅርብ ጊዜ በፊት የተፈጸመ ወይም ድርጊቱ ከተፈጸመ ብዙ ጊዜ ያልቆየ መሆኑን ያመለክታል፡፡

ምሳሌ፡- መጽሐፉን ወስዷል፡፡

በምሳሌው ላይ እንደሚታየው የመውሰዱ ድርጊት የተፈጸመበት ጊዜ ሩቅ አለመሆኑን ያመለክታል፡፡ የቅርብ ሃላፊ የግስ አምዱ /ውኧስድ-/ ሲሆን፣ ከአምዱ ቀጥሎ የገባው የባለቤት አፀፋ /-ኦ/፣ ከባለቤት አፀፋው ቀጥሎ ደግሞ /-ኣል/ የሚለውን ረዳት ግስ አስከትሏል፡፡ ይህ የጊዜ ዓይነት በቦዝ የግስ ቅርጽ ላይ /-ኣል/ የሚለውን ረዳት ግስ ያስከትላል፡፡

ሐ. የሩቅ ሃላፊ ጊዜ፡- አንድ ድርጊት የተፈጸመበት ጊዜ ከሚነገርበት ጊዜ አንጻር ሩቅ መሆኑን ያመለክታል፡፡

ምሳሌ፡- መጽሐፉን ወስዶ ነበር፡፡

በምሳሌው ላይ እንደሚታየው መጽሐፉን የመውሰዱ ድርጊት የተፈጸመበት ጊዜ መራቁን ያመለክታል፡፡ የሩቅ ሃላፊ የግስ አምዱ /ውኧስድ-/ ሲሆን፣ ከአምዱ ቀጥሎ የገባው የባለቤት አፀፋ /-ኦ/፣ ከባለቤት አፀፋው ቀጥሎ ደግሞ “ነበር” የሚለውን ረዳት ግስ አስከትሏል፡፡

3. የትንቢት ጊዜ፡- አንድ ድርጊት ገና ያልተፈጸመ እና ወደፊት የሚፈጸም መሆኑን ያመለክታል፡፡

ምሳሌ፡- መጽሐፉን ይወስዳል፡፡

በምሳሌው ላይ እንደሚታየው መጽሐፉን የመውሰዱ ድርጊት ገና ያልተፈጸመ፣ የመውሰዱ ተግባር ወደፊት የሚከናወን መሆኑን ያመለክታል፡፡ ግሱም /ይ-/ የባለቤት አጸፋ፣ /ውኧስድ-/ የግስ አምድ እና /-ኣል/ የሚለውን ረዳት ግስ አካቶ ይዟል፡፡

(ምንጭ፡- ባየ ይማም (2000) “የአማርኛ ሰዋስው” ላይ ተሻሽሎ የተወሰደ)

፩. ቀጥሎ የቀረቡት ዐረፍተነገሮች በየትኛዉ የጊዜ አይነት እንደቀረቡ ግለፁ።

ሀ. የኢትዮጵያ መድህን ድርጅት የስራ አመራሮች ቀጣይ ሳምንት ስብሰባ ያደርጋሉ።

ለ. ባለፈው ክረምት በአብዛኛው የሃገራችን ክፍል ከፍተኛ ዝናብ ነበር።

ሐ. በብሔራዊ ቲያትር የስነ-ጽሁፍ ውድድር ይካሄዳል።

መ. መምህሩ ለተማሪዎቹ የፈተና ወረቀት እየመለሰ ነው።

ሠ. ነጋዴው ህብረተሰብ ግብሩን በወቅቱ ከፍሏል።

ረ. ሀኪሙ ታማሚውን እየመረመረ ነው።

፪. ከላይ በተራ ቁጥር “፩” ላይ የቀረቡትን ዐረፍተ ነገሮች በሃላፊ ጊዜ የቀረበውን ወደትንቢት ጊዜ፣ በትንቢት ጊዜ የቀረበውን ወደአሁን ጊዜ፣ በአሁን ጊዜ የቀረበውን ደግሞ ወደሃላፊ ጊዜ በመለወጥ ጻፉ።

፫. ለሚከተሉት የጊዜ አይነቶች ሁለት ሁለት አረፍተነገሮችን መስርቱ።

ሀ. የአሁን ጊዜ

1. ______________________________

2. ______________________________

ለ. የሃላፊ ጊዜ

1. ______________________________

2. ______________________________

ሐ. የትንቢት ጊዜ

1. ______________________________

2. ______________________________

# የምዕራፉ ማጠቃለያ

ምዕራፍ ኹለት ግብር በሚል ርዕስ የቀረበ ሲሆን በስሩም የተለያዩ ጉዳዮች ተነስተዋል፡፡ በማዳመጥ ክፍል ውስጥ "የግብር ጠቀሜታ እና አጀማመር" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ አዳምጣችሁ የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎችን ሠርታችኋል፤ በጽሑፉ ውስጥ ተካተው የሚገኙትን ጠቃሚ እና እምብዛም ጠቃሚ ያልሆኑ መረጃዎችን ለይታችኋል፡፡

በክፍል ኹለት ግብርን በሚመለከት ከመገናኛ ብዙኃን ወይም ከተለያዩ መጻሕፍት ያነበባችሁትን መረጃ፣ እንዲሁም ከገቢዎች ቢሮ የሰበሰባችሁትን መረጃ መሠረት በማድረግ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ቃላዊ ዘገባን በመጠቀም አቅርባችኋል፤ የክርክር አቀራረብ ሂደትን በመከተልም ክርክር እንዴት ሊቀርብ እንደሚችል ልምምድ አድርጋችኋል፡፡

በክፍል ሦስት "ግብር እና ዓይነቶቹ" በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ በማንበብ ለአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ምላሽ ሰጥታችኋል፡፡

በክፍል አራት ጽሕፈትን በሚመለከት በቀረቡት መልመጃዎች አማካይነት የተዘበራረቁ ዓረፍተ ነገሮችን ማስተካከልን፣ የተሟላ አንቀጽ መጻፍን፣ቁጥራዊ መረጃዎችን ወደግራፍ መቀየርና መረጃዎችን በአንቀጽ መጻፍን ተምራችኋል፡፡

በክፍል አምስት ቃላትን በፊደል ተራ ቅደም ተከተል በማስተካከል፣ ፍቻቸውን ከመዝገበ ቃል በመፈለግንና ትርጉማቸውን ሊያመለክቱ የሚችሉ ዓረፍተ ነገሮችን በመስራት ተለማምዳችኋል፡፡

በክፍል ስድስት ደግሞ የአሁን ጊዜን፣ የኃላፊ ጊዜን እና የትንቢት ጊዜን ሊያመለክቱ የሚችሉ ግሶችን መለየትና መጠቀምን ተምራችኋል፡፡

## የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

1. ቃላዊ ዘገባ ማለት ምን ማለት ነው?
2. በክርክር የቅድመ ዝግጅት ተግባር ሊከናወኑ የሚገባቸውን ተግባራት ዘርዝሩ፡፡
3. ከግብር ዓይነቶች ውስጥ ሁለቱን በመጥቀስ አብራሩ፡፡
4. ከዚህ በታች በቀረበው ሠንጠረዥ ላይ ከደሞዝ ገቢ የሚከፈልን የግብር መጠን በቅደም ተከተል የሚመለክት መረጃ በመቶኛ ተገጿል፡፡ የቀረበውን ቁጥራዊ መረጃ ወደ አንቀፅ ቀይራችሁ ጻፉ፡፡

| በየወሩ ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ በብር | ከመቀጠር በሚገኝ ገቢ ላይ ተፈፃሚ የሚሆን |
|---|---|
| 0 — 600 | 0% |
| 601 — 1,650 | 10% |
| 1,651 — 3,200 | 15% |
| 3,201 — 5,250 | 20% |
| 5,251 — 7,800 | 25% |
| 7,801 — 10,900 | 30% |
| 10,900 በላይ | 35% |

5. የአሁንና የሃላፊ ጊዜን ሊያመለክቱ የሚችሉ ሦስት ሦስት ዓረፍተ ነገሮችን ጻፉ፡፡

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ ኹለት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ቅጽ ቀርቦላችኋል፡፡ በዚህም መሠረት በእያንዳንዱ ማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ቅጹን አሟሉ፡፡

| ተ.ቁ. | የማመሳከሪያ ነጥቦች | √ | ? | X |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ካዳመጥኩት ምንባብ ጠቃሚና እምብዛም ጠቃሚ ያልሆኑ መረጃዎችን መለየት ችያለሁ | | | |
| 2 | ሀሳቤን በራስ መተማመን መግለጽ ችያለሁ | | | |
| 3 | ቃላዊ ዘገባ ማቅረብ ችያለሁ | | | |
| 4 | መረጃዎችን በጽሁፍና በግራፍ መተርጎም ችያለሁ | | | |
| 5 | አንቀጽ መጻፍ ችያለሁ | | | |
| 6 | መዘገበ ቃላትን መጠቀም ችያለሁ | | | |
| 7 | የተለያዩ የጊዜ አመልካች ግሶችን መለየትና መጠቀም ችያለሁ | | | |

፪. ከዚህ በላይ በቀረበው ቅጽ የ(?) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትገነዘቡ ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

አማርኛ

(፱ኛ) ክፍል

# ምዕራፍ ሦስት፡- ማዕድን ማውጣት

**የምዕራፉ ዓላማዎች፡-**

**ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፣**

- ❖ አዳምጣችሁ ፀሐፊው ሊያስተላልፍ የፈለገውን መልዕክት ትገልጻላችሁ፡፡
- ❖ አንብባችሁ በጽሑፍ ውስጥ ያሉ ተደራስያንን ትለያላችሁ፡፡
- ❖ ለጽሑፉ ማጠቃለያ ትሰጣላችሁ፡፡
- ❖ ለቃላት ተመሳሳይ ፍች ትሰጣላችሁ፡፡
- ❖ በጽሑፍ ውስጥ ሥርዓተ ነጥብን ትጠቀማላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

# የኢትዮጵያ ማዕድናት

### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

ከዚህ በታች ለቀረቡት የቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች ላይ ጥንድ ጥንድ በመሆን ከተወያያችሁ በኋላ የደረሳችሁባቸውን ነጥቦችም ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

1. ማዕድን ምንድን ነው?
2. ማዕድናት ምን ምን ጥቅም የሚኖራቸው ይመስላችኋል?
3. በሀገራችን ከሚገኙት የማዕድን ዓይነቶች ውስጥ የምታውቋቸውን ዘርዝሩ፡፡

### የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች እስካሁን ባዳመጣችሁት የምንባብ ክፍል መነሻነት በቃል መልስ ስጡ፡፡

1. በዓለማችን ላይ ማዕድናት የሚገኙት ከየት ነው?
2. ከማዕድናት መካከል የሰው ልጆች ልዩ ዋጋና ትርጉም የሚሰጡት ለየትኞቹ ነው?

### የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

፩. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ያደመጣችሁትን ምንባብ መሠረት አድርጋችሁ በመወያየት በጽሑፍ ምላሽ ስጡ፡፡

ሀ. በሀገራችን ማዕድናትን ማምረት የተጀመረው መቼ ነው?

ለ. በሀገራችን ማዕድናት በምን በምን መልኩ ይመረታሉ?

ሐ. በኢትዮጵያ ከሚገኙት የተፈጥሮ ማዕድናት ውስጥ የተወሰኑትን ጥቀሱ፡፡

መ. የጌጣጌጥ ማዕድናት ተፈላጊነታቸውና ተወዳጅነታቸው ከፍ እንዲል ያደረገው ምንድን ነው?

ሠ. ኢትዮጵያ ከጠጣር ማዕድናት ጋር ከተዋወቀች ረጅም ዘመን ያስቆጠረች ለመሆኑ በማስረጃነት የሚጠቀሰው ምንድን ነው?

፪. በጥንድ በመሆን ጸሐፊው ማስተላለፍ በፈለገው ሀሳብ ላይ በመወያየት የጋራ መልሳችሁን በቃል ግለጹ፡፡

## ክፍል ኹለት፡- መናገር

ከዚህ በታች በቀረቡት ርዕሶች ላይ በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ የቡድናችሁን ሀሳብ በቅደም ተከተል በማደራጀት ለክፍል ጓደኞቻችሁ ቃላዊ የዘገባ አቀራረብ መንገድን በመጠቀም አቅርቡ፡፡

፩. የማዕድን ዓይነቶችና መገኛ ቦታቸው

፪. የማዕድን ዓይነቶችና ጠቀሜታቸው

፫. በባህላዊ እና በዘመናዊ የማዕድን አወጣጥ ሂደት ላይ የሚስተዋሉ ልዩነቶች

## ክፍል ሦስት፡- ንባብ

# የማዕድናት ዓይነቶች እና ጠቀሜታ በኢትዮጵያ

### ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

ከዚህ በታች በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ የጋራ ምላሻችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡


፩. ማዕድናት ለአንድ ሀገር ከሚሰጧቸው ጥቅሞች የምታውቋቸውን ዘርዝሩ፡፡

፬. ወርቅ በሀገራችን በየትኛው ክፍል በብዛት የሚገኝ ይመስላችኋል?

፫. ከዚህ በታች "የማዕድናት ዓይነት እና ጠቀሜታ በኢትዮጵያ" በሚል ርዕስ የቀረበው ምንባብ ይዘት ምን ይመስላችኋል?

## የማዕድናት ዓይነቶች እና ጠቀሜታ በኢትዮጵያ

ኢትዮጵያ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች በርካታ የማዕድን ዓይነቶች አሏት፡፡ በሀገሪቱ ከሚገኙት የማዕድናት ዓይነቶች ውስጥ አንዱ ወርቅ ነው፡፡ **ወርቅ** ከከበሩ ማዕድናት አንዱ ነው፡፡ በጣም በሚስብ ቀለም፣ ዝገትን የመቋቋም እናበብዙ ልዩ ባህሪዎቹ ምክንያት በሰዎች ዘንድ በጣም የተከበረ ነው፡፡ አነስተኛየወርቅ መጠን በሁሉም ቦታ ይገኛል፡፡ይሁን እንጂ ከፍተኛ የሆነ የወርቅክምችት በብዛት የሚገኘው በኦሮሚያ፣ በትግራይ፣ በጋምቤላ፣ በቤንሻንጉልናበሌሎች አካባቢዎች ነው፡፡



ወርቅ

**ኦፓል** ብርሃንን የመሳብና የማንፀባረቅ ባህሪው የሰውን ዓይን መማረክ ብቻ ሳይሆን ቀልብንም በመሳብ የመጫጫን ስሜትን አስወግዶ ዘና የማለት ስሜትንና ውስጣዊ ሃይልን የሚያበረታታ ልዩ ማዕድን ነው፡፡ ውዱ ጠጣር ማዕድን ኦፓል በሃገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ የተገኘው እ.ኤ.አ. በ1990ዎቹ መጀመሪያ አካባቢ በታሪካዊቷ የሸዋ አካባቢ ሲሆን፣ ትልቅ ሊባል የሚችለው ግኝት እንደ እ.ኤ.አ

በ2008 ከመዲናችን 550 ኪሎ ሜትር ርቀት በምትገኘው ደቡብ ወሎ ዞን ልዩ ስሙ ወገል ጤና አካባቢ ነው፡፡

**አኳማሪን** ሌላው የከበረ ማዕድን ነው፡፡ እጅግ ከፍተኛ የሆነ መግነጢሳዊ ባህሪ ያለው ነው፡፡ የዘርፉ ተመራማሪዎች እንደሚሉት አኳማሪን የአዕምሯዊ አመክንዮ ሂደቶችን ያፋጥናል፡፡ እንዲሁም ፈጣን ምላሽ የመስጠት ችሎታን ያጠናክራል፡፡ አኳማሪን አረንጓዴ-ሰማያዊ እና ሰማያዊ ዓይነት የማዕድን ቤሪል ነው፡፡ ቀለሙ ብዙውን ጊዜ ቀለል ያለ አረንጓዴ  ሰማያዊ ነው፡፡ የአኳማሪን ክሪስታሎች መጠናቸው ትልቅ እና በአንፃራዊነት ንፁህ እና በጥሩ ሁኔታ የተመሰረቱ በመሆናቸው፣ በተለይም የማዕድን ናሙናዎችን ሰብሳቢዎች ዋጋቸውን ከፍ ያደርጉታል ፡፡

የከበረ ማዕድን ከሚባሉት አንዱ አሜቲስት ነው፡፡ **አሜቲስት** ከኳርትዝ ማዕድን ዓይነቶች ሐምራዊ ዝርያ ነው፡፡ እንደ ሳፋየር እና ታንዛኒት ያሉ ሌሎች ሐምራዊ ዕንቁዎች ቢኖሩም ብዙውን ጊዜ ከሐምራዊ ቀለም ጋር የሚዛመድ ዕንቁ ነው፡፡ አሜቲስት በዓለም ላይ በጣም ተወዳጅ የሆነ ሐምራዊ ዕንቁ ነው ፡፡ የኳርትዝ ሐምራዊ ቀለም ዓይነታቸው የተለያየ ሲሆን፣ ከ 2000 ዓመታት በላይ ለጌጣጌጥ መስሪያነት ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ አሜቲስት ዶቃዎችን እና ሌሎች ጌጣጌጦችን ለመስራት እና ለጌጣጌጥ አገልግሎት የሚውል ማዕድን ነው፡፡

**የድንጋይ ከሰል** ሌላው የከበረ ማዕድን ሲሆን ከፍተኛ መጠን ያለው ካርቦን እና ሃይድሮካርቦኖች ያሉት ተቀጣጣይ ጥቁር ወይም ቡናማ ጥቁር የደለል ድንጋይ ነው፡፡ የድንጋይ ከሰል ለኃይል ምንጭነት ያገለግላል፡፡ በሙቀት አማካኝነት የዕፅዋት ክምችት ወደ ከሰል እንዲለወጥ አድርገውታል፡፡ የድንጋይ ከሰል ከሃይል ምንጭነት በተጨማሪ ለሲሚንቶ፣ ለብረታብረት እና ለጨርቃጨርቅ ፋብሪካ ግብዓትነት ያገልግላል፡፡

የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

፩. እ.ኤ.አ. በ2008 የኦፓል ምርት በየትኛው የሀገራችን ክፍል ተገኘ?

፪. ከ2000 ዓመታት በላይ ለጌጣጌጥ መስሪያነት የዋለው ማዕድን ምን በመባል ይጠራል?

፫. ለሲሚንቶ፣ ለብረታብረትና ለጨርቃጨርቅ ፋብሪካዎች ግብዓትነት የሚውለው ማዕድን ምን ይባላል?

**ኳርትዝ** የተሰኘውም ሌላኛው የከበረ ማዕድን ነው፡፡ ኳርትዝ በምድር ገጽ ላይ እጅግ  የበዛና በስፋት የሚገኝ ማዕድን ነው፡፡  በሁሉም የአለም ክፍሎች የሚገኝ እና የተትረፈረፈ ነው፡፡ በእሳተ ገሞራ አማካኝነት፣ በደቃቅ አለቶች ውስጥ በብዛት ይገኛል ፡፡ ሜካኒካዊ እና ኬሚካዊ የአየር ሁኔታ መቋቋም የሚችል ነው፡፡ በብዛት በተራራ ጫፎች፣ በባህር ዳርቻ፣ በወንዝ እና በበረሃ አሸዋ በብዛት ይገኛል፡፡ ኳርትዝ የብርጭቆ ወረቀት፣ ብርጭቆ፣ የኮምፒዩተር ዕቃዎችና ጌጣጌጥ ለመስሪያነት ይጠቅማል፡፡

**የ**ሩቢ ማዕድን ከኮራደም የማዕድን ዓይነቶች አንዱ ነው፡፡ ሩቢ በጣም ታዋቂ ከሆኑ የከበሩ ማዕድናት ተጠቃሹ ሲሆን ጌጣጌጥ ለመስራት በስፋት ጥቅም ላይ ይውላል፡፡ ሩቢ የእጅ አምባር፣ የአንገት ጌጥ፣ ቀለበት እና የጆሮ ጌጥ ሌሎችንም የጌጣጌጥ ዓይነቶች ለመስራት ይጠቅማል፡፡ በሌሎች ጌጣጌጦች ላይ ፈርጥ በመሆን በርካታ ጌጣጌጦችን ለመስራት ይጠቅማል፡፡ በዓለም ላይ ውድ ከሚባሉት ድንጋዮች ውስጥ ሩቢ አንዱ ሲሆን ከሀምራዊ እስከ ደም የሚመስል ቀይ ቀለም ያለው የከበረ ድንጋይ ነው፡፡ ቀዩ እንቁ በማለትም ይጠሩታል፡፡ በዓለም ላይ ከባድና ተፅዕኖ ፈጣሪ ከሚባሉት ድንጋዮች ውስጥ አንዱ የሆነው ሩቢ ጥንታዊ እና ታሪካዊ ከመሆኑ ባሻገር እስካሁን ድረስ በባህላዊ፣ በማህበራዊና በሀይማኖታዊ መንገድ ተፅዕኖው ከፍ ያለ ነው፡፡



ሩቢ

**ሳፋየር** (Sapphire) ከከበሩ ማዕድናት ውስጥ ተጠቃሽ ነው፡፡ ሳፋየር በዓለም ላይ ውድ ከሚባሉት ጌጣጌጦች ውስጥ የሚመደብ ሲሆን፣ ከአልማዝ በመቀጠል ሁለተኛው ውድ ድንጋይ ነው፡፡ በብዛት ሰማያዊ ቀለም ያለው ሲሆን ቢጫ፣ ሀምራዊ፣ ብርቱካናማ እና ነጭ ቀለሞችም አሉት፡፡ ብዙውን ጊዜ በቀን ብርሃን ወይም በፍሎረሰንት መብራት ሲታይ ሐምራዊ ቀለምን ያሳያሉ፡፡ ሳፋየር የጥንካሬ ምልክት ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ በከበሩ ድንጋዮች ላይ ተቆርጠው ፈርጥ የሚሆኑ እና ጌጣጌጥ ተሰርቶባቸው የሚለበሱ ናቸው፡፡ ሳፋየር ከቀይ ቀለም በስተቀር በሁሉም ቀለም በሚባል ደረጃ ይገኛል፡፡ ነገር ግን በዓለም ላይ ተፅዕኖ ፈጣሪና ተወዳጅ የሆኑት ሁለት ቀለሞች ናቸው፡፡



ሳፋየር

**ሰንፔር** በተለያዩ ሀገራት በሀይማኖታዊና በባህላዊ መንገዶች እንደየቀለማቸው ሊያስገኙ ይችላሉ የሚባሉ ጥቅሞች አሉት፡፡ ሰማያዊ ሰንፔር በዓለም ላይ ሰንፔርን በቀለሙ ሰማያዊ ብቻ እንዲመስለን ያደረገ ተፅዕኖ ፈጣሪ ድንጋይ ነው፡፡ ሌላው ደግሞ ሰማያዊ ሰንፔር የተለየ ሀይል እንዳለው በተለያዩ ጂሞሎጂስቶችና ኮከብ ቆጣሪዎች እንዲሁም ሀይማኖታዊ መፅሐፎች በመገለፁ ብዙ ሰወች እንዲመርጡት ምክንያት ሆኗል፡፡ በጂሞሎጂስቶች የተጠና ለሰዎች ሊያስገኙላቸው ይችላሉ የተባሉ ጥቅሞች ግልፀኝነትን፣ መንፈሳዊና አእምሯዊ ጥንካሬን ይጨምራል፤ የአመራር ብቃትን የላቀ ያደርጋል፤ ለአዕምሮ አዎንታዊ ምላሾችን ያስገኛል፤ የማስታወስ ችሎታን ያጎለብታል፤ ተስፋን ይጨምራል፤ የፈጠራ ችሎታን ያጎለብታል፤ ከመጥፎ አጋጣሚዎች ይጠብቃል፤ ከመብረቅ

ከማእበልና ከጎርፍ አደጋ እንዲሁም ከሰው ሰራሽ አደጋዎችና ጥቃቶች ይከላከላል ብለው ያምናሉ፡፡

ሌላው በአለምላይ ተወዳጅና ተፅዕኖ ፈጣሪው የሰንፔር ዓይነት ቢጫ ሰንፔር ነው፡፡ ቢጫ ሰንፔር በብዛት የማይገኝ የሰንፔር ዓይነት ሲሆን፣ እንደ ሰማያዊው ሁሉ የተለያዩ ጥቅሞች ስላሉት አስፈላጊ ነው፡፡ ቢጫ ሰንፔር በተለይ ለምግብ እንሽርሽሪትና የሆድን የውስጥ ሰላም ያመጣል ተብሎ ይታመናል፡፡ ለአዕምሯችን ትኩረትን ይጨምራል፡፡ በውስጣችን የሚመላለሱ መጥፎ ነገሮችን ያጠፋል ተብሎም ይታመናል፡፡ ቢጫ ሰንፔር በጣም ብዙ ያልተዘረዘሩ ጥቅሞች አሉት፤ ምክንያቱም ስለሰንፔር አንድ ራሱን የቻለ መጽሐፍ ያስፈልገዋል፡፡

**ኤመራልድ** ሌላው የከበረ ማዕድን ሲሆን፣ የተለያዩ ስያሜዎች ነበሩት፡፡ ማዕድኑ በቀደሙት ጊዚያት በተለያዩ ሃይማኖቶች ልዩ ክብር ይሰጠው ነበር፡፡ በግብጽ የእውነተኛ ህይወት ምልክት ተደርጎ ይወሰድ ነበር፡፡ የነገስታት የክብር መገለጫ፣ መዋቢያ እንደሆነም ይታሰባል፡፡ ይህ የከበረ ማዕድን የፈጣሪ ስጦታ እንደሆነም ይታመናል፡፡ የእውነተኛ ፍቅር መገለጫ ተደርጎም ይወሰዳል፡፡ ኤመራልድ የተለያዩ ትርጉሞችና ጥቅሞች አሉት፡፡ የወደፊት ተስፋና የዕድገት ምልክትም ተደርጎ ይወሰዳል፡፡ የስነ ልቦና ባለሙያዎች ልብን በሃሴት የሚሞላ፣ ውስጣዊ የተነቃቃ ስሜትን የሚፈጥር ልዩ ማዕድን ነው ይሉታል፡፡ በራስ መተማመንን የሚፈጥር፣ የማሰብ አድማስን የሚያሰፋና ጥበበኛ ለመሆንም የሚጠቅም እንደሆነም ይገልጻሉ፡፡ የመረዳትን ችሎታ የሚጨምር ነው የሚሉትም አሉ፡፡



ኢመራልድ

በዓለም ላይ የከበሩ ማዕድናት ከሚባሉት ከዲያመንድ ፣ ከሩቢና ከሳፋየር መካከል አንዱ ነው፡፡ ኢመራልድ አረንጓዴ ቀለም ያለው ሲሆን፣ ሰማያዊ አረጓዴ ወይንም ቢጫ አረንጓዴ ሆኖ ይገኛል፡፡ በሁሉም ቦታ የማይገኝ በተወሰኑ ቦታዎች ብቻ የሚገኝ ነው፡፡ ኢመራልድ በአለም ላይ በ ኮሎምቢያ ፣ በ ዛምቢያ፣ በብራዚልና በዙምባብዌ ሀገሮች ይገኛል፡፡ ሀገራችንም የኢመራልድ ማዕድን ባለቤት ነች፡፡ በኢትዮጵያ የኢመራልድ ማዕድን የታወቀው በባህላዊ አምራቾች በ2008 ዓ.ም መጨረሻ ነው ፡፡ ማዕድኑ በስፋት የተገኘው በኦሮሚያ ክልል በጉጂ ዞን ሰባቦሩ ወረዳ ነው፡፡ ኤመራልድ በሌሎች ቦታዎችም ይገኛል፡፡

ሌላው ደግሞ **የታንታለም** ማዕድን ሲሆን፣ በቀደሙት ጊዜያት ታንታሊየም እየተባለ ይጠራ ነበር፡፡ ስያሜው ታንታለስ ከሚለው የግሪክ ቃል የመጣ ነው፡፡ ጠንካራ እና ሰማያዊ ግራጫ ቀለም ያለው ከብረት ምድብ የሚመደብ ሲሆን በቅይጥ መልክም ይገኛል፡፡ ፕላቲኒየምን በመተካት ለቤተ-ሙከራ መሳሪያዎች አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡ ለኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡ ለሞባይል ስልክ፣ለዲቪዲ ማጫወቻና ለኮምፒዩተሮች ይጠቅማል፡፡ ለቴሌቭዥን ድምጽ ጥራት መጨመር ቁልፍ ሚና የሚጫወተው የታንታለም ማዕድን ነው፡፡ ለህክምና መሳሪያዎች ያለው ጠቀሜታም ከፍተኛ ነው፡፡

(ምንጭ:- የኢትዮጵያ ማዕድን ሚኒስቴር)

## የአንባቦ መረዳት ጥያቄዎች

፩. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቃል ምላሽ ስጡ፡፡

ሀ. በኢትዮጵያ ከሚገኙት የማዕድን ዓይነቶች ውስጥ ሦስቱን ጥቀሱ፡፡

ለ. ዝገትን የመቋቋምና በሰዎች ዘንድ በጣም የተከበረው የማዕድን ዓይነት የትኛው ነው?

ሐ. ኦፓል የተባለው ማዕድን በሀገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ የተገኘው መቼ እና የት ነው?

መ. የማዕድን ናሙና ሰብሳቢዎች ዋጋውን ከፍ ያደርጉታል የተባለው ማዕድን የትኛው ነው?

ሠ. በጂኦሊጅስቶች ጥናት መሠረት ሰንፔር የተባለው ማዕድን ለሰዎች ሊያስገኝ ይችላል ከተባሉት ጥቅሞች ውስጥ ቢያንስ ሦስቱን ግለጹ።

፪. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልሱ።

1. ዶቃዎችንና ሌሎች ጌጣጌጦችን ለመስራት የሚውለው የከበረ ማዕድን ምን ይባላል?

ሀ. ታንታለም ለ. አሜቲስት

ሐ. ሩቢ መ. ሳፋየር

2. የስነ-ልቦና ባለሙያዎች ኢመራልድ የተባለው ማዕድን ልብን በሀሴት የሚሞላ እንደሆነ ይገልጻሉ። ይህ ሃሳብ ምንን ያመለክታል?

ሀ. የውስጥ ደስታን ይፈጥራል

ለ. የሰዎችን ሞራል ያነቃቃል

ሐ. ሆድ እንዲሞላ ያደርጋል

መ. የሰዎችን ውስጣዊ ስሜት ያንፀባርቃል

3. በምንባቡ መሰረት ማዕድናት ከሚሰጡት ጥቅም ውስጥ ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ. ለጌጣጌጥ መስሪያነት

ለ. ምቹ አካባቢን መፍጠሪያነት

ሐ. ፈጣን ምላሽ መስጠት

መ. የምግብ እንሸርሸሪት ማምጣት

4. ለኃይል ምንጭነት የሚያገለግለው የማዕድን ዓይነት የትኛው ነው?

ሀ. አሜቲስት ለ. ሩቢ ሐ. የድንጋይ ከሰል መ. ኳርትዝ

5. በባህላዊ ማህበራዊና ኃይማኖታዊ ተፅዕኖው ከፍ ያለው የከበረ ማዕድን የትኛው ነው?

ሀ. ታንታለም ለ. ኢመራልድ ሐ. ወርቅ መ. ሩቢ

6. በተራሮች ጫፍ፣ በባህር ዳርቻ፣ በወንዝ እና በበረሃ አሸዋ በብዛት የሚገኘው ማዕድን የትኛው ነው?

ሀ. ሰንፔር ለ. ሳፋየር ሐ. ወርቅ መ. ኳርትዝ

፫. በምንባቡ መሠረት በ "ሀ" ረድፍ ለቀረቡት ሀሳቦች ከ "ለ" ረድፍ ተስማሚውን መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ አዛምዱ፡፡

| "ሀ | "ለ" |
|---|---|
| 1. በሌሎች ጌጣ ጌጦች ላይ ፈርጥ በመሆን ለበርካታ ጌጣጌጥ መስሪያ የሚጠቅም | ሀ. ኢመራልድ |
| 2. በፍሎረሰንት መብራት ውስጥ ሐምራዊ ቀለም የሚያሳይ | ለ. ቢጫ ሰንፔር |
| 3. ለምግብ እንሽርሽሪትና ለሆድ የውስጥ ሰላም ማምጣት | ሐ. ሳፋየር |
| 4. ሰማያዊ አረንጓዴ ወይም ቢጫ አረንጓዴ ሆኖ የሚገኝ | መ. ታንታለም |
| 5. ለኤሌክቶኒክስ መሳሪያዎች ጠቀሜታ ያለው | ሠ. ሩቤ |

፬. በኢትዮጵያ ውስጥ ስለሚገኙ ማዕድናት ዓይነትና ጠቀሜታ በሚመለከት አንብባችኋል፡፡ የማዕድናቱ ተጠቃሚ እነማን ሊሆኑ ይችላሉ? ለምን?

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

፩. ከላይ የቀረበውን ምንባብ አጠቃላይ ሀሳብ በሁለት አንቀጽ አሳጥራችሁ ጻፉ፡፡

፪. በአካባቢያችሁ የምታውቋቸውን የማዕድን ዓይነቶች ከዘረዘራችሁ በኋላ ለምን አገልግሎት እንደሚውሉ ዘርዝራችሁ ጻፉ፡፡

፫. ከዚህ በታች ከቀረቡት ርዕሶች አንዱን በመምረጥ አንቀጽ ጻፉ፡፡

፫.፩. የማዕድን ጥቅም

፫.፪. የትምህርት አስፈላጊነት

፫.፫. ተግቶ ማጥናት

### የሥርዓተ ነጥቦች

በጽሑፍ ውስጥ የሚገቡ ነጥቦችና ምልክቶች የቃላት፣ የሐረጋት እና የዐረፍተ-ነገሮች አሰላለፍ፣ የቋንቋውን ሰዋስዋዊ ሕግጋት በመከተል፣ በጽሑፍ የሰፈረው መልዕክት ያለምንም መድበስበስ፣ በአንድ አፍታ የንባብ ዕይታ ለአንባቢው እንዲከሰት፣ መልዕክቱ አሻሚና የተዛባ እንዳይሆን በማድረጉ በኩል ትልቅ ሚና አላቸው፡፡

በአማርኛ ቋንቋ ጽሑፎች ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉ በርካታ የሥርዓተ ነጥብ ዓይነቶች አሉ፡፡ አንድ የሥርዓተ ነጥብ ዓይነት ከአንድ በላይ አገልግሎት ሊኖረው ይችላል፡፡ በሚከተለው ሠንጠረዥ ላይ የተካተቱት የሥርዓተ ነጥብ ዓይነቶች ከሚኖራቸው አገልግሎት ውስጥ አንዱን ሊያመለክት ከሚችል ምሳሌ ጋር ቀርበዋል፡፡

| ተ.ቁ. | የሥርዓተ ነጥብ ዓይነቶች | ምሳሌ |
|---|---|---|
| 1 | አንድ ነጥብ (.) | ነጋዴው በስድስት ወራት ውስጥ 1.25 ሚሊዮን ብር አተረፈ፡፡ |
| 2 | ሁለት ነጥብ (:) | የመጀመሪያው ክፍለ ጊዜ ጠዋት በ2:30 ሰዓት ይጀምራል፡፡ |
| 3 | ሦስት ነጥብ ወይም ነጠብጣብ (…) | ሰርገኛ መጣ … |
| 4 | ሁለት ነጥብ ከሰረዝ (:-) | በመማሪያ መጽሐፋችን ውስጥ ዘጠኝ ምዕራፎች ይገኛሉ፡፡ እነሱም፡- |
| 5 | አራት ነጥብ (፡፡) | ልጆች ጨዋታ ይወዳሉ፡፡ |
| 6 | ትዕምርተ - ጥ ያ ቄ / የጥያቄ ምልክት (?) | ምን እያደረጋችሁ ነው? |
| 7 | ትዕምርተ-አንክሮ/ቃለ አጋኖ (!) | ጎሽ! ደግ አደረጉ! |
| 8 | ትዕምርተ-ጥቅስ (“ ”) | የህመሙ መንስዔ የ “ነርቭ” መሸማቀቅ ነው፡፡ |
| 9 | ነጠላ ትዕምርተ-ጥቅስ (‹ ›) | “ጥሩ ውጤት ለማምጣት ‘ተግታችሁ አጥኑ፡፡ የሚለውን የመምህራችንን ምክር መዘንጋት የለብንም”በማለት የክፍል አለቃችን መከረን፡ |
| 10 | ሙሉ ሰረዝ (—) | ከተራ ቁጥር 1 — 5 |
| 11 | ነጠላ ሰረዝ (፣/÷) | ተማሪዎቹ ደብተራቸውን፣ መጽሐፋቸውን እና ማስመሪያቸውን ይዘው መጥተዋል፡፡ |
| 12 | ድርብ ሰረዝ (፤) | ትምህርቷን በሚገባ ታጠናለች፤ የዕረፍት ጊዜዋን ባግባቡ ትጠቀማለች፤ ወላጆቿንም በሥራ ታግዛለች፤ |

| | | |
|---|---|---|
| 13 | ቅንፍ ( ) | የበኩር ልጄ (የመጀመሪያ ልጄ) በህክምና ሙያ ተመረቀች፡፡ |

ከላይ በቀረበው ሠንጠረዥ ውስጥ ከተካተቱት በተጨማሪ ንዑስ ሰረዝ(-)፣ ትዕምርተ-ስላቅ (¡)፣ እመጫት(^)፣ እዝባር ወይም አቆልቋይ ( / ) የመሳሰሉት ይገኙበታል፡፡

፬. ከዚህ በታች ሥርዓተ ነጥቦቹ ያልተሟሉለት አጭር ጽሁፍ ቀርቦላችኋል፡፡ ጽሁፉን በሚገባ በማንበብ በተገቢው የሥርአተ ነጥብ ዓይነት አሟልታችሁ እንደገና ጻፉ፡፡

> ከዕለታት አንድ ቀን አንድ አዳኝ በወጥመድ አንዲት ዋኔ ይዞ ወደቤቱ ሲመለስ፣ ወዴት ነው የምትወስደኝ ብላ ዋኔዋ ጠየቀችው አዳኙም፣ ምን ትጠይቂኛለሽ አርጄ ልበላሽ ነዋ ብሎ መለሰላት እንዴት ያለኸው ሞኝ ነህ አሁን እኔን በልተህ ልትጠግብ ነው እስቲ አስተውለህ ተመልከተኝ! ሰውነቴ በጣም ያነሰ ፍጥረት ነኝ፡፡ ከጉሮሮህ እንኳ አልወርድም፡፡ ይልቅዬ እንስማማ! እኔ የሚጠቅሙህን ሶስት ምክሮች ልስጥህ እኔን ደግሞ ማረኝ በዚህ ከተስማማን አንዱን አሁን ሁለተኛውን ስትለቀኝ ከዛፉ ላይ ሁኜ ሶስተኛውን ደግሞ እዚያ ማዶ ካለው ዳገት አፋፍ ላይ ተቀምጬ እነገርሃለሁ አለችው፡፡

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

፩. በጥንድ በመሆን ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላት ሁለት የሌተለያዩ ፍቾቻቸውን የሚያመለክቱ ዐረፍተ ነገሮችን መስርቱ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሀ. ማዕድን | ለ. ተማረች | ሐ. ጠረጠረች | |
| መ. አልቦ | ሠ. ምሳ | ረ. ደግሰው | |
| ሰ. ደለበ | ሸ. ሰከነ | ቀ. ቀለበ | በ. ለፋ |

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ስር የተለያዩ ጉዳዮች ተነስተዋል፡፡ በማዳመጥ ክፍል “የኢትዮጵያ ማዕድናት” በሚል ርዕስ በንባብ የቀረበላችሁን ምንባብ መሠረት በማድረግ የተለያዩ የማዳመጥ ክሂልን ሊያዳብሩ የሚችሉ የመልመጃ ጥያቄዎችን ሠርታችኋል፡፡

በክፍል ኹለት መናገር በሚለው ስር ደግሞ በመረጣችሁት ርዕስ ላይ በመዘጋጀት የቃል ዘገባ አቀራረብን ተለማምዳችኋል፡፡

በክፍል ሦስት በቀረበላችሁ ምንባብ መነሻነት የንባብ ክሂላችሁን ሊያዳብሩ የሚችሉ ጥያቄዎችን ሠርታችኋል፡፡

በክፍል አራት ጽህፈትን በሚመለከት የምንባቡን ዋና ሀሳብ አሳጥራችሁ መጻፍን፣ አንቀጽ መጻፍን፣ የአማርኛ ሥርዓተ ነጥብ ዓይነታቸውን እና አጠቃቀማቸውን ተምራችኋል፤ በቀረበላችሁ የመልመጃ ጥያቄ መነሻነትም ሥርዓተ ነጥቦችን ተጠቅማችኋል፡፡

በክፍል አምስት ለቃላት ተመሳሳይ ፍች መስጠትን ተምራችኋል፡፡

## የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

1. አንድን ጽሁፍ አሳጥራችሁ ስትጽፉ ልትከተሏቸው ከሚገቡ ነጥቦች ውስጥ ቢያንስ ሦስቱን ግለጹ፡፡
2. ከሥርዓተ ነጥብ ዓይነቶች ውስጥ የቅንፍን እና የድርብ ሰረዝን ጠቀሜታ በምሳሌ በማስደገፍ አብራሩ፡፡
3. በሀገራችን የሚገኙትን የማዕድን ዓይነቶች የሚያመለክት አጭር ጽሁፍ ጻፉ፡፡

# የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ ሦስት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ቅጽ ቀርቦላችኋል፡፡ በዚህም መሠረት በእያንዳንዱ ማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ቅጹን አሟሉ፡፡

| ተ.ቁ. | የማመሳከሪያ ነጥቦች | √ | ? | X |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ያዳመጥኩትን ምንባብ መልዕክት መግለጽ ችያለሁ | | | |
| 2 | ባነበብኩት ምንባብ ውስጥ ያሉትን ተደራሲያን መግለጽ ችያለሁ | | | |
| 3 | የቀረበውን ጽሁፍ አሳጥሬ መጻፍ ችያለሁ | | | |
| 4 | የሥርዓተ ነጥብ ዓይነቶችና ጠቀሜታ በመለየት በጽሁፍ ውስጥ መገልገል ችያለሁ | | | |
| 5 | ለቃላት ተመሳሳይ ፍች መስተት ችያለሁ | | | |

፪. ከዚህ በላይ በቀረበው ቅጽ የ(?) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትገነዘቡ ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

አማርኛ

(፱ኛ) ክፍል

# ምዕራፍ አራት፡- ልቦለድ

**የምዕራፉ ዓላማዎች፡-**

**ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፣**

- ❖ አዳምጣችሁ ታሪኩን ትተርካላችሁ፡፡
- ❖ በታሪኩ ውስጥ ያሉትን ዋና ገጸባህርያት ትናገራላችሁ፡፡
- ❖ ለክፍል ደረጃው የሚምጥን አጭር ልቦለድ ትጽፋላችሁ፡፡
- ❖ የተለያዩ ሀረጎችን በመጠቀም ዐረፍተ ነገር ትመሰርታላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

፩. ተማሪዎች ከዚህ በፊት ልቦለድ አንብባችሁ ታውቃላችሁ? ካነበባችሁ የምታስታውሱትን ለጓደኞቻችሁ ንገሩ፡፡

፪. ከዚህ ቀጥሎ መምህራችሁ "ሲጨልም" በሚል ርዕስ የቀረበ አንድ አጭር ልቦለድ ያነቡላችኋል፡፡ ልቦለዱን ከማዳመጣችሁ በፊት ከርዕሱ በመነሳት ስለምን ጉዳይ ሊያነሳ እንደሚችል ገምቱ፡፡

### የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

1. በምንባቡ ላይ የአዛውንቱ ዕድሜ ምን ያህል እንደሆነ በትክክል ተገልጿል?
2. "… ለእንቶ ፈንቶ ጉዳይ የማባክነው ጊዜ የለኝም … " ያለው ማነው? ለምን?
3. የመድኃኒት ቤቱ አስተናጋጅ ለአዛውንቱ መድኃኒቱን ተቀብለው ብሩን የሚመልሱላቸው ይመስላችኋል? ለምን?

### የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

፩. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት መልሳቸውን በጽሑፍ ግለጹ፡፡

1. ባዳመጣችሁት አጭር ልቦለድ ውስጥ አዛውንቱ "ለስራ ያልደረሱ ለእህል ያላነሱ" ሲሉ ምን ማለታቸው ነው፡፡
2. በልቦለዱ ውስጥ ያሉትን ዋና እና ንዑሳን ገፀባህሪያት ዘርዝራችሁ ፃፉ፡፡
3. የታሪኩን ትልም ግለጹ፡፡
4. ባዳመጣችሁት ልቦለድ ውስጥ የተገለጸው ድርጊት የተፈጸመበት ቦታ የት ነው?
5. ከምንባቡ ምን ተረዳችሁ?

፬. ከዚህ በታች የቀረቡት ቃላት እና ሀረጋት ካዳመጣችሁት ጽሁፍ የወጡ ናቸው፡፡ በቡድን በመወያየት ፍቻቸውን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

ሀ. ነካ ያደርገዋል

ለ. የእርጎ ዝንብ

ሐ. እንደማታራቁት

መ. ሲዘላብድ

ሠ. አረጋዊው

ረ. የነተበ

ሰ. የእድሜዬ ጀምበር እየጠለቀ

## ክፍል ኹለት፡- መናገር

፩. በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ በጋራ የደረሳችሁበትን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል ተናገሩ፡፡

1. በልቦለዱ የትልም ሁኔታ ላይ ያላችሁን አስተያየት በቡድን በመወያየት ለጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

2. ያዳመጣችሁትን ልቦለድ ታሪክ እንደገና በራሳችሁ አገላለጽ ለጓደኞቻችሁ ተርኩላቸው፡፡

3. የልቦለዱን ጭብጥ በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ በተወካያችሁ አማካይነት ለጓደኞቻችሁ ግለጹላቸው፡፡

## ክፍል ሦስት፡- ንባብ

# "… አሁን አምኛታለሁ"

### ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

፩. ከዚህ በታች "… አሁን አምኛታለሁ" በሚል ርዕስ አጭር ልቦለድ ቀርቦላችኋል፡፡ ከርዕሱ በመነሳት ልቦለዱ ስለምን እንደሚያወሳ በቡድን ተወያይታችሁ መልሶቻችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሯቸው፡፡

፪. ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላትና ሀረጋት ተቃራኒ ፍች ስጡ፡፡

ሀ. ሲብሰከሰክ

ለ. በደመነፍስ

ሐ. ተጀቡና

መ. ብላቴና

ሠ. ዋልጌ

ረ. የሞት አበጋዝ

ሰ. ውለታ ቢስ

ሸ. ድሪቶ

# "… አሁን አምኛታለሁ"

እጇ ወደ ኋላ ከጎጆው ምሶሶ ጋር ታስሮ እርቃኗን ተቀምጣለች፡፡ ግርማ ትልቅ ቢላ በእጁ ጨብጦ ከፊት ለፊቷ እንደ ጅብራ ተገትሯል፡፡ በጉልበቷ ልትሸፍን የምትሞክረውን ሀፍረቷንና የገፋ ሆዷን በእልህ እየተመለከተ በንዴት ቀረባት፡፡ ሁለመናዋ ያስፈራል፡፡ … የሚቁለጨለጩ ዓይኖቿና የሚጉረጠረጡ ዓይኖቹ እኩል ያነባሉ… በርከክ ብሎ በቢላው ጫፍ ጉንጯ ላይ የሚንከባለለውን የዕንባ ዘለላ ለመገደብ ሞከረና ሳግ አፍኖት ዓይኑን ጨፈነ፡፡

"እመነኝ ግርምሽ…፣ ልቤ ዛሬም ካንተ ጋር ነው"
ትክ ብሎ አያትና "ልብሽ ቆሽሿል…፡፡ ዓይኖችሽና ምላስሽ እኩል ይዋሻሉ"

"እመነኝ…"

"ዝጊ …" ብሎ በመጮህ አራስ ነብር ሆነባት፡፡ በርግጋ ዝም አለች

"የገደልሽው ልጄና ከማንም የደቀልሽው ጽንስ …" ቃላት አጠረውና ተነስቶ ከቤቱ ወጣ፡፡ ደጅ መደብ ላይ ተቀምጦ ስቅስቅ ብሎ አነባ፡፡ "ፈጣሪዬ ምን በደልኩህ?" አለ ጉንጮቹን ጥብቅ አድርጎ እየያዘ፡፡

በጦር ግንባር ሳለ ከማንም በላይ ትናፍቀው የነበረችው እሷ ነበረች፡፡ በትዝታ ሲብሰከሰክ ለጠላት ተኩስ በተደጋጋሚ ተጋልጧል፡፡ ጓደኞቹ ወደ ከተማ እየሄዱ በሚደሰቱበት የዕረፍት ጊዜያቸው እሱ ከፎቶዋ ጋር ሲጫወት ያመሻል፡፡ በነኛ ስድስት ዓመታት የቀን ከሌት ጸሎቱ በሰላም ተመልሶ ከእርሷ ጋር መኖር ነበር፡፡ ሁኔታዎቹ የተገላቢጦሽ ሆኑበት፡፡ እጁን ያጣለት ልጁ በአውሬ መበላቱ ተነገረው፡፡ ያ ቀፋፊ የመጨረሻው የውጊያ ውሎ ታወሰው፡፡

ጠላት ወሮ በመሸገበት አነስተኛ ከተማ እየተዋጉ ነበር፡፡ ብዙ ጓዶቹ የተሰውበት መራር ጦርነት ስለሆነ ማፈግፈግ ተገደዱ፡፡ በዚህ ውስጥ ነበር በእሳት ተያይዞ እየፈረሰ ካለ ቤት ውስጥ የህጻን ጩኸት የሰማው፡፡ በደመነፍስ ሮጠ፡፡ በርግጥ አቅፎት ከእሳቱ ሲወጣ ሁሉ የራሱ ልጅ መስሎት ነበር፡፡ የወገን ጦር አፈግፍጎ ስለነበር ልጁን ታቅፎ እየሸሸ ያካሄደው ጦርነት ለዘላለም ሰቀቀን ሆኖት ቀርቷል፡፡ በህጻኑ ደረት ዘልቆ እጁን የመታው ጥይት …. በቃ ሁሉን ነገር ደመደመው፡፡

ግርማ በልጁ ምክንያት ሆዱ ሲባባ ከርሟል፡፡ ስለህጻኑ በእጁ ላይ መሞት አምላኩን ሊወቅስ ሁሉ ዳድቷል፡፡ ቀኝ እጁን አጥቶ ከጦር ሰራዊቱ ሲቀነስም ሀዘኑ አብሮት ነበር፡፡ ያ ሰቀቀን በሚስቱ እቅፍ፣ በልጁ ደስታ አልተሻረም፡፡

"የትም ስትማግጥ ልጇን ላውሬ ሰጠችው" ለራሱ ነበር ያወራው፡፡ ሚስቱ ልጁን ቀብራለት… የስምንት ወር ነፍሰ ጡር ናት… የራሷን አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ጀምራለች…፡፡

ቀዬው ሲደርስ እሱ ባሰበው ደስታ አልተቀበለችውም፡፡ ገና ስታየው ጮኻ ራሷን ሳተች፡፡ ልቡ ተሰብሮ … በሁሉ አቂሞ ነበር፡፡

እየተብሰከሰከ ሁለት ሳምንታት አሳልፏል፡፡ ያቀረበችለትን አልበላም … የነገረችውንም አላመነም … አንድም ቃል አልተነፈሰም፡፡ እንኳን ደህና መጣህ ሲሉትና የልጁንም ሞት ሊደርሱት የመጡትን ሁሉ በዝምታ ሸኛቸው፡፡ እጁን ስላጣለት ህጻን ፈጣሪ የእርሱን ብላቴና ሊጠብቅለት ይገባ ነበር ብሎ አምኗል፡፡ ደሙን የገበረለት ሕዝብ ሚስቱንና ልጁን ሊንከባከብ ይገባ ነበር፡፡ ቀን ከሌት ሀሳቡ የነበረች ሚስቱ ራሷንና ልጇን ልትጠብቅ ግዴታዋ ነበር፡፡ ሟች ልጁም ቢሆን ስላባቱ ናፍቆት ራሱን ከሞት መከላከል ነበረበት፡፡ ድቅድቅ ጨለማው ላይ አፍጥጦ እንባውን ጠረገ ፡፡ ለምን ነበር የመትረየስ ጥይት እጁን የመታው? ትዝ አለው…. ያ ዓይኑ ላይ ተስሎ ግርማ ከሁሉ ተጣልቶ….. ሁሉን ዘንግቶ ከረመ፡፡ የሚስቱ እንባ እየቀፈፈው ሁለት ሳምንት የናፈቀው ገላዋን ሳይጠጋ ቆየ፡፡ ዛሬ ግን ቢያንስ የሚችለውን ሊበቀል ስለት አነሳ፡፡

### የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

ተማሪዎች ንባባችሁን ገታ አድርጋችሁ ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ምላሽ ስጡ፡

1. እስካሁን ባነበባችሁት የልቦለዱ ክፍል ተሳታፊ ገጸ ባህርያት እነማን ናቸው?
2. ቀጥሎ በሚቀርበው የልቦለድ ክፍል ምን የሚፈጠር ይመስላችኋል?

አያል እንደነገሩ ያሰረውን እጇን ካላቀቀች በኋላ ግራ ገብቷት ቆመች፡፡ ዕርቃኗን መሸፈን አላሰኛትም … ሸሽታ ማምለጥም አልፈለገች፡፡ "እሪ!" ብላ ብትጮኽ

ትወድ ነበር … መፍትሔ ግን አልመሰላትም፡፡

ባሏን ትወደዋለች… ስድስት ዓመት ሙሉ ራሷን በንጽህና ለማቆየት ከስንቱ ዋልጌ ጋር ታግላለች፡፡ የሚልክላትን ደብዳቤ እየመላለሰች ሃምሳ ጊዜ በማንበብ ፍቅርና ናፍቆቷን ስትጠብቅ ኖራለች፡፡

ልጅሽን አልተንከባከብሽም የሚላት ማንም የለም… የባሏን ምትክ ከማንም በላይ አንቀባራ አሳድጋዋለች… ትምህርት ቤት ልትልከው ሁሉ ወስና ነበር… ሰውነቱ መንገዱን መቋቋም እስኪችል ቤት ውስጥ ፊደል ስታስጠናው ቆይታለች፡፡ ላባቱ በራሱ እጅ ነበር ደብዳቤ የሚጽፈው … ለእርሱ የተጻፈውን የሚያነበው ራሱ ነበር፡፡ ግን ምን ያደርጋል …

ያን ክፉ ቀን አትረሳውም፡፡ የዛሬ ስምንት ወር ገደማ ከገበያ ስትመለስ ልጇን አጣችው፡፡ ከአካባቢ ልጆች ጋር ሊጫወት ሄዷል ተባለች፡፡ ዓይኗ ደጅ ደጁን እያየ መጨለም ጀመረ፡፡ ኋላም ልጆቹ ተደናግጠው እየተንጫጩ መጡ፡፡ ልጇን አውሬ እንደበላው አረዷት፡፡ ከማንም ቀድማ ነጠላዋን ጥላ በረረች፡፡ እየጮኸች ወዲያ ወዲህ በረረች፡፡ በርቀት እያየች ጥቅጥቅ ወዳለው ጫካ በድፍረት ገባች… ሁለት ጎረምሶች ጫካው መሃል አፍነው አስቀሯት … ታገለች … አልቻለችም … ደፈሯት፡፡ እየተፈራረቁም አደከሟት፡፡ ጎረቤቶቿ ፋና ይዘው ሲደርሱ ልብሷ ተገልቦ ካንዱ ዛፍ ስር ወድቃ ነበር፡፡ እሷን ተሸክመው ወደውስጥ ሲዘልቁ የልጁን አካል ተበታትኖ አገኙት፡፡ ፍቅሯ ግን አላመናትም… ዕንባዋን እንዳዘ ዕንባ ቆጥሮባታል… ያ ፍልቅልቅ ፊቱ ተጫዋች አንደበቱ ታስሯል፡፡

ነገን ስታየው ጨለመባት እናም ሞቷን ናፈቀች፡፡ የጸነሰችውን ጠልታ … በባሏ ተጠልታ … በባነነ ቁጥር ስለት እያነሳባት የምትኖረው ኑሮ ከበዳት፡፡

እንደተገተረች ፈገግ ለማለት ሞከረች፡፡ እጇ የታሰረበት ገመድ በእጇ ነው፡፡ የልጇን እርሳስና ደብተር አንስታ ሞነጫጨረችና ቀና ብላ ምሰሶውን ተመለከተችው፡፡

ግርማ መወሰን ከብዶታል፡፡ የልቡ ገዳይ በቤቱ ምሰሶ ስር በሀሰት ተጀቡና ትጠብቀዋለች፡፡ አወጣ አወረደ … ነገ ከዛሬ በላይ መራር ሆኖ ታየው፡፡ በዚህ ውስታ ቢስ ዓለም አንዳች ጣዕም እንደሌለ ገባው፡፡ በጨለማ ውስጥ ብለጭ እያሉ የሚያስፈራሩትን የሞት አበጋዞች ሸሽቶ ወደቤት ገባ፡፡

ተንገዳገዶ ቆመ፡፡ የአያል ርቃን በድን ምሰሶው ላይ ተንጠልጥሎ አፍጥጦበታል፡፡ በድን ሰውነቱ ለምንም አልታዘዝ አለው፡፡ ከመሬት ላይ የወደቀችውን ብጣሽ ወረቀት አነበባት…

> "ስለአንተና ስለልጄ ኖሬያለሁ… ልጄና አንተን አጥቻለሁ… በዕንባዬ ያላመንከኝን እውነት በሞቴ ተጋፈጠው… ጨካኝ አውሬ" እየበረረ ወጣ፡፡

አሁን ስለአያል አያውቅም፡፡ ቸርችል ጎዳና ላይ ድሪቶውን ተጀቧቡኖ ጥንድ ወጣቶች ሲያይ እየሮጠ ከፊታቸው ይገተራል፡፡ሴቶቹ ሁል ጊዜ ይበረግጋሉ፡፡ አፍጥጦ ያያቸውና ወንዱን እየጠቆመ "ጨካኝ … አውሬ አይደለም እሺ…" ይላል፡፡ ወደወንዱ ይዞርና "እውነቷን ነው እሺ … እመናት" ይለዋል፡፡ ከዚያም እንደቆሙ ጥሏቸው ቁርጥራጭ ሲጋራ እየለቃቀመ "እኔ ግን አሁን አምኛታለሁ" ይላል፡፡

(ምንጭ፡- የኢፌዴሪ ባህልና ቱሪዝም ሚኒስቴር መሰረታዊ የስነጽሑፍ ማሰልጠኛ ሞጁል (2008) ገጽ 56-59 ላይ የተወሰደ)

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

፩. ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ መልሳችሁን በቡድን ተወካዮቻችሁ አማካይነት በቃል ግለጹ፡፡

1. በታሪኩ ውስጥ የተገለጹትን ገጸ ባህርያት ለይታችሁ አውጡ፡፡
2. ግርማ ለልጁ ሞት እና ከሌላ ወንድ ለመፀነሷ አያልን ተጠያቂ ማድረጉ ተገቢ ነው ብላችሁ ታምናላችሁ? ለምን?
3. አያል ራሷን ማጥፋቷ ተገቢ ነው ትላላችሁ? እናንተ አያልን ብትሆኑ ኖሮ ምን ታደርጉ ነበር?
4. የልቦለዱን ጭብጥ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለጹ፡፡
5. ባጠቃላይ በልቦለዱ ላይ ያላችሁን አመለካከት ግለጹ፡፡

፬. በምንባቡ ውስጥ የተጠቀሱትን ዘይቤያዊ አነጋገሮች ለይታችሁ ካወጣችሁ በኋላ በልቦለዱ ውስጥ ያላቸውን ተግባር ግለጹ፡፡

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

፩. "... አሁን አምኛታለሁ" የሚለውን አጭር ልቦለድ በድጋሚ ካነበባችሁ በኋላ ጭብጡንና የትልም አወቃቀሩን ማስረጃዎችን በመጥቀስ ተንትናችሁ ጻፉ፡፡

፬. የአጭር ልቦለድን ምንነት፣ ባህርያት እና አላባውያንን በተመለከተ የቀረበውን ማስታወሻ መነሻ በማድረግ አንድ አጭር ልቦለድ ጻፉ፡፡

### የአጭር ልቦለድ ባህርያትና አላባውያን

ልቦለድ ደራሲው እውነተኛውን አለም መነሻ በማድረግ ምናባዊ ፈጠራውን ተጠቅሞ የሰውን ልጅ አጠቃላይ ማህበራዊና ግላዊ፣ ቁሳዊና መንፈሳዊ ገጽታዎች የሚያሳይበት የስነጽሑፍ ዘር ነው፡፡ ልቦለድ አጭር እና ረጅም ተብሎ በሁለት ይከፈላል፡፡

### የአጭር ልቦለድ ባህርያት

አጭር ልቦለድ ሰብሰብ ያለ ወይም የታመቀ፣ ጠባቃ ትስስር ያለው፣ ፈጣንነት ጎልቶ የሚታይበትና የሁሉም ነገር መቋጫ የሆነ ብቸኛ የትኩረት ነጥብ ያለው የልቦለድ ዓይነት ነው፡፡ ከአጭር ልቦለድ ባህርያት ውስጥ የሚከተሉት ይጠቀሳሉ፡፡

**ሀ. ነጠላ ውጤት፡-** ሁሉም የአጭር ልቦለድ አላባውያን ተሳስረው ወደአንድ ዋነኛ ትኩረት የሚፈሱበትና ደራሲው በአንባቢው አእምሮ ተቀርጾ እንዲቀር የሚፈልገው አንድ ኪነጥበባዊ ግብ ነው፡፡

ለ. **ጥድፊያ፡-** የሚተረከው ታሪክ ብዙ ሳይጠማዘዝ ቶሎ ቶሎ በመተረክ፣ ትልሙና የተለያዩ ክፍሎች ፍሰታቸውን ጠብቀው ዝርዝር ነገር ሳያበዙ፣ የተስፋፋ የመቼት ገለጻና የገጸ ባሕርይ ዳራ ሳይሰጥ በፍጥነት መጓዝ ነው፡፡

ሐ. **ቁጥብነት፡-** በዋናነት በአጭር ልቦለድ አላባውያንና አኗኗር እርስ በእርስ በሚፈጥሩት አይቀሬ ቅንጅት ውስጥ የሚታይ ነው፡፡ ምሳሌ -የአጭር ልቦለድ ታሪክ የአንድን ገጸ ባህሪ ታሪክ ከልደት እስከሞት የሚተርክ ሳይሆን በአንድ ዋና ገጸ ባህሪ ላይ በማተኮር የሱን ህይወት አንድ ዘለላ በመምረጥ ሌሎችንም አላባውያን በዚሁ ዙሪያ በማጠንጠን ያቀርባል፡፡

## ልቦለድ አላባውያን

ሀ. **ታሪክ፡-** በጊዜ ቅደም ተከተል የተቀናጁ የሁነቶች ትረካ ነው፡፡

ለ. **ገፀባህሪያት፡-** በልቦለዱ ጽሁፍ ውስጥ ደራሲው የሚፈጥራቸው የገሃዱን አለም ሰዎች የሚወክሉ የልቦለድ አለም ሰዎች ናቸው፡፡

ሐ. **መቼት፡-** መቼ እና የት ከሚሉ ሁለት ቃላት የተገነባ ነው፡፡ በልቦለዱ ዉስጥ የተሳሉት ገጸባህሪያት የሚኖሩበት፣ ታሪካቸውን የሚፈጽሙበት ቦታ እና ጊዜ ነው፡፡

መ. **ግጭት፡-** በልቦለዱ ዓለም የሚኖሩ ገጸባህሪያት በታሪኩ ውስጥ በተፈጠረላቸው የእርስ በእርሳዊ ግንኙነት የተነሳ በተለያዩ ምክንያቶች ቅራኔዎች ወይም አለመግባባቶች ሲከሰቱ አንዱ ገጸባህሪ ከሌላዉ ገጸባህሪ ጋር የሚፈጥረው ንትርክ፣ ገጸባህሪያቱ ይህን ልፈጽም ወይም አልፈጽም በሚል ሁኔታ ከራሳቸው ጋር የሚፈጠር ፍጭት (ፍልሚያ) ነው፡፡

ሠ. **ትልም፡-** በልቦለድ ውስጥ በምክንያት እና ውጤት የተሰናሰሉ ሁነቶች እና ድርጊቶች ቅደም ተከተላዊ ትረካ ነው፡፡

ረ. **ጭብጥ፡-** ከአጠቃላዩ የልቦለዱ ታሪክ ተጨምቆ ወይም ተፈልቅቆ የሚወጣ መልዕክት (ቁምነገር) ነው፡፡

ሰ. **አንፃር፡-** ደራሲው ታሪኩን የሚያቀርብበት የትረካ አቅጣጫ ነው፡፡

(ምንጭ፡- ዘሪሁን አስፋው (2005) የስነጽሁፍ መሰረታውያን)

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

ከዚህ በታች ከምንባቡ በተወሰዱ ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ ከስራቸው ለተሰመረባቸው ቃላት ዐውዳዊ ፍቻቸውን ጻፉ፡፡

ሀ. ደጅ መደብ ላይ ተቀምጦ ስቅስቅ ብሎ አነባ፡፡

ለ. ብዙ ጓዶች የተሰውበት መራራ ጦርነት ስለነበረ ማፈግፈግ ተገደዱ፡፡

ሐ. ግርማ በልጁ ምክንያት ሲባባ ከርሟል፡፡

መ. ስለህፃኑ በእጁ ላይ መሞት አምላኩን ሊወቅስ ዳድቷል፡፡

ሠ. ቀየው ሲደርስ እሱ ባሰበው ደስታ አለተቀበለችውም፡፡

ረ. የባሏን ምትክ ከማንም በላይ አንቀባራ አሳድጋዋለች፡፡

ሰ. ጎረቤቶቿ ፋና ይዘው ሲደርሱ…፡፡

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

### የሀረግ ዓይነቶች

ሀረግ ቃላት ተቀናጅተው የሚፈጥሩት ስሬ መዋቅር ነው፡፡ የሀረግ መሰረት ቃላት ናቸው፡፡ የሀረጋቱ ዓይነት ሀረጉን በሚመሰርቱት የቃላት ዓይነት ይወሰናል፡፡ በዚህም መሰረት በአማርኛ ቋንቋ ውስጥ የሚገኙት የቃል ክፍሎችና የሚመሰሩት የሀረግ ዓይነቶች በሚከተለው ሰንጠረዥ ላይ ቀርበዋል፡፡

| ተ.ቁ. | የቃል ክፍሎች | የሀረግ ዓይነቶች |
|---|---|---|
| 1 | ስም | ስማዊ ሀረግ |
| 2 | ግስ | ግሳዊ ሀረግ |
| 3 | ቅጽል | ቅጽላዊ ሀረግ |
| 4 | ተውሳከ ግስ | ተውሳከ ግሳዊ ሀረግ |
| 5 | መስተዋድድ | መስተዋድዳዊ ሀረግ |

**ሰማዊ ሀረግ፡-** ከስም የሚመሰረት የሀረግ ዓይነት ነው፡፡በስማዊ ሀረግ ውስጥ መሪው ቃል ስም ነው፡፡
ምሳሌ፡- ታታሪው ልጅ

**ግሳዊ ሀረግ፡-** ግስን መሰረት አድርጎ የሚመሰረት የሀረግ ዓይነት ነው፡፡ በግሳዊ ሀረግ ውስጥ መሪው ቃል ግስ ነው፡፡

ምሳሌ፡- በፍጥነት መጣች

**ቅጽላዊ ሀረግ፡-** ቅጽልን መሰረት አድርጎ የሚመሰረት የሀረግ ዓይነት ነው፡፡ በቅጽላዊ ሀረግ ውስጥ መሪው ቃል ቅጽል ነው፡፡

ምሳሌ፡- በጣም ደግ

**ተውሳከ ግሳዊ ሀረግ፡-** ተውሳከ ግስን መሰረት አድርጎ የሚመሰረት የሀረግ ዓይነት ነው፡፡ በተውሳከ ግሳዊ ሀረግ ውስጥ መሪው ቃል ተውሳከ ግስ ነው፡፡
ምሳሌ፡- በጣም ክፉኛ

**መስተዋድዳዊ ሀረግ፡-** መስተዋድድን መሰረት አድርጎ የሚመሰረት የሀረግ ዓይነት ነው፡፡ በመስተዋድዳዊ ሀረግ ውስጥ መሪው ቃል መስተዋድድ ነው፡፡ ምሳሌ፡- በመኪና

(ምንጭ፡- ጌታሁን አማረ (1989) ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው)

፩. በሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸው ሀረጋት ከየትኛው የሀረግ ዓይነት ውስጥ እንደሚመደቡ ግለጹ፡፡

፩.፩. ስኬት <u>የአንድ ቀን ክስተት</u> አይደለም፡፡

፩.፪. ቃላት <u>በሥርዓት</u> ተዋቅረው ሀረጋትን ይመሰርታሉ፡፡

፩.፫. የጽሕፈት ቤቱ ሰራተኛ <u>ሥራውን በተመደበለት ሰዓት አጠናቀቀ</u>፡፡

፩.፬. <u>በጣም ብልህ</u> ልጅ ናት፡፡

፩.፭. <u>ክፉኛ</u> ስለታመመ ወደሆስፒታል ወሰዱት፡፡

፪. የሚከተሉትን ቃላት የሀረጉ መሪ በማድረግ ሀረግ መስርቱ፡፡ የመሰረታችኋቸውን ሀረጋት ዓይነትም ግለጹ፡፡

፪.፩. ጥናት

፪.፪. አጎለበተ

፪.፫. ውድቀት

፪.፬. እንደ

፪.፭. ክፉኛ

፫. የሚከተሉትን ሀረጋት በመጠቀም የተሟላ ዐረፍተ ነገር መስርቱ፡፡

፫.፩. በፍጥነት

፫.፪. በቤተ-መጽሐፍ ውስጥ

፫.፫. በጣም ትሁት

፫.፬. ተግተው የሚያጠኑ ተማሪዎች

፫.፭. ብልህ ልጅ

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

ምዕራፍ አራት "ልቦለድ" በሚል ርዕስ የቀረበ ሲሆን፣ በውስጡም የተለያዩ ይዘቶች ተካተውበታል። በምዕራፉ ውስጥ አጭር ልቦለድን አዳምጣችሁና አንብባችሁ የአድምጦ መረዳት እና የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ሠርታችኋል። የቃላትንና የሀረጋትን ተመሳሳይና ተቃራኒ ፍችም ተምራችኋል።

በምዕራፉ ውስጥ የአጭር ልቦለድ ምንነት፣ ባህርያት እና አላባውያን ቀርበዋል። የአጭር ልቦለድ ባህርያት ነጠላ ውጤት፣ ጥድፊያ እና ቁጥብነት መሆናቸውን፣ የልቦለድ አላባውያን ደግሞ ታሪክ፣ ገጸ ባህርይ፣ መቼት፣ ግጭት፣ትልም፣ ጭብጥ፣ አንጻር እንደሆኑ ተምራችኋል።

በሰዋስው ክፍል የሀረግ ዓይነቶችን ተምራችኋል። ሀረግ ቃላት ተቀናጅተው የሚፈጥሩት ሰፊ መዋቅር ነው። የሀረግ ዓይነት የሚወሰነው ሀረጉን በሚመሰርተው የቃል ዓይነት ነው። በዚህም መሠረት ከስም ስማዊ ሀረግ፣ ከግስ ግሳዊ ሀረግ፣ ከቅጽል ቅጽላዊ ሀረግ፣ ከተውሳከ ግስ ተውሳከ ግሳዊ ሀረግ እና ከመስተዋድድ ደግሞ መስተዋድዳዊ ሀረግ ሊመሰረት እንደሚችል ተምራችኋል።

## የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

፩. የአጭር ልቦለድን ባህርያት ከገለጻችሁ በኋላ ለእያንዳንዱ ማብራሪያ ስጡ።

፪. በሚከተለው ስዕላዊ መግለጫ ውስጥ ባሉት ቦታዎች ላይ የአጭር ልቦለድን አላባውያን ጻፉ።

፫. የሚከተሉት ሀረጋት ከየትኛው የሀረግ ዓይነት ሊመደቡ እንደሚችሉ ግለጹ።

ሀ. ታላላቆቹን አከበረ

ለ. ሰፋፊ ሜዳዎች

ሐ. በትምህርት ቤት

# የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ አራት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ቅጽ ቀርቦላችኋል፡፡ በዚህም መሠረት በእያንዳንዱ ማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ቅጹን አሟሉ፡፡

| ተ.ቁ. | የማመሳከሪያ ነጥቦች | √ | ? | X |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ካዳመጥኩት ልቦለድ የታሪኩን ትልም፣ መቼት፣ ገጸባህርያት መለየት ችያለሁ | | | |
| 2 | ያነበብኩትን ምንባብ ዋና ገጸባህርይ መለየት ችያለሁ | | | |
| 3 | የልቦለዱን ታሪክ በራሴ አገላለጽ መተረክ ችያለሁ፡፡ | | | |
| 4 | አጭር ልቦለድ መጻፍ ችያለሁ | | | |
| 5 | ከምንባቡ ውስጥ ዘይቤያዊ አነጋገሮችን መለየት ችያለሁ | | | |
| 6 | የቃላትንና የሀረጋትን ተመሳሳይ ፍቾ መግለጽ ችያለሁ | | | |
| 7 | የቃላትንና የሀረጋትን ተቃራኒ ፍቾ መግለጽ ችያለሁ | | | |
| 8 | የሀረግ ዓይነቶችን መለየትና መመስረት ችያለሁ | | | |

፪. ከዚህ በላይ በቀረበው ቅጽ የ(?) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትገነዘቡ ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

አማርኛ

(፱ኛ) ክፍል

# ምዕራፍ አምስት፡- ቃላዊ ስነጽሑፍ

**የምዕራፉ ዓላማዎች፡-**

ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፣

- የቃላዊ ስነጽሑፍን ጽንሰ ሃሳብ ትተነትናላችሁ፡፡
- የቃላዊ ስነጽሑፍን ባህርያት በመለየት ትገልጻላችሁ፡፡
- የስነቃል ዘርፎችን (ዘውጎችን) ትዘረዝራላችሁ፡፡
- ለቃላዊ ስነጽሑፍ ዓይነቶች ብያኔ ትሰጣላችሁ፡፡
- የቃላዊ ስነጽሑፍ ጭብጥ ትገልጻላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

## ዶሮና ጭልፊት

### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

ከዚህ በታች በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ የቡድናችሁን ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለጹ፡፡

ሀ. ዶሮ በሰማይ የማትበረው ለምን ይመስላችኋል?

ለ. ዶሮ መሬት የምትጭረው ለምንድን ነው?

ሐ. "ዶሮና ጭልፊት" በሚል ርዕስ የሚቀርበው ታሪክ ይዘት ምን ይመስላችኋል?

### የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

ሀ. በታሪኩ መሠረት ጭልፊት መብረር የቻለችው በምን ምክንያት ነው?

ለ. ዶሮ ወደጭልፊት ሳትሄድ ብዙ ቀናትን ያሳለፈችው ለምንድን ነው?

ሐ. ዶሮ የጭልፊትን መርፌ የምታገኝ ይመስላችኋል?

### የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ታሪክ መነሻነት ጥንድ ጥንድ በመሆን ከተወያያችሁ በኋላ መልሳችሁን በጽሁፍ አስፍሩ፡፡

1. የታሪኩ ተሳታፊዎች እነማን ናቸው?
2. "ራቴም ምሳዬም መርፌው ነበር፡፡" ያለው ማነው? ይህን ያለውስ ለምንድን ነው?

3. በታሪኩ መሠረት ዶሮ መሬት የምትጭረው ለምንድ ነው?

4. ጭልፊት የዶሮን ጫጩት ስትነጥቅ የምትታየው ለምንድ ነው?

5. ያደመጣችሁት ታሪክ ደራሲ ይታወቃል? መልሳችሁ "ይታወቃል" ከሆነ ደራሲው ማነው? "አይታወቅም" ከሆነ ለምን?

6. ያዳመጣችሁት ምንባብ ከየትኛው የስነቃል ዓይነት ይመደባል?

7. ከታሪኩ ምን ተረዳችሁ?

## ክፍል ኹለት፡- መናገር

፩. በጥንድ በመሆን በማዳመጥ ክፍል የሰማችሁትን ታሪክ መሠረት በማድረግ በሚከተሉት ጥያቄዎችን ላይ በቡድን ከ 3-5 በመሆን ተወያዩባቸው፡፡ የቡድናችሁንም ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል ተናገሩ፡፡

ሀ. የምታውቁትን ተረት ለቡድን አባሎቻችሁ ተናገሩ፡፡

ለ. በተናገራችሁት ተረት ውስጥ የተሳተፉትን አባላት ዘርዝሩ፡፡

ሐ. የተረቱን መልዕክት ግለጹ፡፡

፪. በጥንድ በመሆን የሚከተሉትን ምሳሌዎች መሠረት በማድረግ ከራሳችሁ አምስት እንቆቅልሾችን በመጻፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

ምሳሌ-

ሀ፡- ጠያቂ --- እንቆቅልህ/ሽ

ተጠያቂ --- ምን አውቅልህ/ሽ?

ጠያቂ --- ለማታምነው ፊቷ ምራቅ ነው ቅባቷ

ተጠያቂ --- ድመት

ጠያቂ --- አውቀህዋል/ሽዋል

ምሳሌ-

ለ፦ ጠያቂ --- እንቆቅልህ/ሽ

ተጠያቂ --- ምን አውቅልህ/ሽ?

ጠያቂ --- እትዬ ሰፊፏ እየተንሳፈፉ መልካም ሰፊድ ሰፉ

ተጠያቂ --- ንብ

ጠያቂ --- አውቀህዋል/ሽዋል

ምሳሌ-

ሐ፦ ጠያቂ --- እንቆቅልህ/ሽ

ተጠያቂ --- ምን አውቅልህ/ሽ?

ጠያቂ --- ባለ ካባ ባለጭራ የተከበረ ደብተራ

ተጠያቂ --- ንጉስ

ጠያቂ --- አላወከውም

ተጠያቂ --- ሀገር ስጠኝ

ተጠያቂ --- (ተጠያቂ ሀገር ይሰጠዋል)

ጠያቂ --- ዋለብህ

አደረብህ

እንደ ሰርዶ ነፈሰብህ

እንዳልሰድብህ ወንድሜ ነህ

እንዳልተውህ ጠላቴ ነህ

ከቤትህ በታች ያለው ልምጭ

እንዳንተው ነጭ

ከዚህ እስከ ይፋት

ያብርህ እንቅፋት

ምርት ምርቱን ለራሴ

ግርድ ግርዱን ለፈረሴ

በአንተ ጉሮሮ አጥንት ይሰንቀር

በኔ ጉሮሮ ጠጅ ይንቆርቆር

ይብቃህ ወይስ ልጨምርልህ

ተጠያቂ --- ኧረ በቃኝ

ጠያቂ --- የበቆሎ እሸት

## ክፍል ሦስት፡- ንባብ

## የስነቃል ምንነትና ባህርያት

### ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

ከዚህ በታች በቀረቡት የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ላይ በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ መልሳችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለጹ፡፡

፩. ስነቃል ምንድን ነው?

፪. ስነቃል ለማኅበረሰቡ ምን ምን ጠቀሜታ ሊኖረው ይችላል?

፫. ከዚህ በታች “የስነቃል ምንነትና ባህርያት” በሚል ርዕስ ምንባብ ቀርቦላችኋል፡፡ የስነቃል ባህርያት ምን ምን ሊሆኑ ይችላሉ?

## የስነቃል ምንነትና ባህርያት

ስነቃል በመነገር፣ በመተረት ወይም በመዜም በተወሰኑ ማህበራዊ አጋጣሚዎች ላይ የሚከወን ቃላዊ ፈጠራ ሲሆን የአንድን ማህበረሰብ ባህል፣ ወግና ልማድ፣ እንዲሁም ታሪክ ማስተላለፊያና ልዩ ልዩ ክስተቶችንና የህይወት መልኮችን መግለጫ ኪነጥበብ ነው። ይህ ኪነጥበብ ማህበረሰቦች በረጅም ዘመን ታሪካቸው ያጠራቀሙትና የሚያጠራቅሙት ቅርስ ከመሆኑም በላይ ለህልውናቸው ሲሉ በሚያደርጓቸው እንቅስቃሴዎች ምክንያት የሚከሰት ከአካባቢያቸውና ከተፈጥሯቸው ጋር ካላቸው መስተጋብርና ትግል የሚፈጠር የአያሌ ገጠመኞች ጥርቅምና የገጠመኞቹም ማንጸባረቂያ ነው። ይህ ቃላዊ ኪነጥበብ በተለይ ፊደል ቀርጸው በጽሁፍ በማይገለገሉ ማህበረሰቦች ዘንድ ማንነትንና ምንነትን፣ እምነትን፣ የኑሮ ዘይቤንና ፍልስፍናን፣ አጠቃላይ የዓለም አመለካከትን ቀርጾ ለተተኪው ትውልድ በማስተላለፍ ረገድ የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው።

በስነቃል ህዝቦች ማንነታቸውን ያሳውቁበታል፣ የዘርያቸውን አመጣጥ ይተርኩበታል፤ ስለአካባቢያቸውና በአጠቃላይ ስለዓለማቸው ያላቸውን ፍልስፍና ይቀርጹበታል። ወግና ልማዳቸውን አጠንክረው የሚያቆዩበት ዋነኛ መሳሪያቸውም ነው። ሀዘን ደስታቸውን፣ ምኞት ተስፋቸውን፣ ፍቅር ጥላቻቸውን፣ ድል ሽንፈታቸውን፣ ድጋፍ ተቃውሚቸውን በአጠቃላይ የህይወታቸውን መልኮች ያንጸባርቁበታል። ታሪካቸውን ለተከታዮቻቸው በማስተላለፍ የዘርያቸውን ተከታታይነት ያረጋግጡበታል። ሰናይ የሚሏቸው ማህበራዊ እሴቶችና ልማዶች ተጠብቀውና ተከብረው እንዲቆዩ፣ እኩይ የሚሏቸው ደግሞ እንዲወገዱ ያደርጉበታል። በአንድ ማህበረሰብ ላይ የደረሱ አስከፊ ሁኔታዎች የተፈጥሮ አደጋ፣ ስደት፣ ረሀብ፣ ወረርሽኝ፣ ጦርነት የመሳሰሉት ኑሮን አናጊ አጋጣሚዎች የነበረው አመለካከትና የደረሰበት ጉዳት በስነቃሉ አማካይነት ተቀርጾ ለተከታዩ ትውልድ ይተላለፋል።

የስነቃል ምንጭ የማህበረሰቡ ልዩ ልዩ ገጠመኞች ናቸው። በተለይ ከጥንታዊ የአኗኗር ዘይቤ ብዙ ባልራቁና ባልበለጸጉ ማህበረሰቦች በእለት ተእለት ህይወታቸው ውስጥ በሚከሰቱ የተለያዩ ግንኙነቶች ምክንያት አያሌ ስነቃሎች ይቀርባሉ።

በተለያዩ ማህበራዊ አጋጣሚዎች በየወቅቱና በየዘመናቱ የሚነገሩት ተረቶች፣ በአምልኮ ስነስርዓቶች ላይ የሚደረደሩት ውዳሴ አማልክትና ዝማሬዎች፣ በእርሻ፣ በአረም፣ በአጨዳና በውቂያ በሌሎችም መሰል ህይወት ደጋፊ ስራዎች ላይ

የሚዜሙና የሚነገሩ ስነቃሎች፣ በከብት ስምሪት ጊዜ የሚባሉ እንጉርጉሮዎች፣ በቀብር ስነስርዓትና ሀዘን ላይ የሚደረደሩ የሙሾ ግጥሞች፣ በክብረ በዓላት፣ በሰርግ፣ በልጆች ጨዋታ የሚዘፈኑ ባህላዊ ዘፈኖች፣ በደቦ፣ በእድር፣ በእቁብና በመሳሰሉት አጋጣሚዎች ላይ የሚሰነዘሩ ምሳሌያዊ አነጋገሮች፣ ሰዎች በሚገኙባቸው አጋጣሚዎች የሚነገሩ ወጎች፣ ቀልዶች፣ ለማህበረሰቡ ጀግኖች እና ተደናቂ ግለሰቦች የሚነገሩ ግጥሞችና አፈታሪኮች፣ እንዲሁም ሌሎች ስነቃሎች ማህበረሰቦቹ ስለራሳቸው፣ ስለሰው ልጅ፣ ስለአካባቢያቸውና ስለዓለም ያሏቸውን አመለካከቶችና የህይወት ፍልስፍናዎች የሚያንጸባርቁ ናቸው፡፡

በማህበረሰብ ውስጥ ቡድኖችም ሆኑ ግለሰቦች በስነቃል ያሉበትን ሁኔታ በማጤን ሂስ ይሰጣሉ፤ ድጋፍ ተቃውሚቸውን ይገልጻሉ፤ ያለፈውን ያስተላልፋሉ፤ የወደፊቱን ይተነብያሉ፤ የአፈጣጠራቸውን ምስጢር ይመረምራሉ፡፡ በተጨማሪም የሰውን ልጅ መሰረታዊ ባህርያት ይገነዘባሉ፤ ለህልውናቸው ምክንያት ናቸው ብለው የሚያስቧቸውን ነገሮች ያሞግሳሉ፡፡ ድክመት ጥንካሬንም ይመረምራሉ፤ ህጻናቱንና ወጣቶቹን ያስተምራሉ፡፡

> **የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎች**
>
> *ተማሪዎች እስኪ ንባባችሁን ገታ አድርጋችሁ ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች በቃል ምላሽ ስጡ፡፡*
>
> ፩. ባነበባችሁት የምንባብ ክፍል የስነቃል ምንጭ ተብሎ የተገለጸው ምንድን ነው?
>
> ፪. እስካሁን ካነበባችሁት የንባቡ ክፍል ስነቃልን በተመለከተ የተነሱ ነጥቦች ምን ምን ናቸው?

ከስነቃል ባህርያት አንዱ አመንጭውን ወይም ደራሲውን ለማወቅ አለመቻሉ ነው፡፡ አንድን ተረት፣ ቀልድ ወይም ባህላዊ ዘፈን ለመጀመሪያ ጊዜ የተረተው፣ የተናገረው ወይም የዘፈነው እገሌ ነው ብሎ ዛሬ በደራሲነት አንድን ሰው ለመጥቀስ አይቻልም፡፡ አፈጣጠሩና ክንውኑ በጋራ በመሆኑ ባህላዊው ምግባር ለግለሰቡ ትኩረት አይሰጥም፡፡ ስነቃሉም ሀብትነቱ የማህበረሰቡ ነው፡፡ ስለዚህ የአቀንቃኙ ወይም የፈጣሪው ስም አይታወቅም፡፡ ስነቃል በቃል ከአንዱ ወደ

አንዱ የሚተላለፍ በመሆኑ መጀመሪያ ያፈለቀውን ግለሰብ ወይም ቡድን ማወቅ አይቻልም፡፡ ስነቃሉን ሲነገር ወይም ሲዜም ሰምቶ በማስታወስ መልሶ ለሌሎች ለመንገር ወይም ለማዜም የቻለ የማህበረሰቡ አባል ካንዱ ወደሌላው ሊያስተላልፈውና ለጊዜው ባለቤቱ ለመሆን ይችል ይሆናል፡፡ ከዚህም የተነሳ ነው ስነቃል የህዝብ ሀብት ነው እየተባለ የሚነገርለት፡፡ የባህሉ ሰው የሆነ ሁሉ ችሎታው ካለው ከመተረትና ከማዜም የሚያግደው አይኖርም፡፡ ምንም እንኳን የአንድን ስነቃል ደራሲ ለይቶ ማወቅ አይቻልም ቢባልም ቀደም ባለጊዜአንድ የፈጠራ ችሎታ ያለው ሰው የፈጠረው መሆኑን እንገነዘባለን፡፡

የግለሰቡ ኪናዊፈጠራ አሻራም እንዳለበት ግልጽ ነው፡፡ ስነቃ ሉን ካንዱ ሰምቶ ለሌላ የሚነግረው፣ የሚተርተው ወይም የሚያዜመው ደግሞ የራሱን ፈጠራ በመጨመር ለሌላያስተላልፈዋል፡፡ ከዚህም የተነሳ ስነቃል የተለዋዋጭነት ባህሪ አለው፡፡

አፈጣጠሩና ክንውኑ በጋራ በመሆኑ ስነቃሉ ቡድናዊ ተግባር ነው፡፡ ብዙዎቹ የስነቃል ዓይነቶች ባንድ ሰው ብቻ የሚባሉ አይደሉም፡፡ ብዙዎቹ በህብረት የሚነገሩ፣ የተናጋሪንና የአድማጭን ተሳትፎ የሚጠይቁ ናቸው፡፡ ለምሳሌ በተረት ተራች አለ፤ ተረቱን የሚያዳምጡ አሉ፡፡ ተረቱ በሚተረትበት ጊዜ አድማጮቹ ዜማ ካለው አብረው ያዜማሉ፤ ተራቹ ጥያቄ ቢጠይቃቸው ይመልሳሉ ወይም እንደተረቱ ባህርይ በአንድ ነገር ይሳተፋሉ፡፡ በባህላዊ ዘፈንም አቀንቃኝ አለ፤ ተሳታፊዎች ወይም ደግሞ ተቀባዮች አሉ፡፡ በድምጻቸው ያጅባሉ፤ ያጨበጭባሉ ወይም ከዘፈኑ ጋር የሚዛመድ የሰውነት እንቅስቃሴ ያደርጋሉ፡፡ የስነቃል የተሳታፊነት ወሰንና አግባብ እንደየስነቃሉ ዓይነት ይለያያል፡፡ ለምሳሌ በእንቆቅልሽ የጥያቄና መልስ ተሳትፎ ጊዜ ስህተት ቢፈጠር አድማጩ ማረሚያ ሊሰጥ ይችላል፡፡ በፉከራ አይዞህ በርታ በማለት ማደፋፈር የተለመደ ነው፡፡ በሙሾ ደግሞ ዋይ! ዋይ! እያሉ ደረት መምታት ፣ እጅ ማርገብገብ ወይም መዝለል ይኖራል፡፡የስነቃል ዓይነቶች የራሳቸው የሆነ ቡድናዊ አሰራር አላቸው፡፡

ስነቃል ብዙውን ጊዜ የሚቀርበው በአጫጭር ቅርጾች ነው፡፡ የሰው የማስታወስ አቅም የተወሰነ በመሆኑና የስነቃሉም ተሳታፊዎች በአንዳንድ አሰባሳቢ አጋጣሚዎች በመገኘት ሊያዳምጡና ሊመለከቱ የሚችሉት ለተወሰነ ጊዜ ወይም ቆይታ በመሆኑ ከጊዜውና ከሁኔታው ጋር ተመጣጣኝ ለመሆን የግድ በአጫጭር ቅርጾች መቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡ በአንጻሩ ደግሞ በአንዳንድ አካባቢዎች እንደ

"ኤፒክ" ያሉ ረጃጅም የስነቃል ቅርጾች መኖራቸው መዘንጋት የለበትም፡፡

ከተገለጸው በመነሳት የስነቃል ዋና ዋና ባህርያት ቃላዊነት ፣ ቡድናዊነት ፣ ተከዋኝነት ፣ ዕውዳዊነትና ተለዋዋጭነት ናቸው፡፡

ምንጭ፡-(ዘሪሁን አስፋው፣ የስነ-ጽሁፍ መሰረታዉያን፣ 2005፣ 20-22፣ ለማስተማሪያነት ንዲያመች ተሻሽሎ የቀረበ)

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

፩. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክል ለሆኑት "እውነት"፣ ስህተት ለሆኑት ደግሞ "ሐሰት" በማለት በቃል መልሱ፤ ምክንያታችሁንም ግለጹ፡፡

ሀ. ሙሾ በመተረት የሚገለጽ የስነቃል ዓይነት ነው፡፡

ለ. የስነቃል ባለቤት በውል ስለማይታወቅ የሕዝብ ሀብት ነው ይባላል፡፡

ሐ. ስነቃል አፈጣጠራዊ ክንውኑ በጋራ የሚከወን በመሆኑ ቡድናዊ ባህርይ አለው፡፡

መ. ስነቃል በደራሲው ተጽፎ በመተረትና በመዜም ከትውልድ ትውልድ ይተላለፋል፡፡

ሠ. በስነቃል አማካይነት ማንነትን ማሳወቅ፣ ምኞትና ተስፋን ማንጸባረቅ ይቻላል፡፡

ረ. ስነቃለ ከትውልድ ወደ ትውልድ በሚተላለፉበት ጊዜ ምንም ነገር አይጨመርበትም፤ አይቀነስበትም፡፡

፪. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት ከተሰጡት አማራጮች ውስጥ ተገቢውን መልስ ምረጡ፡፡

1. ቀጥሎ ከቀረቡት የስነቃል አይነቶች ውስጥ በአቀራረብ ቅርጽ ልዩ የሆነው የትኛው ነው?

ሀ. ተረት

ለ. አፈታሪክ

ሐ. ቀረርቶ

መ. እንቆቅልሽ

2. ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ የስነቃል ዋነኛ ባህርያት ተብለው የሚጠሩት የትኞቹ ናቸው?

ሀ. ቡድናዊነት

ለ. ተከዋኝነት

ሐ. ተለዋዋጭነት

መ. ሁሉም መልስ ናቸው

3. ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ ስነ-ቃልን አስመልክቶ ትክክል ያልሆነው የትኛው ነው?

ሀ. የበርካታ ገጠመኞች ነጸብራቅ ነው።

ለ. በተገኘው አጋጣሚ ይቀርባል።

ሐ. የህይወት መልኮች ነጸብራቅ ነው።

መ. የተደራሲያንን ተሳትፎ አይፈልግም።

4. “አንድ ሰው የሰማውን ተረት ለሌላ ሰው በሚናገርበት ጊዜ በጎደለው እየሞላና የራሱን ፈጠራ እያከለ ይናገራል፡፡” የሚለው የትኛውን የስነቃል ባህሪ ያመለክታል?

ሀ. የህዝብ ሃብትነት

ለ. የተለዋዋጭነት

ሐ. የአውዳዊነት

መ. የተከዋኝነት

5. በምንባቡ መሰረት ስነቃል በአጫጭር ቅርጾች የሚቀርበው ለምንድን ነው?

ሀ. የተሳታፊዎች የመከታተያ ጊዜ ውሱን ባለመሆኑ

ለ. ትረካው ከጊዜውና ከሁኔታው ጋር ተመጣጣኝ በመሆኑ

ሐ. የሰው ልጅ የማስታወስ አቅሙ የተወሰነ በመሆኑ

መ. ሁሉም መልስ ናቸው፡፡

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

፩. የስነቃልን ምንነት ጥንድ ጥንድ በመሆን ከተወያያችሁ በኋላ መልሳችሁን በጽሑፍ አስፍሩ፡፡

፪. ያነበባችሁትን ምንባብ መሠረት በማድረግ ቃላዊ ስነጽሑፍ በጽሑፍ ከሚቀርብ ስነጽሑፍ የሚለይበትን ባህሪ ጥንድ ጥንድ በመሆን ከተወያያችሁ በኋላ መልሳችሁን በሚከተለው ሰንጠረዥ ላይ አስፍሩ፡፡

| ቃላዊ ስነጽሑፍ | ጽሑፋዊ ስነጽሑፍ |
|---|---|
| | |
| | |
| | |

፫. የስነቃልን ዋና ዋና ባህርያት በምሳሌ በማስደገፍ አብራርታችሁ ጻፉ፡፡

፬. በበይነ መረብ እና በቤተ መጽሐፍ በመጠቀም በቃላዊ ስነ-ጽሁፍ ተግባር ላይ የተፃፉ የተለያዩ ጽሁፎችን አንብባችሁ ያገኛችሁትን መረጃ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል ግለጹላቸው፡፡

፭. ከዚህ በታች በቀረበው ሰንጠረዥ መሰረት የስነቃል ዓይነቶችን ዘርዝሩ፡፡

| በመነገር | በመዜም | በምስል |
|---|---|---|
| | | |
| | | |
| | | |

፮. ከዚህ በታች የቀረቡትን ምሳሌያዊ ንግግሮች መልዕክት አብራርታችሁ ጻፉ፡፡

ሀ. ድር ቢያብር አንበሳ ያስር

ለ. የነቶሎ ቶሎ ቤት ግድግዳው ሰንበሌጥ

ሐ. ሳይርቅ በቅርቡ ሳይደርቅ በርጥቡ

መ. ቀይና ወርቅ ሲብለጨለጭ ያልቅ

ሠ. ጤፍ ከነወንድሟ ጎተራ ትሞላለች

ረ. ላም እሳት ወለደች፤ እንዳትልሰው ፈጃት እንዳትተወው ልጅ ሆነባት

፯. ቀጥሎ በቀረቡት ቃላዊ ግጥሞች ላይ በጥንድ በመወያየት የያዙትን መልዕክት ጻፉ፡፡

ሀ. ገበሬ ቢኮራ ምርቱን አምርቶ ነው

ነጋዴ ቢኮራ ትርፉን አትርፎ ነው

የሰነፍ ኩራቱ ከምን የመጣ ነው

ለ. በጎምላላ በሬ ሂድ ብሎ ሂድ ብሎ

ቆርቆሮ አለበሰ ሳሩን ወዲያ ጥሎ

ሐ. ቁም ነገረኛ ሴት ለትዳሯ ጠጅ

የልብ ታደርሳለች በቤትም በደጅ

መ. የዐባይ ውሀ ሞልቶ ዳር ዳሩን ይዋኛል

ያንተ ልብ እንዴት ነው የኔስ ይዋልላል

ሠ. የፈተለች እንደሁ አስመስላ ጭራ

የጋገረች እንደሁ አስመስላ ሞራ

የጠመቀች እንደሁ የማሩን ወለላ

እሷን የሠራ 'ለት አልሠራም ወይ ሌላ

፰. በግጥማዊ ቅርጽ እና በዝርዋዊ ትረካዊ ቅርጽ ሊቀርቡ የሚችሉ የስነቃል ዓይነቶች ዘርዝሩ፡፡

# የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ በማዳመጥ ክፍል ውስጥ ባዳመጣችሁት ትረካ አማካይነት የታሪኩን ተሳታፊዎች፣ ትረካው ግላዊ ባለቤት የሌለው መሆኑንና በየትኛው የስነቃል ክፍል ውስጥ እንደሚመደብ፣ የታሪኩ መልዕክት (ጭብጥ) ምን እንደሆነ ተምራችኋል፡፡

በክፍል ኹለት በቡድን በመሆን ባቀረባችሁት ተረት መሠረት የተረቱን ተሳታፊዎችና መልዕክቱን በመግለጽ ተለማምዳችኋል፡፡ የእንቆቅልሽ አከዋወንን በቀረበላችሁ ምሳሌና በጻፋችኋቸው እንቆቅልሾች አማካይነት ተለማምዳችኋል፡፡

በክፍል ሦስት የስነቃል ምንነትንና ባህርያትን በቀረበው ምንባብና በሠራችኋቸው መልመጃዎች አማካይነት ተምራችኋል፡፡

በክፍል አራት ደግሞ በቃላዊ ስነጽሁፍ ምንነት ላይ ተወያይታችኋል፡፡የቃላዊ ባህሪያትን፣ ተግባራትን፣ ክፍሎችንና ዓይነቶች ለይታችኋል፡፡

# የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

1. ስነቃል ማለት ምን ማለት ነው?
2. ሁለት እንቆቅልሾችን ጻፉ፡፡
3. የስነቃል ባህርያት ምን ምን ናቸው?
4. ስነቃል ለማኅበረሰቡ የሚኖረውን ፋይዳ ግለጹ፡፡
5. በመዜም ከሚቀርቡ የስነቃል ዓይነቶች ውስጥ ቢያንስ ሁለቱን ጻፉ፡፡

# የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ አምስት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ቅጽ ቀርቦላችኋል፡፡ በዚህም መሠረት በእያንዳንዱ ማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ቅጹን አሟሉ፡፡

| | የማመሳከሪያ ነጥቦች | √ | ? | X |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ያዳመጥኩትን ተረት መልዕክት መግለጽ ችያለሁ | | | |
| 2 | የስነቃልን ጽንሰ ሀሳብ መለየት ችያለሁ | | | |
| 3 | የእንቆቅልሽ ጥያቄዎችን መጻፍና መልሳቸውን መመለስ ችያለሁ | | | |
| 4 | የስነቃልን ባህርያት መለየት ችያለሁ | | | |
| 5 | የስነቃል ዓይነቶችን መለየት ችያለሁ | | | |
| 6 | በመነገር፣ በመተረትና በመዜም የሚቀርቡትን የስነቃል ዓይነቶች መዘርዘር ችያለሁ | | | |
| 7 | የስነቃልን ጭብጥ (መልዕክት) መግለጽ ችያለሁ | | | |

፪. ከዚህ በላይ በቀረበው ቅጽ የ(?) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትገነዘቡ ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

አማርኛ

(፱ኛ) ክፍል

# ምዕራፍ ስድስት፡- ግጥም

**የምዕራፉ ዓላማዎች፡-**

**ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፣**

- ❖ የግጥሙን ሀሳብ ካዳመጣችሁ በኋላ በቃላቸው ትገልጻላችሁ፡፡
- ❖ በግጥሙ ውስጥ የተጠቀሱ የተለያዩ ዘይቤያዊ አነጋገሮችን ትለያላችሁ፡፡
- ❖ በጽሑፍ ውስጥ ዘይቤያዊ አነጋገሮችን ትጠቀማላችሁ፡፡
- ❖ በግጥም ውስጥ የቃላት አጠቃቀምን ትለማመዳላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

አደን

### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

፩. ተማሪዎች ከአሁን በፊት ግጥም አንብባችሁ ታውቃላችሁ? መልሳችሁ "አዎ" ከሆነ እስኪ የምታስታውሱትን ግጥም ለጓደኞቻችሁ ንገሯቸው፡፡

፪. ግጥም ምንድን ነው? በቡድን ተወያዩና መልሶቻችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ በተወካዮቻችሁ አማካኝነት ግለጹላቸው፡፡

### የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

፩. ከዚህ በታች የቀረቡት ስንኞች ካዳመጣችሁት ግጥም ውስጥ የተወሰዱ ናቸው፡፡ በየስንኞቹ ውስጥ የተሰመረባቸውን ቃላት እና ሀረጋት ዐውዳዊ ፍች ጻፉ፡፡

ሀ. ስንዴ ጨበጨበ እሸቱ ደረሰ፡፡

ለ. ዝናቡም ሲፈጸም ተከተለ ብራ፡፡

ሐ. ካፋፍ ላይ ሲያስተውሉት አገሩን በሰፊ፣

መ. መሬት ትታያለች የክት ልብሷን ለብሳ፣

ሠ. አክርማ እና ጦስኝ ደግሞም እነሙጃ፣

፪. ባዳመጣችሁት ግጥም ውስጥ ያሉትን ዘይቤያዊ አገላለጾች ጻፉ፡፡

፫. ያዳመጣችሁትን ግጥም መሠረት በማድረግ ምስል ከሳች ቃላትንና ዘይቤያዊ አነጋገርን የያዘ ግጥም በመጻፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡

## ክፍል ኹለት፡- መናገር

፩. የሚከተለውን ግጥም የአነባበብ ስልቱን በመጠቀም አንብቡ፡፡

### አደን

አሣዳጄን አመለጥኳት

አመለጠችኝ ያሣደድኳት፡፡

ኗሪ ሆንኩኝ እንደፍየል

በነብርና ቅጠል መሀል

አቤት አለች ያልጠራኋት

የጠራኋት ድምፅም የላት፡፡

ራቂኝ 'ምላት ጎኔ ወድቃ

ቅረቢኝ 'ምላት ከኔ ርቃ፡፡

አንዴ ስታደን አንዴም ሳድን

ዕረፍት አጥቼ ስባክን

የዕድሜዬን ጀንበር ብታዘባት

ልትጠልቅ ምንም አልቀራት፡፡

(ምንጭ፡- ደበበ ሠይፉ (1992) ለራስ የተጻፈ ደብዳቤ
(የብርሃን ፍቅር ቅጽ ፪)

፪. በቡድን በመወያየት በግጥም እና በዝርው ትረካ መካከል ያለውን ልዩነት ግለጹ፡፡ በቀረበው ምሳሌ መሠረት የሁለቱንም ልዩነት ለማመልከት የሚከተለውን ሠንጠረዥ ተጠቀሙ፡፡

| የግጥምና የዝርው ትረካ ልዩነት | |
|---|---|
| ግጥም | ዝርው ትረካ |
| ስንኞቹ በአንድ በአንድ መስመር እየተጻፉ ወደታች ይደረደራሉ | ዐረፍተ ነገሮቹ በመስመሮቹ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው መስመር ተከታትለው ይጻፋሉ |
| | |
| | |
| | |
| | |
| | |

፫. በቡድን በመሆን በመረጣችሁት ርዕስ ላይ አሳማኝ ገለጻ በማዘጋጀት ለክፍል ጓደኞቻችሁ የቅስቀሳ ንግግር አቅርቡ፡፡

## ክፍል ሦስት፡- ንባብ

### አገሬ

#### ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

፩. በግጥም ውስጥ ቃላትና ሀረጋት ተደጋግመው ሲቀርቡ ይታያል፡፡ የቃላትና ሐረጋት በግጥም ውስጥ ተደጋግመው የመቅረባቸው ምክንያት ምን ይመስላችኋል? በቡድን ተወያዩበት፡፡

፬. በግጥም ውስጥ ምሳሌያዊ ንግግሮች፣ ዘይቤያዊ አገላለጾች፣ የተመረጡ ቃላት ጥቅም ላይ የሚውሉት ለምን ይመስላችኋል? በቡድን ተወያዩባቸው።

፫. ከዚህ በታች "አገሬ" በሚል ርዕስ የቀረበው ግጥም ስለምን የሚገልጽ ይመስላችኋል?

## አገሬ

አገሬ ውበት ነው!

ለምለም እና ነፋስ የሚጫወቱበት፣

ፀሃይ የሞላበት፣ ቀለም የሞላበት።

አገሬ ቆላ ነው፣ደጋ ወይና ደጋ፣

እዚያ ብርሃን አለ ሌሊቱ ሲነጋ።

አገሬ ተራራ ሸለቆ ረባዳ፣

አገሬ ጅረት ነው ገደል እና ሜዳ።

ውሸት ነው በበጋ ፀሃይ አትፋጅም፣

ክረምቱ አይበርድም፣

አይበርድም አይበርድም።

አገሬ ጫካ ነው፣

እንስሳት አራዊት የሚፈነጩበት፣

በወጥመድ ሳይገቡ፣ ሳይነካቸው ጠላት፣

እዚያ አለ ነፃነት፣

በሀገር መመካት፣

በተወላጅነት፣

በባለቤትነት፣

እዚያ አለ ነፃነት፡፡

አገሬ ሀብት ነው፡፡

ጎመኑ ስብ ጮማ፣ ቆሎው ክትፎ ስጋ፣

ድርቆሹ ፍትፍት ነው፣ ቃሪያው ሙክት ሰንጋ፡፡

ጠጁ ነው ወለላ፣

ከኮኛክ ይነጥቃል፣ የመንደሩ ጠላ፡፡

እህሉ ጣም አለው፣ እንጀራው ያጠግባል፣

ከቢራ ከሻምፓኝ፣ ውሃው ይጣፍጣል፡፡

በዓሉ ይደምቃል፣

ሙዚቃው ያረካል፣

ጭፈራው ዘፈኑ፣ ችግርን ያስረሳል፡፡

እዚያ ዘመድ አለ፡፡

ሁሉም የናት ልጅ ነው፡፡

ሁሉም ያባት ልጅ ነው፡፡

ጠላትም አንዳንዴ ይመጣል መቃብር፣

ባላጋራም ቸር ነው፣ “ያገር ልጅ” ሲቸገር፡፡

ገነት ነው አገሬ፡፡

ምነው ምን ሲደረግ፣

ምነው ለምን እንዴት፣

ዘራፊ ቀማኛ ምቀኛ ወንበዴ፣

ጥቁር አፈር በጁ ስንዝር አፈር አልፎ፣

የተቀደሰውን ያፍሪካ ላይ ደሴት፣

ቢያገኝ ለማርከስ ጠላት ይመኝ እንዴት፡፡

እምቢኝ አሻፈረኝ!

አሻፈረኝ እምቢኝ!

መቅደስ ነው አገሬ፡፡አድባር ነው አገሬ፡፡

አያት ቅድመ አያቴ ድኸው ያደጉበት፣

ካያት ከቅም አያት የተረካከቡት፣

አፈር የፈጩበት፣

ጥርስ የነቀሉበት፡፡

አገሬ አርማ ነው የነፃነት ዋንጫ፣
በቀይ የተጌጠ ባረንጓዴ ቢጫ፡፡

እሾክ ነው አገሬ፡፡

በጀግናው ልጅ አጥንት የተከሰከሰ፣

ጠላት ያሳፈረ አጥቂን ድባቅ መትቶ ወዲያ የመለሰ፡፡

አገሬ ታቦት ነው መቅደስ የሃይማኖት፣
ዘመን የፈተነው በጠበል በጸሎት፡፡

ለምለም ነው አገሬ፡፡

ውበት ነው አገሬ፡፡

ገነት ነው አገሬ፡፡

ብሞት እሄዳለሁ ከመሬት ብገባ፣

እዚያ ነው አፈሩ የማማ ያባባ፡፡

ስሳብ እሄዳለሁ ቢሰበርም እግሬ፣

አለብኝ ቀጠሮ ከትውልድ አገሬ፡፡
አለብኝ ቋጠሮ፣
ከትውልድ አገሬ ካሳደገኝ ጓሮ ፡፡

ምንጭ፡- ገብረ ክርስቶስ ደስታ (1996)
(መንገድ ስጡኝ ሰፊ፤ ገጽ 139-140)

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

፩. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች በግጥሙ መሠረት ተገቢውን መልስ ጻፉ፡፡

1. በግጥሙ ውስጥ "እዚያ አለ ነጻነት" የሚለው ሀረግ ምንን ያመለክታል?
2. በግጥሙ ውስጥ "ገነት ነው አገሬ" ሲል ምን ማለቱ ነው?
3. በግጥሙ ውስጥ ተደጋግመው የቀረቡትን ቃላትና ሀረጋት ለይታችሁ ጻፉ፡፡
4. "ብሞት እሄዳለሁ ከመሬት ብገባ፣

   "እዚያ ነው አፈሩ የማማ ያባባ፡፡" ሲል ምን ማለቱ ነው?
5. የግጥሙ አጠቃላይ መልዕክት ምንድን ነው?

፪. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች በግጥም መሰረት ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ ጻፉ፡፡

1. በግጥሙ መሠረት ባለታሪኩ ምን አይነት ሰው ነው?

   ሀ. የመንግስት ባለስልጣን　　ለ. አባት አርበኛ

   ሐ. የከተማ ነዋሪ　　መ. በስደት ላይ ያለ

2. ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ የተጋነነ አገላለጽን የሚያመለክተው ስንኝ የትኛው ነው?

   ሀ. አገሬ ቆላ ነው፣ደጋ ወይና ደጋ፣

   ለ. ጎመኑ ስብ ጮማ፣ ቆሎው ክትፎ ስጋ፣

   ሐ. እህሉ ጣም አለው፣ እንጀራው ያጠግባል፣

   መ. ሁሉም መልስ ናቸው

3. በግጥሙ ውስጥ "ድርቆሹ ፍትፍት ነው፣ ቃሪያው ሙክት ሰንጋ" የሚለው ስንኝ በየትኛው የዘይቤ አይነት የቀረበ ነው?

ሀ. በሰውኛ ለ. በአነጻጻሪ

ሐ. በተለዋጭ መ. በእንቶኔ

4. የግጥሙ ባለታሪክ ወደ አገሩ ለመመለስ ያነሳሳው ምክንያት ምን ሊሆን ይችላል?

ሀ. አገሩ ማረፊያው ስለሆነች ለ. የስደት ኑሮ ስላስመረረው

ሐ. አገሩ በጦርነት ስለተወረረ መ. የስራ ጫና ስለበዛበት

5. ቀጥሎ ከተዘረዘሩት ውስጥ በግጥሙ ያልተገለጸው ሃሳብ የትኛው ነው?

ሀ. የኢትዮጵያ መልክዓ ምድራዊ ገጽታ

ለ. ኢትዮጵያ ለጠላቶቿ መመቸቷን

ሐ. የኢትዮጵያ አየር ንብረት ሁኔታ

መ. ሁሉም መልስ ነው

፫. በቡድን በመሆን በግጥሙ ውስጥ ተካተው የሚገኙትን ምስል ከሳች ቃላትን ለይታችሁ በማውጣት አብራሩ፡፡

፬. በግጥሙ ውስጥ የሚታዩትን ዘይቤያዊ አገላለጾች ለይታችሁ ካወጣችሁ በኋላ ለግጥሙ ያበረከቱትን አስተዋጽዖ (ፋይዳ) አብራሩ፡፡

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

፩. በቡድን በመሆን ከላይ በማዳመጥ እና በንባብ ክፍል የቀረቡትን ግጥሞች መሠረት በማድረግ የግጥምን ባህርያት ጻፉ፡፡

፫. ዘይቤያዊ አገላለጾችን የያዙ የተለያዩ ግጥሞችን አንብባችሁ በግጥሙ ውስጥ ተካተው የሚገኙትን የዘይቤ ዓይነት በመለየት በጽሁፉ ውስጥ ያላቸውን ሚና ጻፉ፡፡

## የግጥም አይነቶች

በአማርኛ ግጥም ተዘውታሪነት ያላቸው የተለያዩ የምጣኔ ስልቶች አሉ፡፡ የግጥም ዓይነቶች በሀረግ ወይም በስንኝ ከሚይዟቸው የምጣኔ ስልትና የቀለማት መጠን አኳያ በተለያዩ ክፍሎች ይመደባሉ፡፡ ከዚህም በመነሳት ከግጥም ዓይነቶች ውስጥ የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

**ሀ. ቡሄ በሉ ቤት፡-** ቡሄ በሉ ቤት በሐረግ (ከ1_4) ቀለሞችን የሚይዝ የስንኝ ምጣኔ ነው፡፡ ምጣኔው "ቡሄ ቡሄ" ከሚባለው የልጆች ጭፈራ ዜማ መጠሪያውን ያገኘ ይመስላል፡፡ ሃረጎች ፈጣኖች፣ ዜማው ቁርጥ ቁርጥ የሚል በጥድፊያ የሚከወን ስንኝ ነው፡፡

ምሳሌ፡- እዘያ ማዶ / ጭስ ይጨሳል

አጋፋሪ / ይደግሳል

**ለ. ሰንጎ መገን ቤት፡-** የሰንጎ መገን ምጣኔ በሐረግ 5 ቀለማት አሉት፡፡ ይህ የምጣኔ ስልት በፈጣንና እልህ፣ ኃይልና ግለት በተቀላቀሉበት ሁኔታ ይከወናል፡፡ብዙ ጊዜም የጀግንነት ሙያ ይነገርበታል፡፡

ምሳሌ፡- ውረድ እንውረድ / ተባባሉና፣

አስደበደቡት / አፋፍ ቆሙና፡፡

**ሐ. የወል ቤት፡-** ይህ የግጥም ዓይነት በአብዛኛው በሀረግ ስድስት ቀለማት አሉት፡፡

ምሳሌ፡- እስከ ጊዜው ድረስ / እስኪሞላ ልኩ፣

የጀግና ፈረስ ነው / የሰው ሁሉ መልኩ፡፡

(ምንጭ፡- ብርሃኑ ገበየሁ (1999) የአማርኛ ሥነግጥም)

፫. በሚከተሉት ግጥሞች ላይ በመወያየት ለሚከተሉት ጥያቄዎች በጽሁፍ ምላሽ ስጡ።

ሀ. ግጥሞቹ ከየትኛው የግጥም ዓይነት እንደሚመደቡ ጻፉ።

ለ. ግጥሞቹ በስንኝ ያላቸውን የቀለም መጠን (ቁጥር) ለይታችሁ ጻፉ።

ግጥም-1

ለእምዬ ኢትዮጵያ እንዲሆን ህዳሴ፣

በርትቼ ሠራለሁ አልሳሳም ለነፍሴ።

ግጥም-2

አንሱ ካላችሁ እናንሳ ወንድ፣

የቋራው ካሳ አባ ሞገድ።

ግጥም-3

የቡሄ ለት / አለኝ ለከት

አንድም አይደል / ያውም ኹለት

ግጥም-4

ስለቱ ዶልዱሞ መገዝገዝ ሲጀምር፣

ምነው እንደ ቢላ ቢሞረድ ያ ብዕር።

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

የሚከተሉትን ቃላት መዝገበ ቃላዊ ፍቻቸውን ጻፉ። የቃላቱን ፍች የሚያመለክቱ ዐረፍተ ነገሮችንም ሥሩ።

ሀ. ጨበጨበ

ለ. ጅረት

ሐ. ፈነጨ

መ. ባላጋራ

ሠ. ገነት

ረ. ጥርኝ

ሰ. ስንዝር

ሸ. ማርከስ ቀ. ድኸው

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

በሚከተሉት ቃላት ላይ ተቀጥለው የሚገኙትን ቅጥያዎች ለይታችሁ አመልክቱ፡፡

ሀ. ጎመኑ

ለ. በሀገር

ሐ. ካረንጓዴው

መ. የመንደሩ

ሠ. ያባት

ረ. ድርቆሹ

ሰ. እየሸሸ

ሸ. የተቀደሰውን

ቀ. አይበርድም

በ. የሚፈነጩበት

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ግጥምን በሚመለከት የተለያዩ ጉዳዮች ተነስተዋል፡፡ በማዳመጥ ክፍል ውስጥ የግጥምን ምንነት፣ በግጥም ውስጥ የሚገኙትን ቃላት ዐውዳዊ ፍች እና በግጥሙ ውስጥ ምስል ከሳች ቃላትንና ዘይቤያዊ አገላለጾች በቀረቡላችሁ የመልመጃ ጥያቄዎች በመታገዝ ተምራችኋል፡፡

በክፍል ኹለት የቀረበላችሁን ግጥም በመጠቀም የግጥም አነባብ ስልት ልምምድ አድርጋችኋል፤ በግጥም እና በዝርው ትረካ መካከል ባለው ልዩነት ላይ በቡድን ተወያይታችኋል ፡፡ በመረጣችሁት ርዕስ ላይም አሳማኝ የንግግር ዝግጅት በማድረግ የቅስቀሳ ንግግር ልምምድ በማቅረብ ተለማምዳችኋል፡፡

በክፍል ሦስት የቃላትና የሀረጋት በግጥም ውስጥ ተደጋግመው የመቅረባቸው ምክንያት ምን እንደሆነ፤ ምሳሌያዊ ንግግሮች፣ ዘይቤያዊ አገላለጾች፣ የተመረጡ ቃላት በግጥም ውስጥ ምን ፋይዳ እንዳላቸው በቡድን ተወያይታችኋል፡፡ በቀረቡላችሁ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች አማካኝነትም የተለያዩ የመልመጃ ጥያቄዎችን ሠርታችኋል፡፡

በክፍል አራት ግጥም የተጨባጭነት፣ የእምቅነትና የቁጥብነት፣ የምናባዊነት እና የሙዚቃዊነት ባህሪ እንዳለው ተምራችኋል፡፡ በግጥም ውስጥ የሚገኘውን ምጣኔ መሠረት በማድረግ የቡሄ በሉ ቤት፣ የወል ቤት፣ የሰንጎ መገን ቤት ግጥም ዓይነቶችንም ተምራችኋል፡፡ በግጥም ውስጥ የሚገኙትን የቀለማት መጠን በመለየት የግጥሞችን ዓይነትም መግለጽን ተለማምዳችኋል፡፡

በክፍል አምስት የቃላትን መዝገበ ቃላዊ ፍች በመፈለግ ፍቻቸውን የሚያመለክቱ ዐረፍተ ነገሮችን በመሥራት ተለማምዳችኋል፡፡

በክፍ ስድስት ደግሞ በቃላት ላይ ተቀጥለው የሚገኙትን ቅጥያዎች በመለየት ልምምድ አድርጋችኋል፡፡

## የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

1. ግጥም ምንድን ነው?
2. ከግጥም ባህርያት ውስጥ ሁለቱን በመጥቀስ አብራሩ፡፡
3. በግጥም ውስት ምስል ከሳች ቃላትን፣ ዘይቤያዊ አገላለጾችን፣ ምሳሌያዊ ንግግሮችን ምን ፋይዳ እንዳላቸው አብራሩ፡፡
4. የግጥም ዓይነቶችን ግለጹ፡፡

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ ስድስት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ቅጽ ቀርቦላችኋል፡፡ በዚህም መሠረት በእያንዳንዱ ማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ቅጹን አሟሉ፡፡

| ተ.ቁ. | የማመሳከሪያ ነጥቦች | √ | ? | X |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ያዳመጥኩትን ግጥም መልዕክት መግለጽ ችያለሁ | | | |
| 2 | የግጥምን ምንነት መግለጽ ችያለሁ | | | |
| 3 | በግጥም ውስጥ የተጠቀሱትን ዘይቤያዊ አገላለጾች መለየት ችያለሁ | | | |
| 4 | ምስል ከሳች ቃላትንና ሀረጋትን በመጠቀም ግጥም መጻፍ ችያለሁ | | | |
| 5 | የግጥም ባህርያትን መግለጽ ችያለሁ | | | |
| 6 | የግጥም ዓይነቶችን መለየት ችያለሁ | | | |
| 7 | መዝገበ ቃላትን በመጠቀም የቃላትን ፍች መግለጽ ችያለሁ | | | |
| 8 | በቃላት ላይ የተቀጠሉትን ቅጥያዎች መለየት ችያለሁ | | | |

፫. ከዚህ በላይ በቀረበው ቅጽ የ (?) እና የ (X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትገነዘቡ ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

አማርኛ

(፱ኛ) ክፍል

ምዕራፍ ሰባት፡- ኮቪድ -19 (ኮሮና)

**የምዕራፉ ዓላማዎች፡-**

**ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፣**

- ❖ ስለ ኮቪድ-19 (ኮሮና) የተጻፈ ጽሑፍ ካዳመጣችሁ በኋላ የጽሑፉን ዋና ሀሳብ ታብራራላችሁ።
- ❖ በነጻነት ወይም በራስ መተማመን መንፈስ ሃሳባችሁን ትገልጻላችሁ።
- ❖ ኮሮናን ለመከላከል የሚያስችሉ መመሪያዎችን በመቀበል ትተገብራላችሁ።
- ❖ ታዳሚውን መሰረት ያደረገ ጽሑፍ ታዘጋጃላችሁ።
- ❖ ስምምነት በተደረሰባቸው ቃላትና ሆሄያት በመጠቀም ትጽፋላችሁ።
- ❖ ዋና ቃሉን ወይም ነጻ ምዕላዱን እንዲሁም ቅድመ ቅጥያውን እና ድህረ ቅጥያውን በማውጣት ታሳያላችሁ።

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

### ኮቪድ-19 (ኮሮና)

### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

፩. ከዚህ በታች በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ በቡድን በመወያየት መልሳችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

ሀ. ኮቪድ-19 (ኮሮና) ምንድን ነው?

ለ. የኮቪድ-19 (ኮሮና) መተላለፊያ መንገዶች ምን ሊሆኑ ይችላሉ?

ሐ. “ኮቪድ-19 (ኮሮና)” በሚል ርዕስ የሚቀርበው ምንባብ ይዘት ምን ይመስላችኋል?

፪. በሚከተሉት ቃላት ፍች ላይ በቡድን በመወያየት መልሳችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

ሀ. ቫይረስ

ለ. እክል

ሐ. ግዴለሽነት

### የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

፩. የኮሮና ቫይረስ ዓይነቶች የተባሉት እነማን ናቸው?

፪. በምንባቡ የተገለጹት የኮቪድ-19 በሽታ ምልክቶች ምን ምን ናቸው?

### የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

፩. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ መልሳችሁን በቃል ግለጹ፡፡

ሀ. የኮሮና ቫይረስ ሰውነት ውስጥ ከገባ በኋላ የበሽታው ምልክት እስከሚታይ ለምን ያህል ጊዜ ሊቆይ ይችላል?

ለ. ኮቪድ-19 የሚያስከትላቸው ጉዳቶች ምን ምን ናቸው?

ሐ. ሁሉም የጉንፋን ምልክቶች በኮቪድ ምክንያት የሚመጡ ናቸው? ለምን?

መ. የኮሮና ቫይረስ ስርጭትን መከላከል የማን ኃላፊነት ነው?

፪. በጥንድ በመሆን ባዳመጣችሁት ምንባብ ዋና ዓላማ ላይ በመወያየት መልሳችሁን በቃል ግለጹ።

፫. በተገቢ ሆሄያት የተዋቀሩ ቃላትን በመጠቀም ላዳመጣችሁት ጽሁፍ የማጠቃለያ ሀሳብ አቅርቡ።።

## ክፍል ሁለት፡- መናገር

፩. በማንኛውም ዕድሜ ላይ ያለ ማንኛውም ግለሰብ በኮቪድ-19 በሽታ ሊያዝ ይችላል። ነገር ግን አንዳንድ ሰዎች ምንም ህመም ባይሰማቸውም እንኳ ወደሌላ ያስተላልፋሉ፤ አንዳንዶቹ ትንሽ ህመም ብቻ ይሰማቸዋል፤ ሌሎቹ በጣም ይታመማሉ፤ አንዳንዶቹ ደግሞ ከሌሎች ይልቅ በፀና ሊታመሙ ይችላሉ። በኮቪድ-19 ምክንያት በፀና የታመሙ ሰዎች ሆስፒታል ገብተው ህክምና ማግኘት ሊኖርባቸው ይችላል። እስኪ እናንተም በይነ መረብን ወይም ሌሎች የመረጃ ምንጮችን በመጠቀም እስካሁን በተደረገው ጥናት መሠረት በኮቪድ-19 የፀና ህመም የመያዝ ዕድላቸው ሰፊ እንዲሆን ሊያደርጉ የሚችሉ የህመም ዓይነቶች በሚመለከት መረጃዎችን በመሰብሰብ ዘገባ በማዘጋጀት አቅርቡ።

፪. በምዕራፍ ሁለት ክርክር ሁለት ተቃራኒ አመለካከት ባላቸው ቡድኖች መካከል የሚካሄድ ሙግት መሆኑን፣ በክርክር ቅድመ ዝግጅት እና ክርክር በሚቀርብበት ጊዜ ምን ምን ተግባራት መከናወን እንዳለባቸው ተምራችኋል፡፡ በተማራችሁት መሠረት “ኮሮና ቫይረስን በባህላዊ መድኃኒት መከላከል ወይም ማከም ይቻላል” በሚለው ርዕስ ላይ በቡድን በመከፋፈል፣ የክርክር አቀራረብን ሂደት በመከተል ክርክር አድርጉ፡፡

## ክፍል ሦስት፡- ንባብ

# ከህዳር በሽታ እስከ ኮሮና

### ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

ከዚህ በታች በቀረቡት የቅድመ ንባብ ጥያቄዎች ላይ በቡድን በመሆን ከተወያያችሁ በኋላ መልሳችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ተናገሩ፡፡

፩. ወረርሽኝ ማለት ምን ማለት ይመስላችኋ?

፪. ኮቪድ-19 (ኮሮና) በሰዎች የአኗኗር ሥርዓት ላይ ምን ምን ለውጦችን የሚያስከትል ይመስላችኋል?

፫. ከዚህ በታች “ከህዳር በሽታ እስከ ኮሮና” በሚል ርዕስ የቀረበው ምንባብ ይዘት ምን ይመስላችኋል?

## ከህዳር በሽታ እስከ ኮሮና

“…ፈጣሪ መጀመሪያ ሀኪሞቹን ወሰደ፤ ከዚያም ህዝቡ በወረርሽኝ አለቀ…”ይህን የጻፉት ወንጌል ለማስፋፋት ወደኢትዮጵያ መጥተው የነበሩ ሚሽነሪዎች ናቸው፡፡ በወቅቱ “የህዳር በሽታ” ተብሎ የሚጠራው የኢንፍሉዌንዛ ወረርሽኝ በሺዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያንን ሕይወት የቀጠፈበት ነበር፡ ፡ እጅግ ጥቂት የሚባሉት የጤና ባለሙያዎች ሳይቀሩ በወረርሽኙ የሞቱበት በመሆኑ ችግሩን

መቆጣጠር አልተቻለም ነበር፡፡ “ስምንት ሀኪሞች ቢኖሩ አራቱ በወረርሽኙ ሞተዋል” መባልን በየስፍራው ሲሄዱ መስማት የተለመደ እንደነበር ፕሮፌሰር ሪቻርድ ፓንክርስት የወቅቱን ማስታወሻ ከታቢዎች ጠቅሰው ጽፈዋል፡፡

ከኤደን ባህረ ሰላጤ ወደኢትዮጵያ እንደገባ የሚነገረው ይህ የመተንፈሻ አካላትን የሚያጠቃው የኢንፍሉዌንዛ ወረርሽኝ በአዲስ አበባ ብቻ ወደ አስር ሺ ሰዎችን ሲገድል በተቀረው የሀገሪቱ ክፍል ደግሞ እስከ ሃምሳ ሺ ሰዎች መሞታቸውን ፓንክረስት “The History of Epidemics in Ethiopia” በተሰኘው ጽሁፋቸው ጠቅሰዋል፡፡ የህዳር በሽታ ጥቃት ለበርካታ የኑሮ ዘዬ መቀየር ምክንያት ሆኗል፤ የወቅቱን መሪዎች ያስጨነቀና አሁን ድረስ የሚታወስ ቀውስ ነው፡፡ በዚህ መነሻም በየዓመቱ ህዳር 12 “ህዳር ሲታጠን” በሚል ስያሜ ኢትዮጵያውያን ከቤታቸው እና ከአካባቢያቸው የበሽታ እና የወረርሽኝ ምንጭ ሊሆኑ የሚችሉ ቆሻሻዎችን እየሰበሰቡ ያቃጥላሉ፡፡ ይህን መሰሉ ምላሽ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በአንዳንድ ወረርሽኞች ክፉኛ ያጠቋቸው በነበሩ የደቡብ አሜሪካ አካባቢዎች እንደሚዘወተር መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ከልምዶች ባለፈ ግን ዓለም በየወቅቱ ከምታስተናግዳቸው ወረርሽኞች ብዛት እና ስፋት አንጻር ምን ቋሚና ሳይንስን መሠረት ያደረጉ ቅድመ መከላከያ ዘዴና ስርዓቶች ማበጀት ተቻለ? የሚለው ጥያቄ የብዙ ተመራማሪና ሳይንስ አዋቂዎች ጥያቄ ነው፡፡ እንደ አሁኑ ያለ የኮሮና ቫይረስ ወረርሽን ሲከሰትም በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ ከቀደሙት ዓለምን ያሽመደመዱ ትልልቅ ወረርሽኞች የተወሰደ ትምህርትና መፍትሔን መለስ ብሎ መቃኘት ለአሁኑ ትግል ትንሽም ቢሆን አቅጣጫ ይሰጣል ይላሉ - ባለሞያዎች፡፡

ከቀደሙ ወረርሽኞች ዓለም ተምሮ ካስቀመጣቸው መፍትሔዎች በወረርሽኝ ወቅት ምልክት ያለባቸው ወይም ታማሚ ሰዎችን ነጥሎ ማስቀመጥና ማከም (ኳራንቲን) አንዱ ነው፡፡ ይህ መፍትሔ ድንበር ዘለል የሆኑ ወረርሽኞችን ለመገደብ ብዙ ያግዛል፡፡ ኳራንቲን ለህዝብ ጤና ጠቃሚ እርምጃ ሆኖ የተጀመረው በአውሮፓ አቆጣጠር በ1580 በእስያ ተከስቶ በነበረው የኢንፍሉዌንዛ ወረርሽኝ ወቅት ነበር፡፡ ሌላው የሚተገበረው የመጀመሪያውን ታማሚ ፈልጎ ማግኘትና፣ ይህ ሰው ያገኛቸውን ሰዎች፣ እንዲሁም ለህመሙ ተጋላጭ የሆነባቸውን ተዋህስያን ምንጭ የመለየት ሥራ (ትሬሲንግ) ነው፡፡ ይህም የተጀመረው በህንድ፣

በእንግሊዝና በራሺያ ተከስተው ሰፊ አካባቢዎችን ከሸፈኑ የኮሌራ ወረርሽኞች በኋላ እንደነበር በአሜሪካው ሀርቫርድ ዩኒቨርሲቲ የህክምና ታሪክ አጥኚ የሆኑት ግራሃም ሞኒ ይናገራሉ፡፡

በዓለም የህክምና ታሪክ ክፉው ወረርሽኝ የሚባለው የ1918 የስፓኒሽ ፍሉ ደግሞ እንቅስቃሴ ሙሉ በሙሉ መገደብን እንደ አንድ መፍትሔ መውሰድን ዓለም የተማረበት መሆኑን ባለሞያዎች ያስረዳሉ፡፡ ብዙዎቹ የተከሰቱ የጉንፋን ወረርሽኞች ያስተማሩት ሁነኛ ትምህርት ደግሞ አገራት በደንብ የተደራጁ የበሽታ ቁጥጥር ማዕከላትን ማቋቋም እጅግ አስፈላጊ መሆኑንና ዓለም አቀፍ ትብብር ወሳኝ እንደሆነ ነበር፡፡ ይህን ተከትሎ ነበር አሜሪካ ሲዲሲ የተባለውን የበሽታ ቁጥጥር ማዕከል ያቋቋመችው፡፡ የዓለም ጤና ድርጅትም የተቋቋመው በዚህ እሳቤ ነበር፡፡ ይሁንና ዓለም ወረርሽኞችን ሙሉ በሙሉ ለመቆጣጠርና እንዳይከሰቱም ጭምር ለማድረግ የምትችልበት አቅም ላይ አልደረሰችም፡፡ የክትባቶችና የጸረ-ተዋህስያን መድኃኒቶች መፈጠር፣ እንዲሁም የተሻለ አቅም ያላቸው የጤና ተቋማትን በብዙ ሀገራት መገንባት መቻሉ ከወረርሽኞች መመከት የተወሰዱ ትምህርቶች ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡

ይሁንና ወረርሽኞችን የመመከት አቅም፣ ከቀደሙ ጉዳቶች ተምሮ ጠንካራ ግንዛቤ ያለው ማኅበረሰብና የጤና ስርዓት መገንባት ለብዙ ደሃ ሀገሮች ፈታኝ ነው፡፡ ኢትዮጵያውያንንም የፈተነው የቀደመ ወረርሽኝ ኢንፍሉዌንዛ ብቻ አልነበረም፡፡ ከ16ኛው ክፍለ ዘመን አንስቶ የተከሰቱ እንደ  ታይፈስ፣ንዳድ፣ኮሌራ፣ፈንጣጣ ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህ ወረርሽኞች ከጦርነትና ድርቅ ጋር ተደምረው የቀደሙ ዘመናት መሪዎች የሰልጣን ዘመንን በብዙ ፈትነዋል፡፡ እነዚህን ወረርሽኞች በቅጡ ተረድቶ ምላሽ ለመስጠት፣ ዳግም እንዳይከሰቱም ብልሃት ለማበጀት የቀደሙት ነገሥታትና መሪዎች የየአቅማቸውን ቢጥሩም፣ በዘመናቱ የነበረው የሳይንስ ዕውቀት አነስተኛ መሆን፣ የባለሞያ እጥረትና የዘመናዊ መድኃኒት እጦት ኢትዮጵያን ከጦርነት ባላነሰ ብዙ ዋጋ አስከፍሏታል፡፡

የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎች

፩. ኳራንቲ የሚለው ቃል የያዘውን ፍች ግለጹ፡፡

፪. እስካሁን ባነበባችሁት የምንባብ ክፍል ውስጥ የተጠቀሰውን የተላላፊ በሽታ ዓይነቶች ግለጹ፡፡

፫. በምንባቡ መሠረት ኢትዮጵያን ከጦርነት ባላነሰ የጎዳት ምንድን ነው?

ሀገራችንም ሆነች ዓለማችን በተለያዩ ጊዜያት በተከሰቱ ወረርሽኞች አልፈዋል፡፡ እያንዳንዱ ወረርሽኝ ና ጥፋት ዛሬ ላይ ዓለም ለደረሰበት ስልጣኔ ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል፡፡ ይህ አዎንታዊ ጎናቸው ነው፡፡ በቅርቡ የተከሰቱት እንደ ሳርስና ኢቦላም ለሰው ልጆች የማስጠንቀቂያ ደወል ሆነው አልፈዋል፡፡ በታሪክ ውስጥ ከፍተኛ ተጽዕኖ ፈጥረው የነበሩ እንደፈንጣጣ፣ ኩፍኝና ፖሊዮ ያሉት በክትባት ኃይል እንዲጠፉ ተደርገዋል፡፡ ይህ ክትባት እስኪገኝ ድረስ ግን ረጅም ጊዜ ፈጅቷል፤ ብዙ ጥፋቶችንም አስከትለዋል፡፡ ቫይረሶች በባህሪያቸው አስቸጋሪ ናቸው፤ እንደባክቴሪያ በቀላሉ በፀረ-ባክቴሪያ መድኃኒቶች የምናክማቸው አይደሉም፡፡ ለአብነት እንኳ ባለፉት 40 ዓመታት ውስጥ 40 ሚሊዮን ሕዝብ የጨረሰውን ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ማጤኑ በቂ ነው፡፡ ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ ፈውስና ክትባት የለሽ የዓለማችን ሌላኛው የቫይረስ ወረርሽኝ መሆኑ ይታወቃል፡፡

ኮቪድ-19 በመባል የሚጠራው አዲሱ ወረርሽኝም ልክ እንደ ፍሉ-18 ከሰውና ከእንስሳት ዝርያ የተቀዳ በመሆኑ ከአሁን ቀደም በሰዎች ዘንድ ሲሰራጭ የነበረው የኮሮና ቫይረስ ከእንስሳት ኮሮና ጋር በመዳቀል የተገኘ አዲስ ዓይነት ዝርያ ነው፡፡ አዲስ ዲቃላ ቫይረስ በመሆኑም “ኖቭል” ( አዲስ ) የሚል ቅጥያ ተሰጥቶታል፡፡ ቻይና ውስጥ ታህሳስ 30/2019 እ.ኤ.አ. ለመጀመሪያ ጊዜ ውሀን ግዛት ውስጥ የታየው ቫይረስ ቀድሞ እንስሶችን ብቻ ያጠቃ የነበረና ሰውን ወደማጥቃት የተቀየረ ስለነበር ነው የውሀን ቫይረስ የ2019 ኖቭል ኮሮና ቫይረስ የተባለው፡፡

ስለቫይረሱ አጀማመር የተሰጠው መላምትም የቫይረሱ ተሸካሚዎች ከሆኑት እንስሳት (የሌሊት ወፍ፣ ድመት፣ ከብት፣ ግመል ወይም እባብ) አፈጣጠሩን በመቀየር ከእንስሳቱ ጋር ቀጥታ ንክኪ ወደነበራቸው ሰዎች ተዛመተ የሚለው ነው፡፡ ቫይረሱ አንዴ የሰው ልጅ ህዋሳት ውስጥ ከገባ ራሱን በማባዛትና ኢንፌክሽን

በማምጣት የበሽታውን ምልክቶች ያሳያል። እስካሁን ድረስ የወረርሽኙ ምንጭ በትክክል አልታወቀም። ቫይረሱ የጤናና የደህንነት ደንቦችን ካላከበረ የውሀን የባህር ምግቦችና የእንስሳት ገበያ ጋር የተገናኘ ነው የሚል እምነት አለ። ይህ የውሀን ገበያ ወዲያውኑ እንዲዘጋ አድርጎታል።

ኮሮና ቫይረስ በአሁኑ ወቅት በዓለማችን ውስጥ ባሉ ሀገሮች ውስጥ በመዛመት ላይ ያለ ወረርሽኝ ሲሆን፣ ወረርሽኙን አስፈሪ ያደረገው እንደ አብዛኛዎቹ በቫይረስ የተነሳ የሚመጡ ህመሞች ሁሉ ፈዋሽ መድኃኒት የሌለው መሆኑ ነው። በሽታው በአጭር ጊዜ እንዲሰራጭ ያደረገው ደግሞ በቀላሉ በትንፋሽና በንክኪ መተላለፍ መቻሉ ሲሆን፣ይህም አደገኛነቱ የላቀ እንዲሆን አድርጎታል። ከሰዎች ጋር በቅርበት በማውራት እና በእጅ በመጨባበጥ ፣ እንዲሁም ሰዎች የነኩትን ነገር በመንካት በቀላሉ ሊተላለፍ ይችላል።

ቫይረሱ በዋናነት ሳንባን፣ ልብንና ኩላሊትን ያጠቃል። የሳንባ አየር አስተላላፊ ህዋሳትን በማሳበጥና ሳንባ ሙሉ በሙሉ ሥራውን እንዳይሠራ በማድረግ የመተንፈስ ስርዓትን የሚያስቆም ሲሆን፣ ኩላሊትንም ደምን የማጣራት ተግባሩን እንዳይሠራ በመከላከል ያዳክማል። በእነዚህ ባህርያቱ የተነሳ በሽታው ገዳይ ሊሆን ይችላል።

ኖቭል ኮሮና ቫይረስ በሁሉም የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ሰዎችን እንደሚያጠቃ ተረጋግጧል፤ ይሁን እንጂ እንደማንኛውም የቫይረስ ኢንፌክሽን ሁሉ የተወሰኑ ሰዎች በሽታው ይጸናባቸዋል፤ ህፃናት፣ አረጋውያን፣ በሽታ የመከላከል አቅማቸው የተዳከመ ሰዎች፣ የስኳር ህመም፣ የልብ ህመም፣ የኩላሊት መድከም፣ የጉበት ህመም፣ አስም፣ የሳንባ ህመም እና ሌሎች የመተንፈሻ አካል ችግሮች ያለባቸው ሰዎች ቫይረሱ በቀላሉ ህመም ሊፈጥርባቸው ይችላል። ከታመሙ በሽታው በጣም ሊጸናባቸው ይችላል። ራሳችንንና በዙሪያችን ያሉ ሰዎችን ከቫይረሱ ለመከላከልም ትክክለኛውን የመከላከያ እርምጃዎች መውሰድ፣ ዙሪያችንንም መከታተል አለብን።

የኮቪድ-19 ሁነኛ የመከላከያ መፍትሄዎቹም አዘውትሮ እጅን በውሃና በሳሙና መታጠብ፣ ከተፋፈጉ ቦታዎች አለመገኘትና እና ከሚያስሉና ከሚያነጥሱ ሰዎች በቂ ርቀት ማበጀት፣ እንዲሁም በአጠቃላይ ንፁህ ሆኖ መገኘት ነው። ከዚህ ውጪ

ይፋዊ መግለጫዎችን ከጤና ምኒስቴርና ተመሳሳይ ተቋማት እንዲሁም ተዓማኒ የመረጃ ምንጮች ብቻ በመውሰድ ራስን ማስታጠቅና መምራት ወረርሽኙን ለማሸነፍ፣ በጤናም ለመሰንበት ያግዛል፡፡ ደጋግመን ጠያቂ ከሆንን መላ ምቶቹን ማክሸፍ ይቻላል፡፡

(ምንጭ፡- አቡሽ አያሌውና ሌሎች (ዓ.ም. ያልተጠቀሰ) የኮሮናው መብረቅ ከሚለው ላይ ለማስተማሪያነት ተሻሽሎ የተወሰደ)

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

፩. ለሚከተሉትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሠረት በማድረግ በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ መልሳችሁን በጽሑፍ አስፍሩ፡፡

ሀ. በምንባቡ ውስጥ የተገለጹትን የመተንፈሻ አካላትን የሚያጠቁ በሽታዎችን ዘርዝሩ፡፡

ለ. በምንባቡ መሠረት የኢንፍሉዌንዛ ወረርሽኝ በአዲስ አበባ የገደለው የሰው ቁጥር ምን ያህል ነው? በተቀረው የሀገሪቱ ክፍልስ?

ሐ. በምንባቡ ውስጥ ህዳር 12 “ህዳር ሲታጠን” በሚል ስያሜ ቆሻሻዎችን እየሰበሰቡ የሚያቃጥሉት ለምንድን ነው?

መ. የመተንፈሻ አካላትን የሚያጠቁ በሽታዎች ከኮቪድ-19 (ኮሮና) ጋር የሚያመሳስሏቸውን ባህርያት ግለጹ፡፡

ሠ. ዓለም ከቀደሙት ወረርሽኞች በመነሳት ወረርሽኙን ለመገደብ ያስቀመጣቸው መፍትሔዎች ምን ምን ናቸው?

ረ. ኮቪድ-19 (ኮሮና) የሚያጠቃው በየትኛው የዕድሜ ክልል ያለን ሰው ነው?

ሰ. የኮቪድ-19 የመከላከያ መፍትሔዎች ምን ምን ናቸው?

፪. ከዚህ በታች የቀረቡት ቃላትና ሀረጋት በምንባቡ ውስጥ የያዙትን አገባባዊ ፍች በጽሁፍ አመልክቱ፡፡

ሀ. የቀጠፈ　　　　ለ. ከታቢዎች

ሐ. የኑሮ ዘዬ　　　　መ. ተህዋስያን

ሠ. በቅጡ

፫. በምንባቡ ይዘት ላይ በቡድን በመሆን ከተወያያችሁ በኋላ የምንባቡን ዋና ዋና ነጥቦች ለይታችሁ ጻፉ፡፡

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

፩. የአንቀጽን አጻጻፍ ስልት በመከተል የምንባቡን ዋና ሀሳብ በአንድ አንቀጽ ጻፉ፡፡

፪. ኮቪድ-19 (ኮሮና) በአካባቢያችሁ ላይ ያመጣውን ተጽዕኖ እና የመከላከያ እርምጃዎቹ ምን እንደሆኑ የሚያመለክት አንድ የተሟላ ጽሁፍ ጻፉ፡፡

፫. ኮቪድ-19 የመተንፈሻ አካልን የሚያጠቃ በሽታ ነው፡፡ ይህ በሽታ በዓለም ዙሪያ ከመንግስታት አንስቶ እስከ ግለሰብ ለኢኮኖሚያዊ እና ለማህበራዊ ህልውና መቃወስ ምክንያት ሆኗል፡፡ እናንተም በኮቪድ-19 (ኮሮና) እና በኤች.አይ.ቪ/ኤድስ መካከል ስላለው አንድነትና ልዩነት በቡድን በመሆን ከተወያያችሁ በኋላ የደረሳችሁበትን ሀሳብ በጽሑፍ አስፍሩ፡፡

፬. የሚከተሉትን ምስሎችና ስዕሎች መሠረት በማድረግ "የኮቪድ-19 (ኮሮና) ምልክቶች" በሚል ርዕስ የጽሁፍ መመሪያ በማዘጋጀት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አንብቡላቸው፡፡




## ክፍል አምስት፡- ቃላት

፩. ቃላት ጠብቀውና ላልተው ሲነበቡ የፍች ልዩነት ያስከትላሉ፡፡ ከዚህ በታች የቀረቡትን ቃላት የንበት ልዩነት ለመረዳት በማጥበቅና በማላላት ካነበባችሁ በኋላ በሁለቱም የንበት ሁኔታ የሚኖራቸውን ፍች ጻፉ፡፡

ሀ. ጎልቶ ለ. መሳል ሐ. አብላ መ. ያለው

ሠ. አያት ረ. ፍራሽ ሰ. አዛባ ሽ. አይበላም

ቀ. አማት በ. አዘመረ ተ. ዐባይ

፪. የሚከተሉትን ቃላት በፊደል ተራ ቅደም ተከተል አስተካክላችሁ ጻፉ፡፡

ሀ. ብርቱ ለ. ኃይለኛ ሐ. ክረምት መ. ፍቅር

ሠ. ኢትዮጵያ ረ. ዑደት ሰ. ወጣትነት ሽ. ጉሬዛ

ቀ. ወይፈን በ. ቢጋር ተ. ደረጀ

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

### ቅጥያዎች

በቃል ላይ ተለጥፈው ወይም ተቀጥለው የሚገኙ ጥገኛ ምዕላዶች ቅጥያዎች ተብለው ይጠራሉ፡፡ ለምሳሌ "ከቤታችሁ" በሚለው ቃል ላይ "ከ-" እና "-ኣችሁ" የሚሉት ጥገኛ ምዕላዶች "ቤት" በሚለው ቃል ላይ ተቀጥለው የሚገኙ ቅጥያዎች (ጥገኛ ምዕላዶች) ናቸው፡፡

ቅጥያዎች ከሚቀጠሉበት ቦታ አኳያ የሚከተሉትን ስያሜዎች ይዘው ይገኛሉ፡፡ እነሱም፡-

**ሀ. ቅድመ ዐምድ ቅጥያ፡-** ከሚቀጠልበት ቃል መነሻ (መጀመሪያ) ላይ ታክሎ የሚገኝ ቅጥያ ነው፡፡

ምሳሌ፡-

"ከታች" ---> "ከ-" "ታች" በሚለው ቃል መጀመሪያ ላይ በመቀጠሉ ቅድመ ዐምድ ቅጥያ ተብሎ ይጠራል፡፡

**ለ. ውስጠ ዐምድ ቅጥያ፡-** በሚቀጠልበት ቃል መካከል (ውስጥ) ላይ የሚገኝ ቅጥያ ነው፡፡

ምሳሌ፡-

"ሰፋፊ" ---> "-ፋ-" "ሰፊ" በሚለው ቃል መካከል ላይ በመቀጠሉ ውስጠ ዐምድ ቅጥያ ተብሎ ይጠራል፡፡

**ሐ. ድህረ ዐምድ ቅጥያ፡-** ከሚቀጠልበት ቃል መድረሻ (መጨረሻ) ላይ ተቀጥሎ የሚገኝ ቅጥያ ነው፡፡

ምሳሌ፡-

"ቤታቸው" ---> "-ኣቸው" "ቤት" በሚለው ቃል መድረሻ ላይ በመቀጠሉ ድህረ ዐምድ ቅጥያ ትብሎ ይጠራል፡፡

ከላይ በቀረቡት ምሳሌዎች ላይ “ታች”፣ “ሰፊ” እና “ቤት” የሚሉት በየተራ “ከ-“፣ “-ፉ-” እና “-ኣቸው” የሚሉትን ቅጥያዎች ያስከተሉ በመሆናቸው ምክንያት“ዐምድ” ተብለው ይጠራሉ፡፡

(ምንጭ፡- ጌታሁን አማረ (1989) የአማርኛ ሰዋስው በቀላል አቀራረብ ከሚለው ላይ ለማስተማሪያነት ተሻሽሎ የተወሰደ፡፡)

፩. በሚከተሉት ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ በሚገኙት ባዶ ቦታዎች ላይ ተገቢውን ቅጥያ አስፍሩ፡፡

ሀ. ትልም በልቦለድ ትረካ ______ ፊት የሚፈጸም ድርጊትን ያመለክታል፡፡

ለ. ሰው ______ ______ አነበቡት ______ ቶሎ ይረዳሉ፡፡

ሐ. ______ ደራሲው ምናብ ______ ፈጠራ ______ ሚጻፍ ጽሁፍ ልቦለድ ድርሰት ይባላል፡፡

መ. ______ አንቀጽ ውስጥ የሚገኝ ______ ዐረፍተ ነገሮች በሙሉ በአንድ ሀሳብ ዙሪያ የሚያጠነጥን ______ መሆን ይኖርባቸዋል፡፡

ሠ. አንድ ሰው ልቦለድ ______ አነበበ በኋላ ላላነበቡ ሰዎች ______ ቀድሞ የሚነግራቸው ______ ልቦለዱን ታሪክ ነው፡፡

፪. በሚከተሉት ቃላት ውስጥ የሚገኙትን ዋና ቃል ወይም ነጻ ምዕላዱን፣ ቅድመ ዐምድ ቅጥያ እና ድህረ ዐምድ ቅጥያ ለያይታችሁ ጻፉ፡፡

ሀ. በባህላዊ

ለ. ወገናዊነቱን

ሐ. ነጫጭ

መ. ከሰዋዊ

ሠ. እናንተን

ረ. ከሰንሰለታማው

ሰ. ስለዘመዶቻቸው

# የምዕራፉ ማጠቃለያ

ምዕራፍ ሰባት ኮቪድ-19 (ኮሮና) በሚል ርዕስ የቀረበ ነው፡፡ በምዕራፉ የማዳመጥ ክፍል ውስጥ በምንባቡ ርዕስ መነሻነት የቫይረሱን ምንነት፣ ምልክቶች እና በመሳሰሉት ይዘቶች ዙሪያ ተወያይታችኋል፤ የምንባቡንም ዋና ዓላማ ገልጻችኋል፤ በተገቢ ሆሄያት የተዋቀሩ ቃላትንም በመጠቀም ለጽሁፉ የማጠቃለያ ሀሳብ ሰጥታችኋል፡፡

በክፍል ኹለት በይነ መረብን ወይም ሌሎች የመረጃ ምንጮችን በመጠቀም በኮቪድ-19 ፅኑ ህመም የመያዝ ዕድላቸው ሰፊ እንዲሆን ሊያደርጉ የሚችሉትን የህመም ዓይነቶች በሚመለከት መረጃዎችን ሰብስባችኋል፤ ያገኛችሁትንም መረጃ መነሻ በማድረግ ዘገባ አዘጋጅቶ ማቅረብን ተለማምዳችኋል፡፡ በቡድንም በመሆንም በጥያቄው በቀረበው ርዕስ ላይ በቡድን ሆናችሁ በመከራከር ክርክር የማቅረብ ሂደትን ተምራችኋል፡፡

በክፍል ሦስት የቀረበውን ምንባብ በማንበብ ለአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች ምላሽ ሰጥታችኋል፡፡ የቃላትን ዐውዳዊ ፍች ገልጻችኋል፤ የምንባቡንም ዋና ዋና ነጥቦች ለይቶ ማውጣትን ተምራችኋል፡፡

በክፍል አራት ጽሕፈትን በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ አንቀጽ መጻፍን ተምራችኋል፡፡ የቀረቡትን ምስሎች መሠረት በማድረግም "የኮቪድ-19 (ኮሮና) ምልክቶች" የሚል ርዕስን በመጠቀም የጽሑፍ መመሪያ ማዘጋጀትን ተምራችኋል፡፡

በክፍል አምስት የቀረቡትን ቃላት በማጥበቅና በማላላት በትክክል መጥራትን፣ ቃላት ጠብቀውና ላልተው ሲነበቡ የፍች ልዩነት እንደሚያስከትሉ፣ ቃላትን በፊደል ተራ ቅደም ተከተል ማስቀመጥን ተምራችኋል፡፡

በክፍል ስድስት ደግሞ ቅጥያዎች በቃል ላይ ተጨማሪ ሆነው የሚገቡ መሆናቸውን፣ ከሚቀጠሉበት ቦታም አኳያ ቅድመ፣ ድህረ እና ውስጠ ዓምድ ቅጥያ ተብለው ሊጠሩ እንደሚችሉ፣ በቃላት ላይ የተጓደሉ ቅጥያዎችን በመቀጠል ሀሳቡን ማሟላትን፣ ከቃላት ላይ ቅጥያዎችን መለየትን ተምራችኋል፡፡

## የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

፩. ቅጥያ ማለት ምን ማለት ነው

፪. ጠብቀውና ላልተው በመነበብ የተለያዩ ፍቺዎችን የሚሰጡ ሦስት ቃላትን ጻፉ።

፫. በሚከተሉት ቃላት ላይ የተቀጠሉትን ቅጥያዎች ለይታችሁ አመልክቱ

ሀ. ሰባበረው

ለ. ርቀታቸውን

ሐ. ነገረኛነቱን

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ ሰባት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ቅጽ ቀርቦላችኋል፡፡ በዚህም መሠረት በእያንዳንዱ ማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ቅጹን አሟሉ፡፡

| | የማመሳከሪያ ነጥቦች | √ | ? | X |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ያዳመጥኩትን ምንባብ ዋና ዓላማ መግለጽ ችያለሁ | | | |
| 2 | በይነ መረብን በመጠቀም መረጃዎችን መሰብሰብ ችያለሁ | | | |
| 3 | ከተለያዩ ምንጮች ያገኘኋቸውን መረጃዎች በዘገባ መልክ ማቅረብ ችያለሁ | | | |
| 4 | የጽሁፍን ዋና ሀሳብ በአንድ አንቀጽ መግለጽ ችያለሁ | | | |
| 5 | ቃላትን በማጥበቅና በማላላት በማንበብ በትክክል መጥራት ችያለሁ | | | |
| 6 | የፊደል ገበታን በመጠቀም ቃላትን በቅደም ተከተል መደርደር ችያለሁ | | | |
| 7 | በዐረፍተ ነገሮች ውስጥ ቅድመ ዐምድ እና ድህረ ዐምድ ቅጥያዎችን በማስገባት ዐረፍተ ነገሮቹን ማሟላት ችያለሁ | | | |
| 8 | በቃላት ላይ ተቀጥለው የሚገኙትን ቅድመ ዐምድ እና ድህረ ዐምድ ቅጥያዎች ከዋና ቃል ላይ መለየት ችያለሁ | | | |

፪. ከዚህ በላይ በቀረበው ቅጽ የ(?) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትገነዘቡ ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

አማርኛ

(፱ኛ) ክፍል

## ምዕራፍ ስምንት፡- ተውኔት

**የምዕራፉ ዓላማዎች፡-**

**ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፣**

- ❖ ተውኔት በውስጡ የሚያጠቃልላቸውን ፍሬ ነገሮች በመለየት ትገልጻላችሁ፡፡
- ❖ የተውኔት ዓይነቶችን ታብራራላችሁ፡፡
- ❖ የተለያዩ የተውኔት ጭብጦችን ትገልጻላችሁ፡፡
- ❖ የተውኔት ረቂቅ ትጽፋላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

# የተውኔት ምንነትና አላባውያን

### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

፩. ተውኔት ምንድን ነው? በቡድን በመሆን ተወያዩና መልሳችሁን በቡድን ተወካያችሁ አማካይነት ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

፪. ከዚህ በፊት በሬዲዮ ካዳመጣችሁት፣ በቴሌቪዥን ወይም በመድረክ ከተከታተላችሁት ተውኔት የትኛውን ታስታውሳላችሁ? የምታስታውሱትን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ንገሯቸው፡፡

፫. ተዋንያን ማለት ምን ማለት ይመስላችኋል?

### የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

ሀ. እስካሁን ካዳመጣችሁት የምንባብ ክፍል ምን ምን ጉዳዮች ተነስተዋል?

ለ. ተውኔት በመድረክ ላይ እስኪቀርበ ድረስ ተሳታፊ ከሆኑት ባለሙያዎች ቢያንስ ሁለቱን ግለጹ፡፡

ሐ. አንድ የተውኔት ጽሁፍ ለመድረክ እንቅስቃሴ እንዲበቃ አስፈላጊውን ዝግጅት እንዲደረግ ሀላፊነቱን የሚወስደው የትኛው ባለሙያ ነው?

### የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

፩. ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ያዳመጣችሁትን ምንባብ መሠረት በማድረግ ትክክል ለሆኑት “እውነት”፣ ስህተት ለሆኑት ደግሞ “ሐሰት” በማለት መልሱ፤ ምክንያታችሁንም ግለጹ፡፡

ሀ. ተውኔት ከሌሎች የስነጽሁፍ ዘሮች መድረክ ላይ መቅረቡ ያመሳስለዋል፡፡

ለ. በተውኔት ገጸ-ባህርያት ተዋንያንን ወክለው መድረክ ላይ ጥበቡን ይከውናሉ፡፡

ሐ. በተውኔት ውስጥ የሚታይ የፍላጎት አለመጣጣም ወይም ቅራኔ ግጭት ይባላል፡፡

መ. አንድ ተውኔት ከአንድ በላይ ንዑስ ጭብጥ ሊኖረው አይችልም፡፡

ሠ. የአንድ ተውኔት ትርጉም ከተውኔት አላባዎች ይመዘዛል፡፡

፪. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ባዳመጣችሁትን ምንባብ መሠረት ከተሰጡት አራት አማራጮች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ፡፡

1. _________ የምክንያትና ውጤት ትስስር ነው፡፡

ሀ. ሴራ ለ. መቼት

ሐ. ቃለ-ተውኔት መ. ጭብጥ

2. አንድ ተውኔት የሚከናወንበትን ቦታ እና ጊዜ የሚያመለክተው የተውኔት አላባ _________ ይባላል፡፡

ሀ. ገጸ-ባህርይ ለ. ትልም

ሐ. ቃለ-ተውኔት መ. መቼት

3. በተውኔት ውስጥ ገጸ-ባህርያት እርስ በእርሳቸው የሚያደርጉት የምልልስ ንግግር ምን ይባላል?

ሀ. ቃለ-ምልልስ ለ. ቃለ-ተውኔት

ሐ. መቼት መ. ሴራ

4. የአንድ ተውኔት ማዕከላዊ ሀሳብ ምን ተብሎ ይጠራል?

ሀ. ቃለ-ተውኔት ለ. ግጭት

ሐ. ሴራ መ. ጭብጥ

5. ተዋንያን የሚወክሉትን ገጸ-ባህርይ ሆነው እንዲገኙ የሚያስችሉ ባለሙያዎች ምን በመባል ይጠራሉ?

ሀ. የቅብ ወይም የስዕል ባለሙያ

ለ. የድምጽና የሙዚቃ ባለሙያ

ሐ. የሜካፕና ያልባሳት ባለሙያ

መ. ጸሐፊ ተውኔትና መራሄ-ተውኔት

፫. ቀጥሎ ለቀረቡት ጥያቄዎች ያዳመጣችሁትን ምንባብ መሠረት በማድረግ በቡድን በመወያየት መልሳችሁን በፅሁፍ ግለጹ፡፡

1. ተውኔት ከሌሎች የስነ-ጽሁፍ ዘርፎች ጋር ያለውን አንድነት እና ልዩነት ግለጹ፡፡

2. በመቼት ገለጻ ውስጥ ያሉትን የአገባብ ዋና ዋና ክፍሎች ዘርዝሩ፡፡

3. የመራሄ-ተውኔትንና የጸሃፊ-ተውኔትን ምንነት አብራሩ፡፡

## ክፍል ኹለት፡- መናገር

ከዚህ በታች አንድ የተውኔት ትዕይንትን የሚያመለክት ጽሁፍ ቀርቦላችኋል፡፡ ተውኔቱን ከየቡድናችሁ አንድ ወንድ እና አንድ ሴት ተማሪ በመሆን የገጸባህርያቱን ምልልስ እየተቀባበላችሁ ካነበባችሁ በኋላ ከጽሁፉ በታች የተገለጹትን ተግባራት አከናውኑ፡፡

### ትዕይንት

ተማሪ-1 (ትግስት)፡- ታዲያስ! ደህና ነህ ወይ አክሊሉ?

ተማሪ-2 (አክሊሉ)፡- እባክሽ ተይኝ፡፡ ደህና ሆንኩ አልሆንኩ ምን ዋጋ አለው?

ተማሪ-1፡- እንዴ! ምን ሆንክ? የግዜር ሰላምታ ካስጠላህ ምን ያህል ጊዜ ሆነህ? እንደኛው ዱርዬዎች አስቸገሩህ እንዴ?

ተማሪ-2፡- እነሱስ ከኔ ምን ይፈልጋሉ ብለሽ ነው? አሉ እንጂ  የባሉ፡፡
ተማሪ-1፡- ከፈተና ወደኩ እንዳትለኝ!

ተማሪ-2፡- ድሮስ? አጭበርብረው አልያም በዓይናቸው ጥራት ተጠቅመው ከሚያልፉ በስተቀር እንደኔ አይነቱ እንዴት ያልፋል ብለሽ ነው?

ተማሪ-1 ፡- አንተስ በዓይን ጥራቱ መቼ ሰንፈህ ታውቃለህ? ጎበዝ አልነበርህም?

ተማሪ-2፡- ነበርኩ፡፡ አላስበላ ሲለኝስ? ሲሰያስፎግረኝስ? ያ ፋራ!ያ መናጢ ተማሪ!

ተማሪ-1፡- የቱ ነው መናጢ? የቱ ነው ፋራ ተማሪ?

ተማሪ-2፡- ያ የህብር ሽርከኛ ነዋ !

ተማሪ-1፡- የቱ ነው ደግሞ የህብር ሽርክ

ተማሪ-2፡- ያ አጉል ሀቀኛ ነኝ ባዩን ተማሪ ነዋ ከዚያ ላይ ቲቸርም! ብቻ ዛሬ

ጥሩ አይደለሁም፡፡

ተማሪ-1፡- ገና አሁን ዋሽህ አክሊሉ፡፡ በማታውቀው ነገር ውስጥ ገብተህ ባትፈተፍት መልካም ነው፡፡ ሀቀኛ የሚለው ስም ለቲቸር የተሰጣቸው ካለምክንያት አይምሰልህ! የሚያስተምሩትን ትምህርት ጠንቅቀው የሚያውቁ በመሆኑ ነው፡፡ ፈተናቸው ጠበቅ ይላል! ይህ ደግሞ ሊያስነቅፋቸው አይችልም፡፡ ፋራ ምትለውም ተማሪ በራሱ ሚሰራ ስለሆነ ለምን ትሰድበዋለህ?

ተማሪ-2፡- ኤዲያ! አንች ደግሞ ደርሰሽ የማይሆነውን ሁሉ ነው የምታሞካሽው! አለን እንጂ እንደናንተ ያልታደልን ደረቆች፡፡
ተማሪ-1፡- ኧረ ባክህ! እንዴት አምሮብሃል? እኛ ደግሞ ምንድን ነን? ማርክ ተዝቆ ይሰጣቸዋል ያለህ ማነው? ይህን ያጣ ወሬህን ብትተወው መልካም ነው!

ተማሪ-2፡- ተይ ባክሽ ያደባባዩን ነገር የጓዳ ምስጢር ልታደርጊው ነው? አሁን ማን ይሙት

ህብር በጭንቅላቷ ተማምና ነው የምታልፈው?ተደግፋ አይደል?
ስንቱን ሰቅላ በአናታቸው ሽርተቴ የምትጫወተው?

ተማሪ-1፡- አትሳሳት አክሊሉ፡፡ በሀቅ የሚሰሩትን ስም ለማጉደፍ አትሞክር፡፡ ህብርም በጭንቅላቷ የምትተማመን ለመሆኗ ከአንዴም ሁለት ጊዜ በሴክሽን ደረጃ መሸለሟን ህሊናህ አያጣውም፡፡ ስሟን ላጉድፍ ካላልክ በስተቀር! ቲቸር ሀቀኛም ቢሆኑ እገሌን… ከእገሌ፣ ወንዶችን ከሴቶች የማይለዩ፣ የማያዳሉ ሰው ናቸው ብል መሳሳት አይሆንብኝም፡፡ እና ስህተትህን በስህተት አትደጋግመው ይልቅ የራስህን ድክመት መመልከት አለብህ

ተማሪ-2፡- ካልሽ እሺ፡፡ እኔ ምን ላድርግ የሚባለውን ይዤ እኮ ነው፡፡ በርግጥ እኔም ራሴን መመልከት መልካም ነው አንችም እስካሁን ስህተቴን ልታርሚልኝ በመጣርሽ አመሰግንሻለሁ እታረማለሁም ለማንኛውም ቻው! (ተጨባብጠው ይለያያሉ)

ምንጭ፡- (ደበበ ኃይለጊዮርጊስ (2008) ቅድመ ኮሌጅ አማርኛ ተቀንጭቦ ለክፍል ደረጃው ተሻሽሎ የተወሰደ)

፩. ትዕይንት ምን እንደሆነ ተወያዩ፡፡

፪. ተውኔቱን የሚተውኑ ከየቡድናችሁ አንድ ወንድና አንድ ሴት ተማሪ ከመረጣችሁ በኋላ ተዘጋጅተው ለክፍል ጓደኞቻቸው ያቅርቡ፡፡

፫. በተውኔቱ ላይ ስለእያንዳንዱ ተዋናይ የቋንቋ አጠቃቀም ላይ ተወያዩ፡፡

፬. በቡድን ሦስት ሦስት በመሆን በተማሪዎች በቀረበው ተውኔት ላይ ያላችሁን ምልከታ በጽሁፍ ተንትናችሁ አቅርቡ፡፡

፭. የተውኔቱ ጽሑፍ በተማሪዎች ከመቅረቡ በፊት እና ከተተወነ በኋላ በተረዳችሁት እና ባሳደረባችሁ ተጽዕኖ ዙሪያ ተወያዩ፡፡ የውይይታችሁንም ሀሳብ በጽሑፍ አቅርቡ፡፡

## ክፍል ሦስት፡- ንባብ

# ዘለለኝ

### ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

ከዚህ በታች በቀረቡት ጥያቄዎች ላይ በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ የደረሳችሁበትን የጋራ ሀሳብ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

1. ተውኔት እና ድራማ በሚሉት ቃላት መካከል ያለው ልዩነት ምን ይመስላችኋል?

2. በአንድ ተውኔት ውስጥ ምን ምን ነገሮች ተካተው የሚገኙ ይመስሏችኋል?

3. ከዚህ በታች "ዘለለኝ" በሚል ርዕስ አንድ ተውኔታዊ ጽሁፍ ቀርቦላችኋል፡፡ ከርዕሱ በመነሳት ምን ትገምታላችሁ?

### ዘለለኝ (ክፍል አንድ)

የመቶ አለቃ ገበየሁ ቤት አንድ ክፍል ብቻ ይኑረው እንጂ በጣም ሰፊ ነው፡፡ በሁለት ትልልቅ መጋረጃዎች በመጠቀም ሁለት የተለያዩ ክፍሎች አበጅተውለታል፡፡ ከበሩ በስተግራ ያለው መስኮት በመጋረጃ ተጋርዷል፡፡ በውስጡ የእህል ማቅረቢያና ማብሰያ (የባልትና ዕቃዎች) ተቀምጠዋል፡፡ ከመግቢያው በር በስተቀኝ ትልቅ ቁም ሳጥን ቆሟል፡፡ ከቁም ሳጥኑ ቀጥሎ የመቶ አለቃ ገበየሁ አልጋ ተዘርግቷል፡፡ የአልጋው ዙሪያ ስስና ነጭ በሆነ መጋረጃ ታጥሯል፡፡ ከበሩ ፊት ለፊት አልጋው ወደተዘረጋበት ጥግ ሙሉ ወንበሮች ያሉት የምግብ ጠረጴዛ አለ፡፡ ቁርስ የተበላባቸው እቃዎች ለመታጠብ በትልቅ ትሪ ተሰብስበው መሬት ላይ ተቀምጠዋል፡፡

አስካለ ጠይምና ወፍራም፣ መካከለኛ ቁመት ያላት ናት፡፡ በለበሰችው የማዕድ

ቤት ልብሷ እጇን እየጠራረገች ከውጭ ገባች።

አስካለ፡- (ባልዲውን አንስታ ከውስጡ ባለው ውኃ ለቅለቅ ለቅለቅ ካደረገች በኋላ ከሚታጠበው እቃ ላይ ታፈስበታለች። የዕቃ ማጠቢያ ሳሙናና ጨርቅ አቅርባ ትቀመጥና ተመልሳ ትነሳለች።) አይ የኔ ነገር! በሃሳቤ ውኃ ላመጣ ልሄድ ነበር። ወይ ልቤ! ልቤን ምን በላው? ያለውኃ እቃ ይታጠብ ይመስል። የዚህ የቦኖ ውኃ ደግሞ ከመራቁም በላይ ወረፋው ቶሎ አይገኝም። እንዲያው ፍርጃ ነው ባካችሁ። (ባልዲዋን አንጠልጥላ እየወጣች) ልሂድና ልገተረው! (በሩን መለስ አድርጋው ትወጣለች። አንድ ደቂቃ ባልሞላ ጊዜ ውስጥ የተዘጋው በር ይከፈታል። ከግንባሩና ከአይኖቹ አካባቢ በስተቀር ሌላው መልኩ ባጎፈረ ጢም የለበሰ ሰውዬ በተከፈተው በር ብቅ ይላል። ከበሩ ላይ እንደቆመ ወደ ግራም ወደ ቀኝም ጥግ በአይኑ ያማትራል።)

ስም አይጠሬ፡- (ለማረጋገጥ) እዚህ ቤት! ቤቶች! (የስምአይጠሬ ጓደኛ ከኋላው ይመጣና ነካ ነካ ያደርገዋል። ሌላ ሰው የመጣበት መስሎት በድንጋጤ ለመሮጥ እየቃጣው) የማነ ነህ እንዴ? ምነው ቆሌየን ገፈፍከው? ከዚያው ሁነህ ጠብቅ።

የማነ፡- ዝም ብላ ባልዲዋን እንዳንጠለጠለች ወደታች ነጉዳለች።

ስም አይጠሬ፡- ተዋት ትሂድ! መሄዷን አይደለ የምንፈልገው። (የእገፋው) ይልቅ ፈጥነህ ሂድና ቅድም ካሳየሁህ ቦታ ቆመህ ጠብቅ። አሁን ከሰው ቤት ውስጥ ገብተን እንደቆምን ባለቤቱ ቢመጣ ምን ይባላል። በል ለማንኛውም ውጣና ዙሪያ ገባውን እየቃኘህ ጠብቅ።

የማነ፡- እንግዲህ ነቅተህ አዳምጠኝ። እሷ ስትመጣ ካየሁ እዚያው ከቆምሁበት ቦታ እንዳለሁ በፉጨት ነው የማሳውቅህ። ፉጨቱን ሳትሰማ ቀርተህ ግን ጉድ እንዳትሆን።

ስም አይጠሬ፡- (የየማነን ትከሻ መታ መታ አደረገ) ስማ የማነ እሷ ብቻ ሳትሆን ማንም ሰው ወደዚህ ግቢ ለመግባት አቅጣጫውን ከቀየረ ፉጨትህን ፊው ፊው አድርግልኝ።

የማን፡- እሺ፡፡ (ይሄዳል፡፡) ስምአይጠሬ ወደቤት ገብቶ የማብሰያ እቃዎች የተቀመጡበትን መጋረጃ ገልጦ ያያል፡፡ የረባ እቃ አለመኖሩን እንዳየ አልጋውን ወደሸፈነው መጋረጃ ይሄድና ይገልጣል፡፡ ወዲያው ወደበሩ ሮጦ ሄዶ ወደግራም ወደቀኝም ተገላምጦ አይቶ ሰው አለመኖሩን አረጋግጦ በኋላ ተመልሶ ይገባል፡፡ የአልጋውን መጋረጃ ሲገልጥ አዲስ ጃኬት በራስጌ ተንጠልጥሎ ያገኛል፡፡ ጃኬቱን አውርዶ የእሱን በማውለቅ ይለካል፡፡ ልክ መሆኑን እንዳረጋገጠ አውልቆ በእጁ ይይዛል፡፡ ሰው አለመኖሩን ለማረጋገጥ እንደገና ወደበሩ ይሮጣል፡፡ ከዚያም ተመልሶ ከአልጋው ስር አጎንብሶ ያያል፡፡ ጫማዎችን ተራ በተራ እያወጣ ካየ በኋላ አንዱን ጥቁር ቆዳ ጫማ መርጦ አውጥቶ በጃኬቱ ይጠቀልለዋል፡፡ ወደላይ ቀና ሲል ከቁም ሳጥኑ ላይ አንድ ሻንጣ ያያል፡፡ እሱን ለማውረድ ሲፍጨረጨር ፉጨት ተደጋግሞ ተሰማ፡፡ ስምአይጠሬ አልሰማም፡፡ ሻንጣውን አውርዶ አስተካክሎ ይዞ ሊወጣ ሲል አስካለ በሩን በባልዲው ገጭታ ትገባለች፡፡

አስካለ፡- እንግዲህ የቦኖው ውሃ ከጠፋ የት ተኬዶ ይቀዳል? ወጡስ እሺ ተሰርቷል፡፡ ቁርስ የተበላበት እቃ በምን ይታጠብ? (ስምአይጠሬ ባንድ እጁ ሻንጣውን በሌላ እጁ ጃኬቱንና ጫማውን እንደያዘ በአልጋው መጋረጃ ተከልሎ ይቀመጣል፡፡) እሰኪ እዚህ ታች ሰፈር ግማሽ ባልዲ ውሃ ልለምን ይሆን? እኔ የማውቀው ደግሞ ሰራተኛዋን እማዋይሽን ነው፡፡ ድንገት ባለቤቷ ከቤት ካሉስ? አፌን ሳላበላሽ እመለሳለሁ እንጂ ደፍሬስ እሳቸውን አልጠይቅም፡፡ (ባልዲውን ይዛ ትወጣለች፡፡) ይኸኔ ፉጨቱ ተደጋግሞ ይሰማል፡፡ መሄዷን ለማረጋገጥ አንገቱን ብቅ አድርጎ ሲመለከት በሩጫ ወደ ቤት ትገባለች፡፡ ውይ! ውይ! ወይኔ እድሌ የመቶ አለቃ መጡብኝ፡፡ እኔ ከላይ ከታች ስል ለካ የምሳ ሰዓት ደርሷል ለካ፡፡ (ለማጽዳት ያቀረበችውን እቃ ቶሎ ቶሎ ማጠብ ትጀምራለች፡፡ ስም አይጠሬ የያዘውን ሻንጣ እና ጃኬት ቀስ አድርጎ አስቀምጦ መደበቂያ ቦታ ይፈልጋል፡፡ ከዚያም ጫማውን ያወልቅና አልጋው ላይ ወጥቶ በአንሶላው ተሸፍኖ በጀርባው ይተኛል፡፡ የመቶ አለቃ ገበየሁ መለዮውን ለብሶ ከግራ ጎኑ ኮልት ሽጉጡን አገልድሞ ይገባል፡፡)

ገበየሁ፡- ምሳ ደርሷል ወይስ ትንሽ ያስጠብቃል?

አስካለ፡- ደርሷል ጋሼ፡፡

ገበየሁ፡- እስቲ እንግዲያስ ቶሎ አቅርቢልኝና በቁሜ ቀምሼ ልሂድ ጎሽ፡፡ በጣም እቸኩላለሁ፡፡ (ወደአልጋው ይሄድና መጋረጃውን ገልጦ የራስ ቆቡንና ሽጉጡን ካልጋው ጠርዝ ላይ ካስቀመጠ በኋላ ላቡን በፎጣ እየጠራረገ የተኛውን ሰውዬ ያየዋል፡፡ ዝቅ ባለ ድምፅ) ሰማሽ ወይ አንቺ አስካለ!

> **የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎች**
>
> 1. እስካሁን ባነበባችሁት ክፍል ተሳታፊ የነበሩት ገጸ-ባህርያት እነማን ናቸው?
> 2. ስምአይጠሬ የገባው እማን ቤት ነው? ምን ሊያደርግ?
> 3. ገበየሁ የተኛውን ሰውዬ ምን የሚያደርገው ይመስላችኋል?

አስካለ፡- (ገበየሁ ወደ ቆመበት እየሄደች) አቤት! አቤት! ምን አሉኝ?

ገበየሁ፡- ጋሼ ወንዳፍራሽ በስንት ሰዓት መጣ?

አስካለ፡- (ግራ ተጋብታ) ጋሼ ወንዳፍራሽ?

ገበየሁ፡- አዎ ጋሼ ወንዳፍራሽ፡፡ አታውቂውም እንዴ?

አስካለ፡- አላውቃቸውም፡፡

ገበየሁ፡- ከዚህ ቤት ከገባሽ ወዲህ መጥቶ አያውቅም ማለት ነው? ታዲያ ገብቶ ሲተኛ አላየሽውም? ከቤት ወጥተሽ ነበር?

አስካለ፡- አንድ ጊዜ ውሃ ላመጣ በሩን መለስ አድርጌ ቦኖው ጋ ወርጀ ነበር፡፡ ያኔ ይሆናል መጥተው የተኙት ( ድምጹን አጥፍቶ የነበረው ስም አይጠሬ እንቅልፍ የወሰደው አስመስሎ ያንኮራፋል፡፡)

ገበየሁ፡- ውሃ ለመቅዳት ከሄድሽ ለምን ዘግተሽው አልሄድሽም? በቁልፍ ዘግቶ መሄድ ከበደሽ? እሱ እንኳን አጎቴ ነው እንኳንም አልተዘጋበት፡፡

እንደአጋጣሚ በዚያ ሰዓት ሌባ ገብቶ ቢሆን የልቡን ሰርቶ ሄዶ ነበር ማለት ነው፡፡

አስካለ፡- ዘግቼው እኮ ነው የሄድኩ፡፡

ገበየሁ፡- እና ቁልፉን ሰብሮ ገባ ማለት ነው?

አስካለ፡- በቁልፍስ አልዘጋሁትም፡፡

ገበየሁ፡- ወደፊት እንዳይደግምሽ፡፡ የትም ይሁን የትም ቦታ እግርሽ ወጣ ካለ በቁልፍ ቆልፊሽ ሂጂ፡፡ በይ አሁን ቶሎ ምሳ አቅርቢ፡፡ (ገበየሁ እየታጠበ እያለ አስካለ ምግቡን አዘጋጅታ ጠረጴዛ ላይ አስቀመጠች፡፡) በይ አብረን እንድንበላ እንግዳውን ቀስቅሽው፡፡

አስካለ፡- (ስምአይጠሬን በእጇ እየነካካች) ጋሼ! ጋሼ! ይነሱ የመቶ አለቃ መጥተዋል፡፡ ... ይነሱ ይልዎታል፡፡ (ስም አይጠሬ እንቅልፍ ያሸነፈው በመምሰል "አአ..." ብሎ ተገላብጦ ተመልሶ ዝም ይላል፡፡) ጋሼ! አንቱ!

ገበየሁ፡- ጋሼ ወንዳፍራሽ ብለሽ መጥራት አቃተሽ?

አስካለ፡- ጋሼ ወንዳፍራሽ! ጋሼ ወንዳፍራሽ! ጋሼ ወንዳፍራሽ!

ገበየሁ፡- (ገበየሁ ከምግብ ጠረጴዛው አጠገብ እንደተቀመጠ) ጋሼ ወንዳፍራሽ! እንደምን ዋልክ? (መልስ አይሰጥም፡፡)

አስካለ፡- (እየወዘወዘች) ጋሼ! ጋሼ ወንዳፍራሽ! የመቶ አለቃ ይጠሩዎታል፡፡ (እንደገና "አአ..." ብሎ ከተገላበጠ በኋላ ዝም ይላል፡፡)

ገበየሁ፡- (የቀረበለትን ምግብ መብላት እየጀመረ) ተይው! ተይው! አስካለ ተይው በቃ ይለፍለት፡፡ የቀን እንቅልፍ መጥፎ አይደል፡፡ ተይው ሲጨርስ ይነሳ፡፡ (ፋታ) ስሚ አስካለ!

አስካለ፡- አቤት! ... (እየተጠጋች) ወጥ ልጨምር?

ገበየሁ፡- ትንሽ የተረፈ ቅራሪ የለሽም?

አስካለ፡- አለ፡፡ ቆይ ላምጣ፡፡

ገበየሁ፡- ቆይ! ቆይ! አስካለ!

አስካለ፡- አቤት፡፡

ገበየሁ፡- አንድ ጠርሙስ ብቻ ከሆነ ለጋሼ ወንዳፍራሽ ይቀመጥለት፡፡

አስካለ፡- አይ ሌላም አለ፡፡ አንድ ሁለት ያህል ይኖራል፡፡

ገበየሁ፡- (እየተጣደፈ እየጎረሰ) እንግዲያውስ አንዱን ወዲ በይው፡፡ (ቀድታ ስትሰጠው እየተቀበለ) ስሚ አስካለ

አስካለ፡- አቤት

ገበየሁ፡- ጋሼ ወንዳፍራሽ ሲነሳ ምሳውን ጋብዢው፡፡ ታዲያ ወጡን ሞቅ አድርጊለት፡፡ በረድ ብሏል፡፡ (በቁም ሳጥኑ መስታወት እያየ መለዮ ቆቡን ደፍቶ ሽጉጡን አንስቶ ከታጠቀው በኋላ እያስተካከለ) ሰዓቱም ከዚሁ እንዳለሁ ደረሰ፡፡ በይ የነገርኩሽን እንዳትረሺ፡፡ (ወጥቶ ከሄደ በኋላ እንደገና ተመልሶ ይገባና) ስሚ አስካለ ከመስሪያ ቤት ድንገት ልሂድ ካለ እንዳይመጣ ለቅሶ ብሎ ሌላ ቦታ ሄዷል በይው፡፡

አስካለ፡- እሺ እነግራቸዋለሁ፡፡ (የመቶ አለቃ ገበየሁ ወጥቶ እንደሄደ የፉጨት ጥሪ ተደጋግሞ ይሰማል፡፡)

ስም አይጠሬ፡- (ከእንቅልፉ መንቃቱን ለማሳወቅ እያዛጋ) ማነሽ አንቺ! ኤይ! …

አስካለ፡- (ስምአይጠሬ ጋ ሄዳ) አቤት ጋሼ ወንዳፍራሽ! … ጠሩኝ?

ስም አይጠሬ፡- አዎ ጠራሁሽ፡፡(ከተጋደመበት ተቻኩሎ ከተነሳ በኋላ አትኩሮ እያያት) እንዴ?… አንቺ ደግሞ ከየት መጣሽ? አዲስ ሰራተኛ ነሽ ልበል?

አስካለ፡- (እንደመሳቅ እያለች) ልክነዎት አዲስ ነኝ፡፡ ሰሞኑን ነው የመጣሁ፡፡

ስም አይጠሬ፡-እኔማ የጠራሁሽ የቀድሞዋ የማውቃት ሰራተኛ መስለሽኝ ነበር፡፡ ብቅ ስትይ አዲስ መልክ ሆነብኝና ደነገጥሁ፡፡

አስካለ፡-　　አስደነግጣለሁ ማለት ነው?

ስም አይጠሬ፡- አንቺ ምን በወጣሽ እቴ! የኔ አስተሳሰብ ነው እንጂ… የማላውቀው ሰው ከየት መጣ ብለሽ ያፋጠጥሽኝ እንደሆነ ደነገጥሁኝ…

አስካለ፡-　　(ስጋት እየታየባት) ኧረ እኔ አይወጣኝም፡፡

ስም አይጠሬ፡-(ከትብሎ ይስቅና) አይዞሽ ለቀልድ ያመጣሁት ነው፡፡ በይ ወንዳፍራሽ እባላለሁ እንተዋወቅ! (ይጨብጣታል) የመቶ አለቃ ገበየሁ አጎት ነኝ፡፡ ቅድም ስመጣ አልነበርሽም፤ የት ሄደሽ ኖሮ ነው?

አስካለ፡-　　ውኃ ላመጣ ወደ ቦኖ ወርጄ፡፡

ስም አይጠሬ፡- ታዲያ በር ተትቶ ይኬዳል ብለው መከሩሽ? የዘመኑ አይን አውጣ

ሌባ ክፍቱን አግኝቶ ይቅርና ሰብሮ ገብቶ መዝረፉን አታውቂም … ታውቂያለሽ ?

አስካለ፡-　　(እንደ መሽኮርመም እያለች) አውቃለሁ ኧረ፡፡

ስም አይጠሬ፡- አዎ ታውቂያለሽ! … ያለፈው አልፏል፤ ለወደፊቱ እንዳይለመድሽ፡፡ ገበየሁ መጥቶ ነበር እንዴ?

አስካለ፡-　　አዎ ምሳ በልተው ገና አሁን ወጡ፡፡

ስም አይጠሬ፡- እሱን ብየም አልነበር አመጣጤ? (በቁጭት)ምናለ ብትቀሰቅሱኝ ኖሮ! እስከነጭራሹ አላያችሁኝም ልበል?

አስካለ፡-　　ቀስቅሰነዎት ነበር ኧረ፡፡ መቶ አለቃ ምሳ ከኔ ጋር ይብላ ብለው ቀስቅሽው ስላሉኝ ለማስነሳት ብጎተጉት ብጎተጉት እንቅልፍ ተጭኖት አልነሳም አሉ፡፡

ስም አይጠሬ፡- (በብስጭት ያጨበጭብና) አዬ ሞት! እንቅልፍ የሞት ታናሽ ወንድም ነው ይባል የለ? ደህና አጋጥሞኝ የነበረው ሰውዬ እንደገና አመለጠኝ፡፡ በእንቅልፍ ሰመመን እያለሁ እሱ መሆኑን ሳላውቅ እንጂ የሰው ንግግር ይሰማኝ ነበር፡፡ እና በስንት ሰዓት እመጣለሁ አለ?

አስካለ፡- አስር ሰዓት እመጣለሁና ከቻልህ እስከዚያው ጠብቀኝ፡፡ (የተደጋገመ የፉጨት ድምፅ ይሰማል፡፡ ግን ስም አይጠሬ አላዳመጠውም)

ስም አይጠሬ፡- (በአነጋገሩም በእንቅስቃሴውም ዘና ብሎ አስቀድሞ ያወረደውን ጃኬት ለብሶ ያወለቀውን የራሱን አሮጌ ኮት ግድግዳው ላይ ይሰቅላል፡፡)የኔ ኮት ስለቆሸሸ የመቶ አለቃን ጃኬት ለብሻለሁ፡፡ (ካልጋው ስር ጎንበስ ብሎ ጫማውን ካየ በኋላ) ይሄ ጃኬት ደግሞ ከኔ ጫማ ጋር አይሄድም፡፡ እንግዲህ የተውሶ ልብስ ከለበሱ አይቀር ጫማውንም ሳድርግና ይለይልኝ፡፡ (ጫማውን አንስቶ ይጫማና አስካለን እየተመለከተ) ከቻልሽ ለቅለቅ አድርገሽ አስጭልኝ፡፡ (ጎንበስ ብሎ እየተመለከተ) ይሽ ጫማ ከልብሱ ጋር ይስማማል አይደል?

አስካለ፡- ይስማማል፡፡

ስም አይጠሬ፡- ደግሞ አንድ ነገር ጎደለኝ የወንድሜ ቢሆንም የተውሶ ከለበስኩ አይቀር ሽሚዙንም ብዋሰው አይከፋም፡፡ ማነሽ እንትናዬ "…የኔ ልጅ!" የቁም ሳጥኑ ቁልፍ የት ነው ያለው? ወይስ ይዞት ሄደ?

አስካለ፡- (በጣቷ እየጠቆመች) እዚያ ላይ ተቀምጧል ጋሽዬ… ከቁም ሳጥኑ አናት ላይ፡፡ (ቁልፉን ለማውረድ ሲንጠራራ የስም አይጠሬ ጓደኛ የማነ ከውጭ የተላከለትንና በበረዶ አገር የሚለበሰውን ባለጎፈር ቆቡን እስካንገቱ ድረስ አጥልቆ ይመጣና በሩ ላይ ይገተራል፡፡ አስካለ አስተውላ እያየችው) ማንን ፈለጉ?

ስም አይጠሬ፡- (በድንጋጤ ወደበሩ ሲሮጥ ጓደኛው መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ አስካለ እንዳትሰማቸው በወፍ ቋንቋ መነጋገር ይቀጥላሉ) ለዘምዝን መዘጣዛህ?

የማነ፡- እዛስዝር ጊዜ ሳዛፏዛጭዝልዝህ ለዘምዘን አዛታዛዳዛምዝጥዝም ወዘይዝስ ጆዞሮዞህ ተዘቆዞርጧዟል? እዝኔዜማዛ ገዘደዘሉዙት ወዘይዝስ ቆዞርዝጠዘው ጣዛሉዙት ብዝዬ ሲዘጨዘንቀዘኝ ጊዜ ዝምብዝዬዘ ገዘስግዝሼዜ መዘጣዛሁ፡፡ ለዘመዘሆኑ ቅዝድዝም ሰዘውዝዬዜው መዘጥዝቶ ሳዛለዘ እዝንዝዴዜት አዘመዘለዘጥዝክ? እዝሷዟስ እዝንዜዴዜት ዝዝምዝ አዘለዘችዝህ?

ስም አይጠሬ፡- በዘኂላዛ አዛጫዛውዝትዝሃዛለዘሁ፡፡

የማነ፡- (እየሄደ) እዝሽዚ ቶዞሎዞ ናዛ!!

ስም አይጠሬ፡- በይ እንግዲህ ደርሼ ልምጣ፡፡

አስካለ፡- (የስም አይጠሬን እጅ ትይዝና) ምሳዎትን ሳይበሉማ አይሄዱም!

ስም አይጠሬ፡- ስመለስ ይሻለኛል፡፡

አስካለ፡- አረ ይተዉ ወጡም ሞቋል በልተው ይሂዱ፡፡ ምን ያህል እንዳያቆይዎ ነው?

ስም አይጠሬ፡-አሁን እመለሳለሁ እያልኩሽ! ደግሞስ በገዛ ሆዴ ምን አግደረደረኝ ብለሽ ነው፡፡ ይልቅ መቶ አለቃ ከመጣ መልእክት ንገሪው (ወረቀት አውጥቶ እያጣጠፈ) ይቺን ማስታወሻ ስጪው፡፡ (ወደ በሩ እያመራ)

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

፩. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ከላይ ያነበባችሁትን የተውኔት ጽሁፍ መሠረት በማድረግ በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ ተገቢውን መልስ ጻፉ፡፡

ሀ. አስካለ ውሃ ለማምጣት የሄደችው ወዴት ነው?

ለ. በጽሁፉ ውስጥ የአስካለ እና የገበየሁ የስራ ድርሻ ምንድን ነው?

ሐ. ተደጋጋሚ የፉጨት ድምጽ ያሰማ የነበረው ማነው? ለምን?

መ. በጽሁፉ ውስጥ ስምአይጠሬ እና የማነ የተባሉት አስካለ እንዳትሰማቸው የተጠቀሙት የቋንቋ አጠቃቀም ምን ተብሎ ይጠራል? በተጠቀሰው ቋንቋ የተገለጸውን የሁለቱንም ንግግር በመደበኛው የቋንቋ አጠቃቀም ጻፉ፡፡

ሠ. ስም አይጠሬ ምሳውን ሳይበላ ለመሄድ የተነሳሳው ለምንድን ነው?

፱. ከዚህ በታች የቀረቡት ቃላትና ሀረጋት ካነበባችሁት ጽሁፍ ውስጥ የተወሰዱ ሲሆኑ፣ በምንባቡ ውስጥ ያላቸውን ፍች ግለጹ።

ሀ. ማዕድ ቤት

ለ. ቦኖ ውሃ

ሐ. ብቅ አለ

መ. ቆሌ

ሠ. መለዮ

**ዘለለኝ (ክፍል ሁለት)**

ገበየሁ፡- (አስካለ አልጋውን እያነጠፈች እያለ የመቶ አለቃ ከአቶ ወንዳፍራሽ ጋር ተያይዞ ከገቡ በኋላ ወንበር ስበው እንደተቀመጡ መቶ አለቃ በእጅ ጭብጨባ ይጣራል። አስካለም ፈጥና መጥታ ከፊት ትቆማለች።) በይ እባክሽ የሚጠጣ ነገር አምጭልን። ይኸን ሰውዬ ክፉ ፀሐይ መቶታል።

አስካለ፡- እሚበላ አይቀድምም?

ገበየሁ፡- በጣም ጥሩ ሀሳብ! (ወደወንዳፍራሽ ዞሮ) ጋሼ ምሳ...

ወንዳፍራሽ፡- የለም የለም በልቻለሁ መቶ አለቃ! እንዴት እስካሁን ይቆያል ብለህ ታስባለህ? እንዳልከው የሚጠጣ ካለ ተስማሚ ነው።

ገበየሁ፡- (ለአስካለ) እንግዲያውስ ጠላውን አምጭልን። (ለወንዳፍራሽ) ቅድም እየተጣደፍኩኝ ምሳ ለመብላት ስመጣ የትኛው ዘመዴ እንደሆነ አላውቅም ብቻ ካልጋዬ ላይ ሰው ተኝቶ አገኘሁ። አንተ መስለኸኝ እንዲጠብቀኝ ንገሪው ብዬ ለአስካለ መልዕክት ትቼ እየተጣደፍኩኝ ወጣሁ። (በየፊታቸው ትልልቅ ብርጭቆ አስቀምጣ

ያቀረበችውን የጠርሙስ ጠላ የምትቀዳውን አስካለን እየተመለከተ) ተኝቶ የነበረው ሰውዬ ማን ነኝ አለሽ? ተነሣ ወይስ አሁንም እንደተኛ ነው? (የሷን መልስ ሳይጠብቅ ከመቀመጫው ተነስቶ የአልጋውን መጋረጃ ገልጦ የተኛ ሰው አለመኖሩን ያረጋግጣል፡፡)

አስካለ፡- ጋሼ ወንዳፍራሽ ነው የሚሉት? አሁን ገና ወጣ፡፡

ገበየሁ፡- (በመገረም ከወንዳፍራሽ ጋር እየተሳሳቀ) ጋሼ ወንዳፍራሽ የምትያቸው እሳቸው ናቸው፡፡ ለወደፊቱ እወቂያቸው፡፡ አንቺ ከዚህ ቤት ከገባሽ በኋላ ስላልመጣ አልተዋወቃችሁም፡፡

ወንዳፍራሽ፡- (ለሰላምታ እጁን እየዘረጋ) ወንዳፍራሽ አብጤ እባላለሁ፡፡

አስካለ፡- ታዲያ ቅድም ተኝተው የነበሩት ሰውዬ ለምን ወንዳፍራሽ ነኝ አሉኝ? ወይስ ሁለት ወንዳፍራሽ አጎት አሉዎት? እራስዎም ቢሆኑ ወንዳፍራሽ ሲነሳ ምሳውን አብይው መልዕክትም ንገሪው ብለው ትዕዛዝ አልሰጡኝም!

ገበየሁ፡- ታዲያ ወንዳፍራሽ ነኝ አለሽ!

አስካለ፡- አዎ፡፡ የአባታቸውን ስም አልነገሩኝም እንጂ ወንዳፍራሽ ነኝ የመቶ አለቃ ገበየሁ አጎት ብለው ቴ…

ገበየሁ፡- (በመገረም ተመልሶ እየተቀመጠ) በጄ ምን ብሎሽ ሄደ በመጨረሻ?

አስካለ፡- ጠብቀን፡፡ አሁን እመለሳለሁ ብለው ሄዱ፡፡

ወንዳፍራሽ፡- እመጣለሁ ብሏል ነው ያልሽው?

አስካለ፡- መምጣቱን እንኳን ያለጥርጥር ይመጣሉ፡፡ ኮታቸውንና ጫማቸውን ከዚሁ ትተው ሄደዋል፡፡ … የሳቸው ስለቆሸሸባቸው የእርስዎን ጃኬትና ጫማ ቀይረው…

ገበየሁ፡- (ከመቀመጫቸው ተስፈንጥረው ተነስተው) የኔን ልብስ ለብሶ ሄደ

አስካለ፡- አዎ፡፡ ብርድ ብርድ ስላላቸው ደግሞ ካፖርትዎትን በላይ ደርበዋል፡፡

ገበየሁ፡-　(ጭንቅላቱን በሁለት እጆቹን ይዞ) ጉድ! ጉድ! ጉድ! … ሙልጭ ተደርጌ ተዘርፌያለኊ!

ወንዳፍራሽ፡-　እስቲ እረጋ ብለህ ይኸን ሰው አስታውሰው ታውቀው እንደሆን፡፡ አንዳንድ ሰው መልኩ እየታወቀ ስሙ ይረሳል፡፡ የቆየ አብሮ አደግ ጓደኛ ሊሆን ይችላል፡፡

ገበየሁ፡-　ወንዳፍራሽ? ሌላ የማውቀው ወንዳፍራሽ ማን አለ? (ፋታ) ደግሞ ባያውቀኝ ኖሮ ካልጋዬ ላይ ባልተኛ ነበር፡፡ መተኛቱን ይተኛ፤ ማወቁንም ይወቀኝ… እንዴት …? (የመገረምና የመናደድ ቃና ያለው ሳቅ ይስቅና) ልብሴንስ ለምን ለበሰ?

ወንዳፍራሽ፡-　እኔ የምልሽ የኔ እህት!… አካሄዱ እንዴት ነው?

አስካለ፡-　አካሄዳቸው ጤነኛ ነው?

ወንዳፍራሽ፡-　እንደሱ ማለቴ ሳይሆን ቀዥ ቀዥ ይላል ወይስ ረጋ ያለ ሰው ነው?

አስካለ፡-　ግርማ ሞገስ ያለው አረማመዱ የሚራመዱ፤ ቆንጆ ደርባባ ሰው ናቸው፡፡

ገበየሁ፡-　ጉድ! ጉድ! …

አስካለ፡-　የመቶ አለቃ ከኔ ቀድሞ ከመጣ ስጭው ብለው የሰጡኝ ማስታወሻ ወረቀትም አለ፡፡

ገበየሁ፡-　እስቲ አምጭው! (ተቀብሎ ደጋግሞ ካነበበ በኊላ) ምን? እንዲህ ነኝና ገበየሁ!

ወንዳፍራሽ፡-　ምን ይላል? እስቲ አምጣው፡፡ (ተቀብሎ ጮክ ብሎ ያነበዋል፡፡) ጤና ይስጥልኝ እንደምን ዋልክ የኔ ወንድም !? …… ሰዓቱ ስላላመቸኝ የምሳ ግብዣህን አክብሬ ሳልበላ በመሄዴ ልባዊ ቅሬታ ተሰምቶኛል፡፡ ቢሆንም በሌላ በሌላው ሳልክስ እንዳልቀረሁ ላረጋግጥልህ እወዳለሁ፡፡ ተጻፈ ከ… ታወቀው ሞጭላፊ ከስም አይጠሬ ባካኙ …ካ ምን ለማለት ፈለገ፡፡ የሰረቅሁት እኔ ነኝ ለማለት ነው?

ገበየሁ፡- (በንዴት እያጨበጨበ) ጉድ! ጉድ! ጋሼ፣ በል ፖሊስ ጣቢያ ሄጄ ሳስመዘግብ... ተጫውቶብኝ ሄዷል፡፡ ምንም አላስተረፈኝም፡፡ ከጃኬቴ ኪስም ገንዘብ ነበረ፡፡ እሱንም ይዞ ሄዷል፡፡ ሎተሪ ወጣልኝ ይበል ዛሬ!

ወንዳፍራሽ፡- (ደጋግሞ እያነበበ) ይኽ ውስጥ አዋቂ ሌባ መሆን አለበት እንጂ፡፡ መቼም ከማዶ መጥቶ ይኽን ያደርጋል ብዬ አልገምትም፡፡

ገበየሁ፡- ወይኔ! እስካሁን በእንዲህ ዓይነት ነገር ጥቃት ገብቶኝ አያውቅም ነበር፡፡ ይቺ ... (ወንዳፍራሽ እየገፋ ይዞት ይወጣል)

## የማንበብ ጊዜ ጥያቄዎች

1. ገበየሁ ተመልሶ የመጣው ከማን ጋር ነው?
2. በአስካለ አገላለጽ ተኝቶ የነበረው ሰው የገበየሁን ጃኬትና ጫማ ቀይሮ የሄደው ለምንድን ነው?
3. በቀጣዩ የተውኔት ክፍል ምን የሚሆን ይመስላችኋል?

አስካለ፡- (ወገቧን ይዛ ቆማ) ታዲያ እኔ ሰረቅሁበት እንዴ? የሱ ቤት የቀረ እንደሆነ ሠርቼ የምበላበት የማጣ መሰለው? ደግሞ ተጠያቂ ትሆኛለሽ ይለኛል፡፡ ሆ ሆይ! እኔን ከሶ ... እስቲ ያሳስረኝ እንደሁ አያለሁ! (ወደ በሩ ጠጋ ብላ ርቀው መሄዳቸውን ካረጋገጠች በኋላ) ኸረ ቆይ እንዲያውስ ከሱ ጋር ምን አናዘዘኝ... አሁኑኑ ቤቱን ጥዬለት ብወጣ አይሻልም? (ልብሷን እና ሌሎች ንብረቶቿን ሰብስባ በማዳበሪያ ጆንያ ከትታ ካጎነበሰችበት ቀና ስትል ስም አይጠሬው ሮጦ ገብቶ ከፊቷ ይገተራል፡፡)

ስም አይጠሬ፡- (በኃይል እየተነፈሰ) ጉድ ሆንኩልሽ አንቺዬ!... መታወቂያዬን ልቤ ጠፍቶ ኪሴ ውስጥ እንዳስቀመጥኩት እረስቼ ሄጃለሁ፡፡ እሱን ልወስድ ስሮጥ መጣሁልሽ፡፡ (ኮቱ ወደተቀመጠበት ሊሄድ ሲል በሁለት እጆቿ ወገቡ ላይ ተጠምጥማ ትይዘውና እሪታዋን ታቀልጣለች፡፡)

አስካለ፡- በህግ አምላክ ከእንግዲህ ወዲያ ምንም ዓይነት ዕቃ ማንሳት አይችሉም፡፡ የውሸትዎን ብዛት ደግሞ ወንዳፍራሽ እኔ ነኝ ማለትዎ፡፡ እርስዎ ወንዳፍራሽ ሳሆኑ ቤት አፍራሽ ነዎት!

ስም አይጠሬ፡- ሴትዮ ባስርደቂቃ ውስጥ አብደሽ ቆየሽኝ ልበል ወይስ ሰይጣን ተነፈሰብሽ?

አስካለ፡- ያበዱትም ሰይጣን የተነፈሰብዎትም እርስዎ ነዎት፡፡ (ነጥቋት ወደጓዳ ሊገባ ሲታገላት አጥብቃ እየያዘችው) ኧረ የምን እብድ ደንበኛ አጭበርባሪ ነዎት እንጂ፡፡

ስም አይጠሬ፡- (ጣቱን አውጥቶ እያስፈራራ)ካሁን በኋላ አፍሽን አሳርፊ! በገዛ ወንድሜ ቤት ብተኛበት፣ ብነሳበት፣ ብበላ... ማንም ሊናገረኝ አይችልም፡፡ ቆይ! እንዲውም ... በዚህ ከተማ ስራ የሚባል ካገኘሽ ውሻ በይኝ! (ለማስለቀቅ እየታገለ) አሁን አትለቂኝም ትለቂኛለሽ?

አስካለ፡- አለቅም! አይን አውጣ፡፡ እልም ያልክ አይናውጣ ነህ!

ስም አይጠሬ፡- (አንገቷን ጨምድዶ ይዞ)እይው ነግሬሻለሁ እንቅ ፍትርቅ አድርጌ ስይዝሽ መተንፈስ ተስኖሽ ሕይወትሽ እንዳታልፍ! (አዘቅዝቆ በብስጭት እየተመለከታት) አንቺ ...

አስካለ፡- ጫፌን ንካኝና እሪ ብዬ አገሩን እንዳላደባልቀው፡፡

ስም አይጠሬ፡-ላንቺ ሲል ነው አገር የሚደባለቀው? ጅል! አንቺን መሰሎች ሺህ ሆነው ቢጮሁም ከወፍ ጫጫታ አይቆጠርም፡፡ ... (በማባበል መልክ) አሁን ሁሉንም ተይውና ልቀቂኝ፡፡

አስካለ፡- ግደለኝ እንጂ ዛሬ ብሞት አለቅም፡፡

የማነ፡- ምንድነው ጩኸቱ? (ስም አይጠሬ ያይና እራሱን ይዞ) አወይ! አወይ ወንድሜን! አቶ ወንዳፍራሽ ምነዎ? ምን ነገር አገኘህ?

ስም አይጠሬ፡-(እግሩን ለማስለቀቅ እየጣረ) ይኸውልህ! በወንድሜ ቤት እንደዚህ ጉድ ሆንኩልህ፡፡ አሳሬን እስክቆጥር ተደበደብኩ፡፡ ... ይኸው አሁን ደግሞ እግሬ ተሰበረ፡፡

የማነ፡-　　ኧረ እባክህ በበሩ ውጣ፡፡ ሌባ ይመስል በመስኮት ምን አንጠለጠለህ፡፡

ስም አይጠሬ፡-ይኸው አታያትም እመቤቲቱ በሩን በቁልፍ ዘግታ አላስወጣ ብላ፡፡

አስካለ፡-　　የመቶ አለቃን አጎት ወንዳፍራሽን በአይኔ በብረቱ ቅድም አይቻቸዋለሁ፡፡ የመቶ አለቃም ሌላ ወንዳፍራሽ የሚባል ዘመድ ሆነ ጓደኛ የለኝም ብለዋል፡፡

የማነ፡-　　ይኸ እኮ ወንዳፍራሽ አይደለም፡፡ ወንድይፍራሽ ነው ስሙ፡፡ ቅድም ያየሻቸው አቶ ወንዳፍራሽ (በእጁ እየጠቆመ) የዚህኛው የአቶ ወንድይፍራሽ ወንድም ለዚያውም ታላቅ ናቸው!

አስካለ፡-　　(በመጠራጠርና በመደንገጥ የማነንና ስም አይጠሬን እየተመለከተች) በእርግጥ ወንድይፍራሽ ናቸው?

የማነ፡-　　(የለበጣ ሳቅ እየሳቀ) ምነው እባክሽ እንደውሽታም ቆጠርሽውን? በይ ክፈችለት ሰው ሳይሰማ፡፡ ነውርም አይደል?

ስም አይጠሬ፡-(በምሬት) እንዲያውም ዛሬ መቶ አለቃ ይምጣልኝ እንጂ አሳይሻለሁ! በይ አሁን ክፈችልኝማ!

አስካለ፡-　　(ደብቃ የያዘችውን ቁልፍ ከጉያዋ አውጥታ ለመክፈት ወደበሩ ስትሄድ መቶ አለቃ ገበየሁ፣ አቶ ወንዳፍራሽና አንድ ፖሊስ አንድነት ተያይዘው ይደርሳሉ፡፡ ካጎነበሰችበት ቀና ብላ እንዳየቻቸው በደስታ) የመቶ አለቃ መጡ! እልልል! እንኳንም መጡ! (የማነ ሮጦ ለማምለጥ ሲሞክር ፖሊሱ ወዲያውኑ ይይዘዋል፡፡ የመቶ አለቃ በጥፊ ደጋግሞ ፊቱ ላይ ያሳርፍበታል፡፡ ፖሊሱ ይገላግላል፡፡)

ገበየሁ፡-　　ለመሆኑ የት አባክ ታውቀኝና ነው እንዴትስ ብትደፍረኝስ ነው … አንተ!

አስካለ፡-　　(በእጇ እያሳየች) እሱ አይደለም የወሰደው ጌቶች ዋናው ይኸኛው ነው፡፡ አቶ ወንዳፍራሽ ነኝ ያለው ይኸነው፡፡ አሁን ደግሞ ስሜ ወንድአፍራሽ ሳይሆን ወንድይፍራሽ ነኝ ብሏል፡፡

ገበየሁ፡- (ስም አይጠሬን አተኩሮ ካየ በኋላ ቤቱን ከፍቶ ይገባና) ማነህ አንተ የማውቅህ ነህ ልበል? በተለይ አይንህ፣ አፍንጫህና ግንባርህ የለመድኩት ዓይነት ይመስለኛል። ፂምህ ብቻ ነው እንግዳ የሆነብኝ። (በሽጉጡ አፈሙዝ ግንባሩ ላይ ይመታውና) ትክክለኛ ስምህ ማን ይባላል? ወንዳፍራሽ ወይስ ስም አይጠሬ? ወይስ አሁን ተናገርክ እንደተባለው ወንድይፍራሽ?

ስም አይጠሬ፡- ዘለለኝ ነኝ ጌታዬ!

ገበየሁ፡- (በሽጉጥ አፈሙዝ ደግሞ ይመታውና) ዘለለኝ? የኛ ሰፈር ደላላ? (ስም አይጠሬ በአዎንታ ራሱን ይነቀንቃል) ይህ ሁሉ ጺም ከየት መጣ ታዲያ? ሳውቅህ ጢም ያለህ አይመስለኝም። (በሽጉጥ የሚመታ አስመስሎ በጥፊ ያጮለዋል። ) ወይስ የኔን ቤት ለመዝረፍ እንዲያግዝህ ስታጎፍር ከረምክ? (ስም አይጠሬ በድንጋጤ ሲንዘፈዘፍ መቶ አለቃ አርቴፊሻል ጺሙን ከፊቱ ላይ ገፎ ያነሳዋል።)

አስካለ፡- አቤት! አቤት! (በመገረም ጉንጮቿን ግጥም አድርጋ ይዛ) እንዴት ያለው ሞላጫ ነው ባካችሁ? ይኸ ሁሉ ብልሃት ከየት መጣለት?

ገበየሁ፡- አየህ እኔ የማውቀው ይኸኛውን መልክህን ነው። (በጥፊ ይደግመዋል) ሌላውን ሰው አልክ አልክና ወደኔ መጣህ? የተሰረቀ ዕቃ በመግዛትና በመሸጥ ልምድህን አዳበርክና ቀጥለህ እራስህ ሌባም አስተላላፊ ደላላም ሆነህ አረፍከው። (ወደፖሊሱ ዞሮ) ፖሊስ!

ፖሊስ፡- (በተጠንቀቅ ቆሞ ሰላምታ ከሰጠ በኋላ) አቤት ጌታዬ?

ገበየሁ፡- በል ሁለቱንም አቆራኝተህ እሰርልኝ እጅ ከፍንጅ ሰርቆ ከለበሳቸው ልብሶቼ ጋር ወደጣቢያ ንዳልኝ።

ወንዳፍራሽ፡- (ወደስም አይጠሬ ጠጋ ብሎ በንዴት ካስተዋለው በኋላ) ሌባ ተይዞ ዱላ አይጠየቅም እንደተባለው በአይበሉብሽም በቢበሉብሽም አገላብጩ ጥፊ ላቅምሰው መቶ አለቃ!

ፖሊስ፡- በቃ ተጠርጣሪው አሁን በህግ ጥበቃ ስር ነው ዱላ በቃ! (ስም

አይጠሬን ከየማነ ጋር አቆራኝቶ አስሮ የሚሄዱበትን አቅጣጫ እንዳሳያቸው መንቀሳቀስ ይጀምራሉ፡፡ መቶ አለቃ፣ ወንዳፍራሽና አስካለም ይከተሏቸዋል፡፡)

(ምንጭ፡- ፋንታሁን እንግዳ (2009) የተውኔት ድርሰት አፃፃፍ ዘዴ)፡፡

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ባነበባችሁት የተውኔት ጽሁፍ መነሻነት በቡድን በመወያየት ተገቢውን መልስ ጻፉ፡፡

ሀ. በክፍል አንድ እና በክፍል ሁለት ላይ ባነበባችሁት ጽሁፍ ውስጥ የተሳተፉ ገጸ-ባህርያት አነማን ናቸው?

ለ. በጽሁፉ ውስጥ የተገለጸው ድርጊት የተፈጸመበትን ጊዜና ቦታ ጻፉ፤ በጽሁፉ ውስጥ ጊዜውንና ቦታውን ሊጠቁሙ የሚችሉትን ነገሮችም አመልክቱ፡፡

ሐ. "… ውስጥ አዋቂ ሌባ መሆን አለበት…" ሲል ምን ማለቱ ነው?

መ. የስምአይጠሬ መጠሪያ ስም ማነው?

ሠ. የተውኔቱ ታሪክ የሚያጠነጥነው በማን ዙሪያ ነው?

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

፩. "ዘለለኝ" በሚል ርዕስ በክፍል አንድ እና በክፍል ሁለት የቀረበውን ተውኔት መልዕክት በጽሁፍ ተንትናችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

፪. በክፍል አንድና ሁለት በቀረበው ጽሁፍ መሠረት በእያንዳንዱ ተዋንያን የቋንቋ አጠቃቀም ሁኔታ ላይ ተወያዩ፡፡

፫. በተውኔቱ መዋቅር ላይ ከተወያያችሁ በኋላ መልሳችሁን አብራርታችሁ ጻፉ፡፡

፬. በንባብ ክፍል በቀረበው ተውኔት መሠረት ተመሳሳይ ሌላ ተውኔት በራሳችሁ ጻፉ፡፡ የጻፋችሁትን የተውኔት ጽሁፍ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በማቅረብ እንዲገመግሙ አድርጉ፡፡

፭. የተለያዩ የተውኔት ዓይነቶችን የሚገልጹ ጽሁፎችን ካነበባችሁ በኋላ ስለእያንዳንዱ የተውኔት ዓይነት አብራርታችሁ ጻፉ፡፡

፮. "ዘለለኝ" በሚል ርዕስ የቀረበው የተውኔት ቅንጫቢ ለየትኛው የተውኔት ዓይነት ምሳሌ ሊሆን ይችላል? ለምን?

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

በዚህ ምዕራፍ ተውኔትን በሚመለከት የተለያዩ ይዘቶች ቀርበዋል፡፡ ተውኔት የስነ-ጽሁፍ ዘርፍ መሆኑን፣ በመድረክ ላይ የሚቀርብ መሆኑን፣ የማኅበረሰቡን ገጽታ በማሳየት ከሌሎች የስነ-ጽሁፍ ዘርፎች የሚጋራቸው ኪነጥበባዊ ባህርያት ቢኖሩትም ገና ከመነሻው በተዋንያን አማካኝነት በመድረክ ላይ የሚደረስ በመሆኑ በአያሌው መለየቱን ተምራችኋል፡፡

ተውኔት በመድረክ ላይ ስለሚቀርብ የተመልካቹን ትኩረትና ስሜት የመሳብ ከፍተኛ ኃይል ያለው መሆኑን ተመልክታችኋል፡፡ ተውኔት የሚቀርብበትን መድረክ የተሟላ ለማድረግ የተለያዩ ባለሙያዎች የሚሳተፉ መሆኑን ተምራችኋል፡፡

መቼት፣ ገጸ-ባህርይ፣ ሴራ፣ ቃለ-ተውኔት፣ ጭብጥ የተውኔት አላባውያን መሆናቸውን ተምራችኋል፡፡ እንዲሁም ስለእያንዳንዳቸው ተግባር በሠራችኋቸው የመልመጃ ጥያቄዎች አማካኝነት ተመልክታችኋል፡፡ በትዕይንት መልክ የተሰጠውንም ቃለ ምልልስ አንብባችኋል፡፡ "ዘለሰኝ" በሚለው ተውኔት መነሻነት በውስጡ ያሉትን ገጸ-ባህርያት፣ የተውኔት መዋቅር ገልጻችኋል፡፡ የተውኔት ዓይነቶችንም በሚመለከት የተለያዩ ጽሁፎችን አንብባችሁ አብራርታችኋል፡፡

## የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

1. ተውኔት ከሌሎች የስነ-ጽሁፍ ዘርፎች የሚለይበትን መሠረታዊ ባህርይ ጻፉ፡፡
2. ተውኔት የሚቀርብበትን መድረክ ድባብ የተሟላ ለማድረግ ከሚሳተፉት ባለሙያዎች ውስጥ ቢያንስ የሁለቱን ስምና ተግባር ግለጹ፡፡
3. የአንድ ተውኔት ትርጉም በምን በምን ሊመዘን ይችላል
4. ከተውኔት ዓይነቶች ውስጥ ቢያንስ ሁለቱን ግለጹ፡፡

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ ስምንት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ቅጽ ቀርቦላችኋል፡፡ በዚህም መሠረት በእያንዳንዱ ማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ቅጹን አሟሉ፡፡

| | የማመሳከሪያ ነጥቦች | √ | ? | X |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የተውኔትን ምንነት መግለጽ ችያለሁ | | | |
| 2 | የተውኔት አላባውያንን መግለጽ ችያለሁ | | | |
| 3 | ተዋናይ ማለት ምን ማለት እንደሆነ መግለጽ ችያለሁ | | | |
| 4 | በተውኔት ውስጥ የሚሳተፉትን ባለሙያዎችና ተግባራቸውን መዘርዘር ችያለሁ | | | |
| 5 | የተውኔት መዋቅርን ማብራራት ችያለሁ | | | |
| 6 | ተውኔት መተወን ችያለሁ | | | |
| 7 | የተውኔት ዓይነቶችን ማብራራት ችያለሁ | | | |
| 8 | የተውኔት ረቂቅ መጻፍ ችያለሁ | | | |

፪. ከዚህ በላይ በቀረበው ቅጽ የ(?) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትገነዘቡ ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

አማርኛ

(፱ኛ) ክፍል

## ምዕራፍ ዘጠኝ፡- ማህበራዊ መገናኛ ብዙኃን እና ተግባቦት

**የምዕራፉ ዓላማዎች፡-**

**ተማሪዎች ይህንን ምዕራፍ ከተማራችሁ በኋላ፣**

- የጽሑፉን ዋና ሃሳብ በማዳመጥ ታጠቃልላላችሁ፡፡
- በታዋቂ ሰዎች ፊት ለፊት ንግግር ታቀርባላችሁ፡፡
- አንብባችሁ ተግባራትን ታከናውናላችሁ፡፡
- የቃላትን ትርጉም ከአውዱ ውስጥ ታወጣላችሁ፡፡
- የንጽጽር ሀረጋትን በመለየት ትጠቀማላችሁ፡፡

## ክፍል አንድ፡- ማዳመጥ

# የጋዜጠኛው ቃለ ምልልስ

### ቅድመ ማዳመጥ ጥያቄዎች

፩. በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በቡድን በመወያየት የጋራ መልሳችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለጹ፡፡

ሀ. ጋዜጠኝነት ማለት ምን ማለት ይመስላችኋል?

ለ. ቃለ ምልልስ ማለት ምን ማለት ይመስላችኋል?

ሐ. ቃለ ምልልስ በሚያደርግ የመገናኛ ብዙኃን ባለሙያ እና በቃለ ምልልስ ሰጪው መካከል የሚኖረው ግንኙነት ምን መሆን ያለበት ይመስላችኋል?

፪. ቀጥሎ ለቀረቡት ቃላት ተመሳሳይ ፍች ስጡ፡፡

ሀ. ታዋቂነት

ለ. መረጃ

ሐ. እፍታ

መ. ኮሚቴ

ሠ. ሊቃውንት

### የማዳመጥ ጊዜ ጥያቄዎች

፩. የቃለ ምልልስ ዋነኛው ዓላማ ምንድን ነው?

፪. ጋዜጠኛ ከጋዜጠኝነት ሙያዊ ብቃት በተጨማሪ ምን ምን ባህርያት ሊኖሩት ይገባል?

፫. ባዳመጣችሁት ቃለ ምልልስ ውስጥ ጋዜጠኛው ከየትኛው የመገናኛ ብዙኃን የመጣ ነው?

## የአዳምጦ መረዳት ጥያቄዎች

፩. ባዳመጣችሁት ምንባብ መሠረት ቃለ ምልልስ ባጋጣሚ በሁለት ሰዎች መካከል የሚደረግ ምልልስ ነው ወይስ አይደለም? ለምን?

፪. ባዳመጣችሁት ቃለ ምልልስ በጋዜጠኛው እና በቃለ ምልልስ ሰጪው አማካኝነት የተላለፈውን መልዕክት ጠቅለል አድርጋችሁ በቃል አቅርቡ፡፡

፫. ባዳመጣችሁት ምንባብ ውስጥ የጋዜጠኛውን እና የቃለ ምልልስ ሰጪውን ቦታ በመተካት የቃለ ምልልሱ ሀሳብ እንዲቀጥል አድርጉ፡፡

፬. ከዚህ በታች ሁለት የተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮችን የያዙ ጅምር ጽሁፎች ቀርበዋል፡፡ እነዚህን ጅምር ሀሳብ የያዙ ጽሑፎች የያዙትን ርዕሰ ጉዳይ መነሻ በማድረግ አሟልታችሁ ጻፉ፡፡

ሀ. ኮሮና ቫይረስ የመተንፈሻ አካላትን የሚያጠቃ ተላላፊ በሽታ ነው፡፡ ይህ ተላላፊ በሽታ ከሰው ወደሰው በተለያዩ መንገዶች ሊተላለፍ ይችላል፡፡ ከመተላለፊያ መንገዶቼች ውስጥ ______________________________
____________________________________________________________
____________________________________________________________
____________________________________________________________
____________________________________________________________
______________________________፡፡

ለ. የጠነከረ መልካም ባህል ነበረን፡፡ ታላላቆቻችንን የማክበርና ቅድሚያ የመስጠት የመልካም ግብረገብነት ኃላፊነትም ነበረብን፡፡ ታላላቆቻችንም በመልሱ የመመረቅ፣ የማመስገን ሀላፊነት ነበረባቸው፡፡ ዛሬ ያ መልካም ባህል የለም፡፡ ጋጠወጥነት በምትኩ እየተንሰራፋ ነው፡፡ አባቶቻችንንና እናቶቻችንን ____________________________________________
____________________________________________________________
____________________________________________________________
____________________________________________________________
____________________________________________________________፡፡

## ክፍል ኹለት፡- መናገር

፩. ከቴሌቪዥን ወይም ከሬዲዮ ወይም ከድረ-ገጽ (በይነ መረብ) ወይም ከጋዜጣ ወይም ከመፅሔት የተለያዩ ማስታወቂያዎችን ከሰበሰባችሁ በኋላ፡-

ሀ. የሰበሰባችኋቸው ማስታዎቂያዎች ጠቀሜታቸው ምን እንደሆነ ግለጹ፡፡

ለ. የሰበሰባችኋቸው ማስታወቂያዎች ለየትኞቹ አድማጮች ወይም ተመልካቾች እንደቀረቡ ግለጹ፡፡

፪. በተለያዩ የመገናኛ ብዙኃን የሚተላለፉ ማስታወቂያዎች የአድማጭን ወይም የተመልካችን ስሜት መቀስቀስ ያስፈለገው ለምንድን ነው? የተመልካችን ስሜት ለመቀስቀስ ምን ምን ስልቶችን ይጠቀማሉ? በሚሉት ጥያቄዎች ላይ በቡድን በመወያየት የጋራ መልሳችሁን በቃል ግለጹ፡፡

፫. "የማስታዎቂያ ቋንቋ ምን መምሰል አለበት?" በሚለው ጥያቄ ላይ ከጓደኞቻችሁ ጋር ተወያዩ፡፡ በውይይታችሁ ለምታነሱት ሀሳብ በተለያዩ የመገናኛ ብዙኃን ዘዴዎች ከተላለፉት ማስታወቂያዎች ጥሩ ምሳሌ ነው የምትሉትን አንዱን አቅርቡ፡፡

፬. በታዋቂ ሰዎች ፊት ንግግር በምናደርግበት ጊዜ ትኩረት ሊሰጥባቸው የሚገቡ ነጥቦች ምን ምን ናቸው? በቡድን ከተወያያችሁ በኋላ ዋና ዋና ነጥቦችን ለክፍል ጓደኞቻችሁ በቃል አቅርቡላቸው፡፡

## ክፍል ሦስት፡- ንባብ

# መገናኛ ብዙኃንና ጋዜጠኝነት

### ቅድመ ንባብ ጥያቄዎች

በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በቡድን በመወያየት የጋራ መልሳችሁን ለክፍል ጓደኞቻችሁ ግለጹ፡፡

፩. መገናኛ ብዙኃን ማለት ምን ማለት ይመስላችኋል?

፪. የምታውቋቸውን የመገናኛ ብዙኃን ዓነቶች ዘርዝሩ፡፡

፫. መገናኛ ብዙኃን ምን ጠቀሜታ ያለው ይመስላችኋል?

### መገናኛ ብዙኃንና ጋዜጠኝነት

መገናኛ ብዙኃን መረጃዎችን ለህብረተሰቡ በተለያዩ አማራጮች ለማድረስ የሚያስችሉ መሳሪያዎች ናቸው፡፡ እነዚህ የመረጃ ማሰራጫ መንገዶችም የህትመት ወይም የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ ብዙኃን ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ የህትመት መገናኛ ብዙኃን የሚባሉት ጋዜጦች፣ መፅሔቶች፣ በራሪ ወረቀቶች፣ ወዘተ. ሲሆኑ፣ የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ ብዙኃን የሚባሉት ደግሞ ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥን፣ በይነ መረብና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ በኤሌክትሮኒክስም ሆነ በህትመት መገናኛ ብዙኃን በየቀኑ የሚቀርቡት መረጃዎች የሁነቶች ወይም የድርጊቶች ዝርዝር ቁም ነገር ቢሆንም መረጃዎቹ የሚቀርቡበት ጊዜ እና ፍጥነት የተለያየ ነው፡፡ በተለይ ከኤሌክትሮኒክስ መገናኛ ብዙኃን ውስጥ አንዱ የሆነው የበይነ መረብ መገናኛ ብዙኃን በፍጥነት በርካታና የተለያዩ መረጃዎች ይተላለፉበታል፡፡ ይህ ደግሞ ከሰው ልጆች የመፍጠር ችሎታ ጋር የተገናኘ ነው፡፡

የኤሌክትሮኒክስ መገናኛ አውታሮች በተለይም በስልክና በበይነ መረብ ረገድ ከቀን ወደ ቀን አዳዲስ ግኝቶች እና የመሻሻል ለውጦች እየተስተዋሉ ናቸው፡፡ የመሻሻሉ ፍጥነት የሚያስደምመው ደግሞ ሰዎች አንዱን ግኝት በአግባቡ

አውቀውና ተጠቅመው ሳይጨርሱ ሌላ መምጣቱ ነው፡፡ በቀናት፣ በወራት፣ ምናልባትም በዓመታት በደብዳቤ አማካኝነት ናፍቆትን የሚለዋወጡበት፣ መልዕክት የሚቀባበሉበት፣ የፖስታ ቤት በርን ደጅ የሚጠኑበት ጊዜ በኢ-ሜይል ከተቀየረ ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ ከሰከንዶች ባነሰ ፍጥነት በበይነ መረብ አማካኝነት ግንኙነት የሚፈጠርበት ይህ ቴክኖሎጂ አድጎ ቲውተርን፣ ኢሞን፣ ሜሴንጀርን፣ ቫይበርን፣ ቴሌግራምን፣ ፌስቡክን፣ ወዘተ. ሊፈጥር ችሏል፡፡ ይህ ቴክኖሎጂ ናፍቆትን ከማስቀረት ባለፈ ማን፣ የትና እንዴት ባለ ሁኔታ እንደሚገኝ ለማወቅም ተችሏል፡፡

ዛሬ የሰው ልጅ ብዙ ጊዜውን አብዝቶ ከሚያሳልፍባቸው ጉዳዮች ማህበራዊ ድረገፆች ዋነኞቹ እንደሆኑ ጥናቶች ያመላክታሉ፡፡ ማህበራዊ ድረ-ገፆች ለፈጣን መረጃ ልውውጥና ለተለያዩ ሀገራት ህዝቦች መቀራረብ ያላቸው ጠቀሜታ እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡በአንፃሩ ለአላስፈላጊ ያታዊ ትንኮሳ፣ ለማይጠቅሙ ምስሎችና መረጃዎች ልውውጥ፣ እንዲሁም አላስፈላጊ ለሆኑ ሃይማኖታዊና ፖለቲካዊ መልዕክቶች የተመቹ በመሆናቸው ስጋትን መፍጠራቸው አይቀርም፡፡ ያም ተባለ ይህ ማህበራዊ ድረገፆች በርካታ ጥቅሞች እንዳላቸው ሁሉ ዘርፈ ብዙ ጉዳትን ሊያስከትሉ እንደሚችሉ በማሰብ አጠቃቀምን ማስተካከል ተገቢ ነው፡፡

የንባብ ጊዜ ጥያቄዎች

፩. ኤሌክትሮኒክ የመገናኛ ብዙኃን በመባል የሚጠሩት ምን ምን ናቸው?

፪. ደብዳቤ ለመላክ ከፖስታ ቤት ደጅ መጥናትን ያስቀረው ምንድን ነው?

፫. በአሁኑ ጊዜ የሰው ልጅ ብዙ ጊዜውን የሚያሳልፈው የት ነው?

ጋዜጠኝነት ለጋዜጣ፣ ለመፅሔት፣ ለሬዲዮ፣ ለቴሌቪዥን፣ ለዜና አገልግሎትና ለተለያዩ የበይነ መረብ መገናኛ አውታሮች ዜናዎችን፣ አጫጭርና ረጃጅም መጣጥፎችን፣ የሐተታ ፅሁፎችንና ርዕሰ አንቀጾችን፣ እንዲሁም የቴሌቪዥን መርሐ ግብሮችን የማቅረብ ሙያ ነው፡፡ ጋዜጠኝነት ከሙያ ዕይታ ተነስቶ ማቀድን፣ መረጃ መሰብሰብን፣ መጻፍንና የአርትኦት ስራ ማከናወንን ይጠይቃል፡፡

ጋዜጠኝነት የተጠናቀረ ቅርፅና ይዘት መያዝ የቻለው ዮሀን ጉተንበርግ የተባለው

ጀርመናዊ እ.ኤ.አ በ1450ዎቹ በአውሮፓ የመጀመሪያውን ማተሚያ መሳሪያ ፈልሰፎ ስራ ላይ ካዋለ በኋላ ነው፡፡ ዘግይተው የተፈለሰፉት ሬዲዮና ቴሌቪዥንም ለጋዜጠኝነት ሙያ መዳበር ከፍተኛ ሚና ተጫውተዋል፡፡

ጋዜጠኞች የሚያቀርቧቸው ፅሁፎች፣ አስተያየቶችና መርሐ ግብሮች ሁሉ የሚተላለፉት ከተራው ሰው ጀምሮ እስከ ዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር ላሉት ተደራሲያን ነው፡፡ ስለሆነም ጋዜጠኛው የሚያቀርባቸው የስራ ውጤቶች ለሁሉም ተደራሲዎች በየፈርጁ በቂ ግንዛቤ የሚሰጡና ተቀባይነት ያላቸው ሊሆኑ ይገባል፡፡

ጋዜጠኝነት የህዝባዊ አገልግሎት ባህሪ ያለው ሙያ እንደመሆኑ መጠን እንደ እኛ ባሉ በልማት ባልገፉ ሀገሮች የማህበራዊ ኑሮ እድገትን፣ የኢኮኖሚ ልማትን፣ የባህል ትንሳኤንና መስፋፋትን፣ እንዲሁም በአጠቃላይ ሁለንተናዊ የአገር ግንባታን በማፋጠን ረገድ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡ የሙያው ዋና ዓላማ ህብረተሰቡን ማሳወቅ፣ ማስተማርና ማዝናናት ሲሆን፣ የማህበራዊ ኑሮን አስተሳሰብ በመለወጥም የሚያደርገው አስተዋፅኦ ልዩና ወሳኝ ነው፡፡

ጋዜጠኝነት ታላቅ ዝናን፣ እውቅናን የሚያስገኝ ሙያ የመሆኑን ያህል ዝና እና እውቅና ለማግኘት የሚከፈለው መስዋዕትነትና አገልግሎትም እጅግ ከባድና ከፍተኛ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ በዓለም አቀፍ ደረጃም ሆነ በአህጉራችን ህይወታቸውን ለሙያቸው ሲሉ የሠዉ፣ ለሃቅ በመቆማቸው ብቻ በፀረ-ሃቅ ወገኖች ጥይት የወደቁ ጀግኖች ጋዜጠኞች ቁጥር ጥቂት አይደለም፡፡

በሀገራችን ህብረተሰቡ ጋዜጠኛ ሁሉ በጣም የተማረ፣ በሙያው የሰለጠነ፣ ብዙ የሚያነብና የሚመራመር፣ ሁሉን ነገር የሚያውቅ፣ ለችግሩ ሁሉ መፍትሔ ያለው፣ ለእውነትና ለህዝባዊ መብት የሚታገል፣ የደረጀ እውቀትና ከፍተኛ የህይወት ልምድ ያቀናጀና ያካተተ እንደሆነ አድርጎ ነው የሚመለከተው፡፡ ነገር ግን በመንግስትም ሆነ በግል መገናኛ ብዙሃን የሚሰሩ ጋዜጠኞች ሁሉም እነኝህን መለኪያዎች ሙሉ በሙሉ በብቃት ያሟላሉ ወይ ብለን ስንጠይቅ አወንታዊ መልስ ማግኘቱ ያዳግታል፡፡

(ምንጭ፡- ማዕረጉ በዛብህ (1995) የጋዜጠኝነት ሙያ ንደፈሃሳብና አተገባበሩ ከሚለውን ላይ ለማስተማሪያ እንዲሆን ተሻሽሎ የተወሰደ)

## የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎች

፩. ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች ምንባቡን መሠረት በማድረግ ትክክል ለሆኑት "እውነት"፣ ስህተት ለሆኑት ደግሞ "ሐሰት" በማለት በቃል መልሱ፤ ምክንያታችሁንም ግለጹ።

ሀ. የሰው ልጅ የፈጠራ ችሎታ በመገናኛ ብዙኃን ለሚተላለፉ መረጃዎች ብዛትና ፍጥነት መሻሻል ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት አለው።

ለ. የሬዲዮና የቴሌቪዥን መፈልሰፍ ለጋዜጠኝነት ሙያ እድገት ትልቅ አስተዋፅኦ አድርጓል።

ሐ. የበይነ መረብ መገናኛ ብዙኃን ጥቅማቸው እንጂ ጉዳታቸው የጎላ አይደለም።

መ. ጋዜጠኝነት ምንም ዓይነት መስዋዕትነትን የሚጠይቅ ሙያ አይደለም።

ሠ. ጋዜጠኝነት ለሀገር ግንባታና እድገት ወሳኝ ሚና አለው።

፪. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች በምንባቡ መሠረት መልስ በጽሁፍ ስጡ።

ሀ. ጋዜጠኝነት የተጠናቀረ ቅርፅ እንዲይዝ የተደረገው መቼ ነው?

ለ. በጋዜጠኝነት ሙያ የሚከናወኑ ተግባራት ምን ምን ናቸው?

ሐ. የሀገራችን ህዝብ ለጋዜጠኞች ያለው አመለካከት ምን ይመስላል?

መ. የበይነ መረብ መገናኛ ብዙኃንን ጥቅምና ጉዳት አብራሩ።

ሠ. በህትመትና በኤሌክትሮኒክ መገናኛ ብዙኃን መካከል ያለውን አንድነት እና ልዩነት ዘርዝሩ።

## ክፍል አራት፡- ጽሕፈት

፩. በቡድን በመሆን የተለያዩ ምርትና አገለግሎቶችን ለማስተዋወቅ የሚያስችሏችሁን ማስታወቂያዎች ጻፉ፤ የምትጽፉት ማስታወቂያ ምርትና አገልግሎቶችን የሚያሳዩ ፎቶዎችን ወይም ምስሎችን ያካተተ መሆን አለበት፡፡

፪. ከላይ በተራ ቁጥር "፩" ጥያቄ የጻፋችሁትን ማስታወቂያ ለክፍል ጓደኞቻችሁ ካነበባችሁ በኋላ፡-

ሀ. ጓደኞቻችሁም የጻፋችሁት ማስታወቂያ ምን ያህል ውጤታማ እንደነበር ግብረ መልስ እንዲሰጧችሁ አድርጉ፡፡

ለ. ጓደኞቻችሁ በጻፋችሁት ማስታወቂያ የተዋወቁ ምርቶችን ለመግዛት ፈቃደኛ ናቸው? ለምን? የማይገዙ ከሆነስ ለምን?

፫ የተለያዩ ጋዜጦችን፣ መጽሔቶችንና በራሪ ወረቀቶችን አንብባችሁ ያገኛችሁትን መረጃ በመጻፍ ለጓደኞቻችሁ በዘገባ መልክ አቅርቡ፡፡

፬. በሬዲዮ ወይም በቴሌቪዥን ከሚተላለፉ መርሀ ግብሮች ጠቃሚ ነው የምትሉትን አንዱን መርጣችሁ አዳምጡና የፅሁፍ ዘገባ አቅርቡ፡፡

## ክፍል አምስት፡- ቃላት

፩. ቀጥሎ የቀረቡት ቃላትና ሀረጋት ከምንባቡ የወጡ ናቸው፡፡ ለነዚህ ቃላት በምንባቡ ውስጥ የሚኖራቸውን ዐውዳዊ ፍች ስጡ፡፡

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. ይተላለፍበታል | ለ. ግኝቶች | ሐ. የሚያስደምመው |
| መ. ደጅ የሚጠኑበት | ሠ. ፈልስፎ | ረ. ተደራሲዎች |
| ሰ. ትንሳኤ | ሸ. የወደቁ | |

፪. ከዚህ በታች በቀረቡት ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ ለተሰመረባቸው ቃላት አገባባዊ ፍች ስጡ፡፡

ሀ. ጉንፋን ብዙ ጊዜ ከአንዱ ወደ ሌላው የሚሰራጨው በትንፋሽ አማካኝነት ነው፡፡

ለ. ጤንነቱ ያልተጠበቀ ትውልድ ተመራማሪ፣ ችግር ፈቺና ፈጣሪ የመሆን እድሉ የመነመነ ነው፡፡

ሐ. ልቦለድ የእውነታው አለም ነፀብራቅ እንጅ ዘገባ አይደለም፡፡

መ. በስራዬ ላይ ያልጠበቅኩት አሜኬላ ገጠመኝ፡፡

ሠ. በህቡዕ ሲንቀሳቀሱ የነበሩት ወንጀለኞች በፖሊስ ቁጥጥር ስር ዋሉ፡፡

## ክፍል ስድስት፡- ሰዋስው

፩. ከዚህ በታች በቀረቡት ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ ተካተው የሚገኙትን ጥገኛ ሀረጎች ለይታችሁ አመልክቱ፡፡

ምሳሌ፡-

መጽሐፉን አንብቤ ጨርሼዋለሁ፡፡

ጥገኛ ሀረግ፡- መጽሐፉን አንብቤ

ሀ. ዘገባውን ያዘጋጀሁበትን ቀን አስታውሰዋለሁ፡፡

ለ. ሁልጊዜ የሚያጠኑ ተማሪዎች አመርቂ ውጤት ያስመዘግባሉ፡፡

ሐ. በሀሳብ ሲብሰለሰል ቆየ፡፡

መ. ስኬታማ ስለሆንኩ ደስተኛ ነኝ፡፡

ሠ. ሀገሩን የሚወድ ትውልድ ራሱን ለማሻሻል ይጥራል፡፡

፪. ከዚህ በታች በቀረበው ምሳሌ መሠረት በዐረፍተ ነገሮቹ ውስጥ የማወዳደር እና የማነጻጸር ተግባር ያላቸውን ሀረጋት ለይታችሁ አመልክቱ፡፡

ምሳሌ፡- እንደወንድሙ እልኸኛ ነው፡፡

አነጻጻሪ ሀረግ፡- እንደወንድሙ --- በዐረፍተ ነገሩ ውስጥ "እሱ" እና "ወንድሙ" ተነጻጽረው ቀርበዋል፡፡እንደ ወንድሙ የሚለው መስተዋድዳዊ ሀረግ የእሱን እልኸኝነት ለማነጻጸር አገልግሏል፡፡

ሀ. እንደአባቷ ትጉህ ሠራተኛ ነች፡፡

ለ. በደረሰበት መከራ እንደወንድሙ ክፉኛ ተጎድቷል፡፡

ሐ. እንደዘመዱ በመካከለኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡

መ. በትምህርቷ እንደአክስቷ ጎበዝ በመሆኗ ተሸለመች፡፡

ሠ. ስራውን እንደጓደኛው ለከፍተኛ ማዕረግ ታጨ፡፡

ረ. ከሥራ ባልደረባው የበለጠ ታታሪ ነው፡፡

፫. የማወዳደር ወይም የማነጻጸር ተግባር ያላቸውን ሦስት ሀረጎችን ጻፉ፡፡

# የምዕራፉ ማጠቃለያ

ምዕራፍ ዘጠኝ ማህበራዊ መገናኛ ብዙኃንንና ተግባቦትን በሚል ርዕስ የቀረበ ሲሆን በስሩም የተለያዩ ጉዳዮች ተነስተዋል፡፡ በማዳመጥ ክፍል ውስጥ የጋዜጠኝነትን ምንነት፣ የቃለ ምልልስን ምንነት፣ በመገኛኛ ብዙኃን ባለሙያ እና በቃለ ምልልስ ሰጪው መካከል የሚኖረውን ግንኙነት በሚመለከት በቅድመ ማዳመጥ ክፍል ተወያይታችኋል፡፡ ምንባቡን ካዳመጣችሁ በኋላ የአድምጦ መረዳት ጥያቄዎችን በመስራት ተለማምዳችኋል፡፡

በክፍል ኹለት ከቴሌቪዥን ወይም ከሬዲዮ ወይም ከድረ ገጽ ወይም ከጋዜጣ ወይም ከመጽሔት የተለያዩ ማስታወቂያዎችን መሰብሰብን፣ የሰበሰበዋችኋቸውን ማስታወቂያዎች ጠቀሜታ መግለጽን እና የማስታወቂያዎችን አድማጭ ወይም ተመልካች መለየትን ተለማምዳችኋል፡፡ እንዲሁም ማስታወቂያዎች የአድማጭን ወይም የተመልካችን ስሜት መቀስቀስን አስፈላጊነት፣ የማስታወቂያዎችን ቋንቋ አጠቃቀም በሚመለከት በመወያየት ሀሳባችሁን የመግለጽ ልምምድ አድርጋችኋል፡፡

በክፍል ሦስት “መገናኛ ብዙኃንና ጋዜጠኝነት” በሚል ርዕስ የቀረበውን ምንባብ መሠረት በማድረግ የተለያዩ የቅድመ ንባብ፣ የንባብ ጊዜ ጥያቄዎችን እና የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን ሰርታችኋል፡፡

በክፍል አራት ጽሕፈትን በሚመለከት በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ማስታወቂያዎችን መጻፍን፣ በጻፋችሁት ማስታወቂያ ላይ በመወያየት ግብረ መልስ መቀበልን፣ የጽሁፍ ዘገባ ማዘጋጀትን ተምራችኋል፡፡

በክፍል አምስት ከምንባቡ ውስጥ የተወሰዱ ቃላትን ዐውዳዊ ፍች መግለጽን፣በዐረፍተ ነገር ውስጥ የተሰመረባቸውን ቃላት አገባባ ፍች መግለጽን ተምራችኋል፡፡

በክፍል ስድስት ደግሞ ጥገኛ ሀረጋትን መለየትን፣ አነጻጻሪ እና አወዳዳሪ ሀረጋትን መለየትን ተምራችኋል፡፡

## የምዕራፉ የክለሳ ጥያቄዎች

ሀ. መገናኛ ብዙኃን ማለት ምን ማለት ነው?

ለ. የቃለ ምልልስ ዋነኛ ዓላማ ምንድን ነው?

ሐ. በሬዲዮ ወይም በጋዜጣ ወይም በቴሌቪዥን ወይም በተለያዩ ማኅበራዊ መገናኛ ብዙኃን የሚቀርቡ ማስታወቂያዎች ምን ጠቀሜታ አላቸው?

መ. የማወዳወር እና የማነጻጸር ተግባር ያላቸውን ሦስት ሀረጋት ጻፉ፡፡

## የግንዛቤ ማመሳከሪያ ቅጽ

፩. ከዚህ በታች በምዕራፍ ዘጠኝ የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ቅጽ ቀርቦላችኋል፡፡ በዚህም መሠረት በእያንዳንዱ ማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ስለመረዳታችሁ እርግጠኛ ከሆናችሁ የ(√)፣ እርግጠኛ ካልሆናችሁ የ(?)፣ ሙሉ በሙሉ ካልተረዳችሁ ደግሞ የ(X) ምልክት በማድረግ ቅጹን አሟሉ፡፡

| ተ.ቁ. | የማመሳከሪያ ነጥቦች | √ | ? | X |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ያዳመጥኩትን ምንባብ መሠረት በማድረግ የቀረቡትን የተለያዩ ጥያቄዎችን መስራት ችያለሁ | | | |
| 2 | ጅምር ሀሳቦችን ማሟላት ችያለሁ | | | |
| 3 | ማስታወቂያዎችን መጻፍ ችያለሁ | | | |
| 4 | የማስታወቂያዎች የቋንቋ አጠቃቀም ሁኔታ ላይ መወያየት ችያለሁ | | | |
| 5 | የቃላትን ዐውዳዊ ፍች መግለጽ ችያለሁ | | | |
| 6 | የንጽጽር ሀረጋትን መለየት ችያለሁ | | | |
| 7 | መዝገበ ቃላትን መጠቀም ችያለሁ | | | |
| 8 | የተለያዩ የጊዜ አመልካች ግሶችን መለየትና መጠቀም ችያለሁ | | | |

፪. ከዚህ በላይ በቀረበው ቅጽ የ(?) እና የ(X) ምልክት ያደረጋችሁባቸውን ነጥቦች በሚገባ እስክትገነዘቡ ድረስ የምዕራፉን ትምህርት ደጋግማችሁ ከልሱ፡፡

## ሙዳዩ ቃላት

| | |
|---|---|
| ሀሴት | ደስታ |
| ሂስ | በደካማ ጎን ላይ የሚያተኩር አስተያየትና ነቀፋ፣ በስነ ጽሁፍ ሥራ ላይ የሚሰነዘር መዛኝ አስተያየት |
| ሌጣ | ነጠላ፣ ብቸኛ፣ ምንም ያልያዘ፣ ባዶ፣ የምታጠባው የምታዝለው ወይም በሆዷ የተረገዘ ልጅ የሌላት |
| መመረቅ | መባረክ፣ መቀደስ፣ ማመስገን፣ ጭማሪ መስጠት |
| መስተጋብር | አንድ ነገር ከሌላው ጋር ያለው ግንኙነት |
| መስዋዕት | ለአምልኮ የሚሰጥ፣ የሚቀርብ ስጦታ፣ ህይወቱን አሳልፎ ሰጠ |
| መብረቅ | የሰማይ ብልጭታን ተከትሎ የሚሰማ ከፍተኛ የፍንዳታ ድምጽ፣ ነጎድጓድ |
| ማዕበል | ኃይለኛ ነፋስ በባህር፣ በውቅያኖስ ላይ የሚፈጥረው የውሃ መናወጥ፣ ሞገድ |
| መከላከል | ማገድ፣ ማጠር፣ መዝጋት፣ ማቆም፣ መንፈግ |
| መዋቢያ | ማማሪያ፣ መቆነጃጃ፣ መሸገኛ |
| መደብ | ከጭቃ፣ ከአፈር፣ የሚሰራ መኝታ፣ የህብረተሰብ ክፍፍል የሚያመለክት፣ ከቅርጫት ስጋ አንዱ ክፍል፣ ችግኝ ለማፍላት የሚዘጋጅ ቦታ፣ ነጋዴዎች ሸቀጣቸውን የሚያስቀምጡበት የተደለደለ ቦታ |
| መግነጢስ | ብረትን ወደራሱ የሚስብ ብረት (ማግኔት) |

| | |
|---|---|
| ማመጣጠን | እኩል ማድረግ፣ አቻ ማድረግ |
| ማስተዋል | መመልከት፣ መቃኘት፣ መመርመር፣ ልብ ማድረግ |
| ማዜም | መዝፈን፣ ማቀንቀን |
| ማደራጀት | ማዋቀር፣ ሥርዓት ማስያዝ |
| ማፈግፈግ | ወደኋላ መመለስ፣ መሸሽ፣ በአቋም አለመጽናት |
| ምሰሶ | አምድ፣ ረጅም እንጨት፣ መለሎነት ያለው በቤት መካከል ቆሞ ዋልታ የሚሸከም፣ የኤሌክትሪክ የስልክ … ሽቦ የሚዘረጋበት ቀጥ ያለ ረዥምና መጠነኛ ውፍረት ያለው እንጨት |
| ምንጭ | የአንድ ነገር መገኛ፣ መነሻ፣ ምክንያት፣ መረጃ፣ ከመሬት ውስጥ እየወጣ የሚፈስ ውሃ፣ መፍለቂያ |
| ሰቀቀን | ናፍቆት፣ ሀዘን፣ ችግር፣ አግኝቶ ከማጣት የሚገኝ ቅዝታ |
| ሰናይ | መልካም፣ ውብ፣ ደግ፣ በጎ፣ ደስ የሚያሰኝ |
| ስርጭት | መተላለፍ፣ ብዙ ቦታ መድረስ |
| ስብ | ነጭና ቅባትነት ያለው ጮማ ስጋ፣ በዕፅዋት ወይም በእንስሳት ውስጥ የሚከማችና ባስፈለገ ጊዜ ኃይል የመስጠት ጠቀሜታ ያለው፣ ለም የዳበረ መሬት፣ ወፍራም ደንዳና |
| ረቂቅ | በጣም የላመ፣ የደቀቀ፣ ጥንቃቄና ጥበብ የሚጠይቅ የጌጣጌጥ ሥራ፣ ለማንበብ የሚያስቸግር በትንንሽ ፊደል የተጻፈ፤ በዓይን የማይታይ፣ በእጅ የማይዳሰስ፣ ውበውስብስብነቱ የተነሳ በቀላሉ ለማየት የማይቻል፣ ሊጨመርበት ወይም ሊቀነስበት የሚችል የመጀመሪያ ጽሁፍ |
| ረባዳ | በተራራዎችና በአምባ ምድሮች መካከል የሚገኝ ግድጓዳ ወይም ዝቅተኛ ስፍራ |

| | |
|---|---|
| ረግረጋማ | ከወንዝ፣ ከሀይቅ፣ ከዝናብ በሚገኝ ውሃ የተሞላ አካባቢ |
| ቅልቅል | ድብልቅ፣ ስብጥር |
| ቅርስ | በቅድመ ታሪክና በታሪክ ዘመን በስነ-ጥበብ፣ በሳይንስ፣ በባህል ወይም በታሪክ ከፍተኛ ተፈላጊነት ያለው፣ የህንጻ ወይም የመታሰቢያ ቦታ ወይም ሀውልት፣ የጥንታዊ ከተማ ፍርስራሽ፣ የመቃብር ቦታ፣ የዋሻ ስዕል፣ የድንጋይ ላይ ጽሁፍ፣ የብራና ጽሁፍ፣ የተጠራቀመ፣ የተካበተ ሀብት፣ ጥሪት |
| ቅይጥ | ድብልቅ፣ ቅልቅል፣ ዝንቅ፣ የልዩ ልዩ ነገሮች አንድነት ቅልቅል |
| በይነ መረጃ | የመረጃ መረብ፣ ድረ ገጽ |
| ተደራሲያን | ታዳሚዎች፣ ተመልካቾች፣ አድማጮች |
| ትልልፍ | መተላለፍ፣ አልፎ መሄድ |
| ትንኮሳ | ጠብ መጫር፣ መጀመር፣ ፍለጋ፣ ለኮፍ ማድረግ |
| ነፍሰ ጡር | የፀነሰች፣ በማህፀኗ ፅንስ የያዘች፣ የከበደች፣ ያረገዘች |
| አመክንዮ | ምክንያት |
| አምልኮ | እምነትን ለመግለጽ ሰዎች የሚያከናውኗቸው ድርጊቶች |
| አራስ ነብር | ቁጡ፣ ኃይለኛ ሰው |
| አቀንቃኝ | የዜማ፣ የዘፈን ወራጅ (አቀንቃኝ ገፀ ባህርይ - አውራ፣ ዋና፣ ዐብይ ገፀ ባህርይ) |
| አውታር | የድንኳን መወጠሪያ ገመድ፣ የበገና፣ የክራር ጅማት |
| አድባር | የመናፍስት ወይም የቆሌ ዓይነት፣ ዛፍ ማዕከል ያደረግ የመናፍስት ወይም የቆሌ አምልኮ የሚከናወንበት አካባቢ፣ ትልቅ፣ ጎምቱ፣ የተከበረ ሰው |

| | |
|---|---|
| እምነት | ሃይማኖት፣ አምልኮ፣ እርግጠኛነት |
| እርቃኗን | ያለ ልብስ ራቁቷን፣ ብቻዋን |
| እኩይ | ምግባረ ቢስ፣ በጣም የከፋ፣ ርህራሄና ምህረት የማያውቅ |
| እየተንሰራፋ | ሰፊ ስፍራ እየያዘ፣ እየተባዛ፣ እየተዋለደ |
| ክምችት | የተከማቸ፣ ስብስብ፣ እክብ፣ ጥርቅም፣ ያልተመረተ ማዕድን፣ የአለት ብዛት |
| ክፍተት | በሁለት ነገሮች መካከል የሚገኝ ባዶ ቦታ፣ ቀዳዳነት፣ ስንጥቅነት፣ የአንድ ነገር ግንኙነት መቋረጥና ክፍት ሆኖ መገኘት |
| ወለላ | ሰፈፍ የሌለበት ንፁህ ማር፣ ሩህሩህ ደግ ሰው |
| ወጥመድ | አድፍጦ ሜዣ፣ አሽክላ፣ ከባቢ |
| ውሰት | መዋስ፣ ከሌላው መበደር፣ መውሰድ |
| ዕንቁ | በባህር ውስጥ የሚገኝ ከወርቅ የሚበልጥ የከበረ ድንጋይ |
| ዘዬ | ፈሊጥ፣ የአሰራር መንገድ፣ ልማድ፣ ቀበልኛ፣ የአካባቢ አነጋገር |
| የሚያስደምም | የሚያስገርም፣ የሚያስደንቅ፣ እጅን በአፍ የሚያስጭን |
| የተዛባ | የተፋለሰ፣ ቅደም ተከተላቸውን የሳቱ፣ የተሳሳቱ |
| ይተነብያሉ | አንድ ነገር ከመድረሱ ወይም ከመደረጉ አስቀድሞ ነገሩ ወደፊት እንደሚደረግ ወይም እንደሚደርስ አስቀድሞ መናገር |
| ይፋ ሆነ | ተነገረ፣ ተወራ፣ ሽሽግነቱ ቀረ፣ ተገለጸ |

| | |
|---|---|
| ደለል | በወራጅ ወሃ፣ በጎርፍ ወይም በነፋስ ተሸካሚነት ተጠርጎ ወይም ተወስዶ በሌላ ቦታ የተከማቸ ለም አፈር፣ የአሸዋ ዝቅጠት |
| ደሴት | ዙሪያውን በባህር የተከበበ መሬት |
| ደጅ መጥናት | ጉዳዩን ለማስፈጸም መጉላላት፣ መመላለስ |
| ዳርቻ | ዳር፣ መሀል ያልሆነ፣ ድንበር |
| ድሪቶ | ያረጀ፣ የተቀደደ፣ የተቦጫጨቀ ልብስ |
| ጋጠወጥነት | ስድ አደግነት፣ ባለጌነት፣ ልቅነት፣ ሥርዓት የለሽነት |
| ግብይት | የሸቀጥ ዕቃዎች ልውውጥ |
| ጎራ | ከፍተኛ ቦታ፣ ኮረብታ፣ ሚና፣ አንጃ፣ ፊና ወገን፣ ካባ፣ ደረደረ፣ ከመረ |
| ፈጠራ | ልቦለድ፣ አዲስ ቁስ አካላዊ እሴቶችንና መንፈሳዊ ፋይዳዎችን የመፍጠር ችሎታና እንቅስቃሴ፣ በምርመራ፣ በሙከራ የሚገኝ አዲስ ነገር፣ ውሸት፣ የፈጠራ ወሬ |

## ዋቢ ጽሑፎች


ማዕረጉ በዛብህ (1995) የጋዜጠኝነት ሙያ ንደፈሃሳብና አተገባበሩ። አዲስ አበባ፣ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት።

ባየ ይማም (2000) የአማርኛ ሰዋስው፣ የተሻሻለ ሁለተኛ እትም። አዲስ አበባ፣ እሌኒ ማተሚያ ቤት።

__________ (2010) አጭርና ቀላል የአማርኛ ሰዋስው (4ኛ ዕትም)። አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች።

ብርሃኑ ገበየሁ (1999) የአማርኛ ሥነግጥም። አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች።

አቡሽ አያሌውና ሌሎች (ዓ.ም. ያልተጠቀሰ) የኮሮናው መብረቅ። አዲስ አበባ፣ ሔሪቴጅ ኅትመትና ንግድ ኃላ/የተ/የግል ማኅበር።

ኢፌዴሪ ባህልና ቱሪዝም ሚስቴር (2008) መሰረታዊ የስነጽሑፍ ማሰልጠኛ ሞጁል። አዲስ አበባ፣ ኢኒስፓየር ፕሪንቲነግ ፕረስ።

እንዳለጌታ ከበደ (1996) ከጥቁር ሰማይ ስር እና ሌሎች አጫጭር ልቦለዶች። አዲስ አበባ፣ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

ዘሪሁን አስፋው (2005) የስነጽሁፍ መሰረታውያን(7ኛ ዕትም)። አዲስ አበባ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

ገብረ ክርስቶስ ደስታ (1996) መንገድ ስጡኝ ሰፊ። አዲስ አበባ።

ጌታሁን አማረ (1989) ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው። አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች።

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን (2002) ስለግብር/ታክስ አስተዳደር አስመልክቶ ከተዘጋጀ የግንዛቤ ማስጨበጫ ማብራሪያ፡፡ አዲስ አበባ፣ ያልታተመ፡፡

ዮናስ አድማሱ (1966) አማርኛ ለኮሌጅ ደረጃ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ያልታተመ)፡፡

ደበበ ሠይፉ (1992) ለራስ የተጻፈ ደብዳቤ (የብርሃን ፍቅር ቅጽ ፪)፡፡ አዲስ አበባ፣ ሜጋ አሳታሚ ድርጅት፡፡

ደበበ ኃይለጊዮርጊስ (2008) ቅድመ ኮሌጅ አማርኛ፡፡ አዲስ አበባ፣ አስቴር ነጋ አሳታሚ ድርጅት፡፡

ጌታሁን አማረ (1989) ዘመናዊ የአማርኛ ሰዋስው፡፡ አዲስ አበባ፣ አልፋ አታሚዎች፡፡

ፈቃደ አዘዘ (1991) የስነቃል መምሪያ፡፡ አዲስ አበባ፣ ኢትዮ ጥቁር ዓባይ አታሚዎች፡፡

ፋንታሁን እንግዳ (2009) የተውኔት ድርሰት አፃፃፍ ዘዴ (4ኛ ዕትም)፡፡ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ድርጅት፡፡

# የአማርኛ የፊደል ገበታ

| ግዕዝ | ካዕብ | ሣልስ | ራብዕ | ኃምስ | ሳድስ | ሳብዕ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | ሁ | ሂ | ሃ | ሄ | ህ | ሆ |
| ለ | ሉ | ሊ | ላ | ሌ | ል | ሎ |
| ሐ | ሑ | ሒ | ሓ | ሔ | ሕ | ሖ |
| መ | ሙ | ሚ | ማ | ሜ | ም | ሞ |
| ሠ | ሡ | ሢ | ሣ | ሤ | ሥ | ሦ |
| ረ | ሩ | ሪ | ራ | ሬ | ር | ሮ |
| ሰ | ሱ | ሲ | ሳ | ሴ | ስ | ሶ |
| ሸ | ሹ | ሺ | ሻ | ሼ | ሽ | ሾ |
| ቀ | ቁ | ቂ | ቃ | ቄ | ቅ | ቆ |
| በ | ቡ | ቢ | ባ | ቤ | ብ | ቦ |
| ተ | ቱ | ቲ | ታ | ቴ | ት | ቶ |
| ቸ | ቹ | ቺ | ቻ | ቼ | ች | ቾ |
| ኀ | ኁ | ኂ | ኃ | ኄ | ኅ | ኆ |
| ነ | ኑ | ኒ | ና | ኔ | ን | ኖ |
| ኘ | ኙ | ኚ | ኛ | ኜ | ኝ | ኞ |
| አ | ኡ | ኢ | ኣ | ኤ | እ | ኦ |
| ከ | ኩ | ኪ | ካ | ኬ | ክ | ኮ |
| ኸ | ኹ | ኺ | ኻ | ኼ | ኽ | ኾ |
| ወ | ዉ | ዊ | ዋ | ዌ | ው | ዎ |
| ዐ | ዑ | ዒ | ዓ | ዔ | ዕ | ዖ |
| ዘ | ዙ | ዚ | ዛ | ዜ | ዝ | ዞ |
| ዠ | ዡ | ዢ | ዣ | ዤ | ዥ | ዦ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የ | ዩ | ዪ | ያ | ዬ | ይ | ዮ |
| ደ | ዱ | ዲ | ዳ | ዴ | ድ | ዶ |
| ጀ | ጁ | ጂ | ጃ | ጄ | ጅ | ጆ |
| ገ | ጉ | ጊ | ጋ | ጌ | ግ | ጎ |
| ጠ | ጡ | ጢ | ጣ | ጤ | ጥ | ጦ |
| ጨ | ጩ | ጪ | ጫ | ጬ | ጭ | ጮ |
| ጰ | ጱ | ጲ | ጳ | ጴ | ጵ | ጶ |
| ጸ | ጹ | ጺ | ጻ | ጼ | ጽ | ጾ |
| ፀ | ፁ | ፂ | ፃ | ፄ | ፅ | ፆ |
| ፈ | ፉ | ፊ | ፋ | ፌ | ፍ | ፎ |
| ፐ | ፑ | ፒ | ፓ | ፔ | ፕ | ፖ |
| ቨ | ቩ | ቪ | ቫ | ቬ | ቭ | ቮ |

## የፊደል ቅደም ተከተል

ሀ. የመጀመሪያ ፊደል = ግዕዝ

ሁ. ሁለተኛ ፊደል = ካዕብ

ሂ. ሶስተኛ ፊደል = ሳልስ

ሃ. አራተኛ ፊደል = ራብዕ

ሄ. አምስተኛ ፊደል = ሀምስ

ህ. ስድስተኛ ፊደል = ሳድስ

ሆ. ሰባተኛ ፊደል = ሳብዕ

# የኢትዮጵያ ቁጥሮች /የአማርኛ ቁጥር/

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ፩_1 | ፲፩_11 | ፴_30 | ፻፲ _110 | ፳፻ _2000 | ፲፼_100,000 |
| ፪_2 | ፲፪_12 | ፵_40 | ፪፻ _200 | ፻_3000 | ፳፼_200000 |
| ፫_3 | ፲፫_13 | ፶_50 | ፫፻ _300 | ፵፻_4000 | ፼_300,000 |
| ፬_4 | ፲፬_14 | ፷_60 | ፬፻ _400 | ፶፻_5000 | ፵፼_400,000 |
| ፭_5 | ፲፭_15 | ፸_70 | ፭፻ _500 | ፷፻_6000 | ፶፼_500,000 |
| ፮_6 | ፲፮_16 | ፹_80 | ፮፻ _600 | ፸፻_7000 | ፷፼_600,000 |
| ፯_7 | ፲፯_17 | ፺_90 | ፯፻ _700 | ፻ _8000 | ፸፼_700,000 |
| ፰_8 | ፲፰_18 | ፻ _100 | ፰፻ _800 | ፺፻_9000 | ፼_800,000 |
| ፱_9 | ፲፱_19 | ፻፩_101 | ፱፻ _900 | ፼_10,000 | ፺፼_900,000 |
| ፲_10 | ፳ _20 | ፻፪_102 | ፲፻_1000 | ፪፼_20,000 | ፻፼_1,000,000 |

# አማርኛ ቋንቋ
# የተማሪ መጽሐፍ
# ዘጠነኛ(፱ኛ) ክፍል